# መጽሐፈ ሰዓታት
# በመቅደሱ ሚዛን

የሰው መንገድ ሁሉ በዓይኖቹ ፊት ንጹሕ ነው፤
እግዚአብሔር ግን መንፈስን ይመዝናል፤
ምሳ16፡2

# ማውጫ


መግቢያ.. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. . .. .. . 3

ምዕራፍ 1 የመጽሐፈ ሰዓታት ስህተቶች.. .. ... .. ... .. . 7

ስለ ሰንበት.. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. .. ... .. . 7

ስለ ቍስቋም/ታሪካዊ ስለሚባሉ ቦታዎች/ .. .. .. 11

ስለ ማርያም.. .. .. .. .. .. .. .. .. .. ... .. . 12

ስለ ጊዮርጊስ.. .. .. .. .. .. .. .. .. .. ... .. . 30

ስለ ተክለሃይማኖት.. .. .. .. .. .. .. ... .. . 36

ምዕራፍ 2 መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ የመጽሐፈ ሰዓታት ውዳሴዎችና ልመናዎች. .. . ... .. ... . 45

የመጀመሪያው ቅዱስ ቅዱስ.. .. .. .. .. .. .. ... 45

ሁለተኛው ቅዱስ ቅዱስ.. .. .. .. .. .. .. ...... 47

ምገስን.. .. .. .. .. .. .. .. .. ... .. .. .. .. ... 51

ሦስተኛው ቅዱስ ቅዱስ. .. .. ... .. .. .. .. ... . 54

በኢየሱስ ስም የቀረቡና የኢየሱስን አማላጅነት የሚገልጹ ልመናዎች.. ..... .. .. .. ... ... .. .. 56

ምዕራፍ 3 የመጽሐፈ ሰዓታት ልመናዎችና ውዳሴዎች እርስበርሳቸው ሲፋለሱ. .. .. ... .. .. .. ... .. 60

ምዕራፍ 4 መጽሐፈ ሰዓታት ለምን የሚፋለሱ ክፍሎች ሊኖሩት ቻለ?.. .. .. .. ...... .. .. .. .... .. .. .. 65

ማጠቃለያ. .. .. .. .. .. .. .. ... ... .. .. .... .. ... 68


---

«መጽሐፈ ሰዓታት በመቅደሱ ሚዛን»


በማናቸውም መንገድ ይህንን መጽሐፍ በከፊልም ሆነ በሙሉ ያለ አሳታሚው የጽሑፍ ፈቃድ ማባዛት በሕግ የተከለከለ ነው::



የመጀመሪያው እትም በወርኃ ጥቅምት 1993 ዓ.ም.
ሁለተኛው እትም በወርኃ ጥቅምት 1995 ዓ.ም.

**"Metshafe Se'atat" According to the Balance of the Sanctuary.**
**First Edition October 2000**
**Second Edition October 2002**



**Copyright © by GBV**



**Published by BGNLJ- A Nonprofit Organization, Devoted to the work of the Lord Jesus Christ and spread of His Truth.**
**Address: P.O.Box 14787, Addis Ababa, Ethiopia.**
**Printed in Ethiopia**

# መግቢያ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

በኢትዮጵያ በይበልጥም ከዓፄ ዘርዓያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ወዲህ ከሚታወቁትና በበርካታ አድባራት ሌሊት ሌሊት ከሚዜሙት መጻሕፍት መካከል አንዱና ዋንኛው መጽሐፈ ሰዓታት ነው። ከመስከረም 25 ጀምሮ እስከ ሕዳር 6 ማለትም ወርኃ ጽጌ በሚባለው ወቅት ሌሊት በዜማ ሲባል ይታደራል። በይበልጥም ከነሐሴ 1 እስከ 16 በተለምዶ ጾመ ፍልሰታ ተብሎ በሚታወቀው ወቅት ሰዓታት አይታጎልም። በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ ዐቢይ ጾም በሚባለው የጾም ወቅትም ይዜማል። አንዳንድ የታወቁና ዝነኛ ሰዎች ሲሞቱም ሰዓታት ይቆምላቸዋል። ይህንንም መጽሐፈ ሰዓታት ተብሎ የሚታወቀውን መጽሐፍ አባ ጊዮርጊስ የተባሉ መነኩሴ ደርሰውታል ተብሎ ይነገራል። እኒህም መነኩሴ ጋስጫ ተብሎ በሚታወቀው አካባቢ እንደተወለዱ መጽሐፈ አርጋኖን በሚባለው መጽሐፍ መቅድም ላይ ተተርኳል። መጽሐፈ ሰዓታትን አባ ጊዮርጊስ ደረሱት ለማለት በቂ የሆነ ማስረጃ ባይገኝም አብዛኛዎቹ ሰዓታት ቋሚዎች የአባ ጊዮርጊስ ነው ይላሉ።

መጽሐፈ ሰዓታትን ማን ደረሰው? እውን መጽሐፈ ሰዓታት ትክክለኛ የክርስቲያን ድርሰት ነውን? በውስጡ የያዛቸው ሐሳቦችስ በእውነተኛው ቅዱስ መጽሐፍ ሲመዘኑ ምን ይመስላሉ? ጠቀሜታቸው አሊያም ጎጂነታቸው እንዴት ነው? ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋርስ ምን ያህል ዝምድና አላቸው? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሣቱ ስለዚህ መጽሐፍ ምንነት ለማወቅ ለሚሹና እየተጠቀሙበት ላሉ ሁሉ አግባብነት ያለው ነው። ይህ በሚባልበት ጊዜ ግን ብዙዎች የመጽሐፈ ሰዓታት ተጠቃሚዎች መገረምና መደነቅ ብሎም ቅሬታ ሳይሰማቸው አይቀርም፤ በተለይም መጽሐፉ የያዘውን ስህተት በተመለከተ «ከጥንት ጀምሮ አባቶቻችን ሲጠቀሙበት የቆዩትን እንዴት ዛሬ ውሸት አለበት ልንል እንችላለን? ስሕተትስ ቢኖርበት ከአሁን በፊት ያልታረመውን እንዴት አሁን ማስተካከል ይቻላል? አባቶቻችን እስከ አሁን ድረስ ያቆዩልንን እንደዚያው እንደነርሱ በእምነት መቀበል ነው እንጂ መጠራጠሩ ወይም መቃሙ የመናፍቅነት አመለካከት ነው» በማለት የመጽሐፉን ስህተት መቃወሙን እንደ ድፍረት ሊቈጥሩት ይችላሉ። ከዚህም የተነሣ አንዳንዶች በግድ የለሽነት መጽሐፉ በያዘው ውሸት ላይ አስተያየት ከመስጠትና ተቃውሞ ከማቅረብ ሊቆጠቡ ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ እዚህ ላይ ብዙዎች ሊገነዘቡት የሚገባው ነገር ቢኖር ከሺህ ዓመታት በፊትም ይጻፍ ትናንትም ይጻፍ አንድ መጽሐፍ በዕድሜ ብዛት ብቻ እውነተኛ ሊሆን እንደማይችል ነው፤ በተቃራኒውም አንድ እውነት በቅርቡ ስለተጻፈ ሐሰተኛ ሊሆን አይችልም፤ ብዙ ሰዎች ስለተስማሙበትም አንድ ውሸት እውነት ሊሆን አይችልም፤ አንድ እውነት ደጋፊ ስለ አጣም ውሸት ሊሆን

አይችልምና የመጽሐፈ ሰዓታት ተጠቃሚዎች «ወኲሎ አመክሩ ወዘሠናይ አጽንዑ ማለትም ሁሉን ፈትኑ መልካሙን ያዙ»/1ተሰ5:21/ በሚለው የተቀደሰ መመሪያ በመነሳሣት መጽሐፈ ሰዓታትን ለመፈተን መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

ቀጣዩ ጥያቄ መፈተኛው ምንድን ነው? ትክክል እንደሆነና እንዳልሆነ ለማወቅ መመዘኛውስ ምንድን ነው? ሰው ለእግዚአብሔር የሚያቀርበውስ የምስጋና ስጦታ በምን ይመዘናል? የሚል ይሆናል። ይህንንም በተመለከተ የእግዚአብሔር ቃል ሲናገር «እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፤ አንተ የእስራኤልን ልጆች ቍጥር ተቀብለህ በቈጠርሃቸው ጊዜ መቅሠፍት እንዳይሆንባቸው በቈጠርሃቸው ጊዜ ከእነርሱ ሰው ሁሉ እንደቍጥራቸው መጠን የነፍሱን ቤዛ ለእግዚአብሔር ይስጥ፤ አልፎ የሚቈጠር ሁሉ ግማሽ ሰቅል እንደመቅደሱ ሰቅል ሚዛን ይሰጣል፤ .. ስነፍሳችሁ ማስተስረያ የእግዚአብሔርን ስጦታ ስትሰጡ ባለጠጋው ከሰቅል ግማሽ አይጨምር፤ ድሀውም አያጕድል» ይላል/ዘጸ30:11-15/።

ከዚህ በላይ በተቀመጠው ንባብ መሠረት በዘመነ ብሉይ ሰው ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው የነፍሱ ቤዛ ወይም የማስተስረያ ስጦታ በታመነው «የመቅደሱ ሚዛን» መመዘን እንዳለበት ተደንግጎ እናገኛለን፤ ምክንያቱም ነፍስን በተመለከተ ያለው ነገርና ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ስጦታ በሌሎች ታማኝነት በሚጎድላቸውና ከተፈለገው በላይ በሚጨምሩና ከሚፈለገው በታች በሚያሳንሱ ሚዛኖች ሊመዘን ስለማይገባው ነው። እስራኤልም ስለነፍሳቸው በእግዚአብሔር ፊት ያቀርቡት የነበረው ቤዛም በመቅደሱ ሚዛን እንዲለካ የተወሰነው ከሁሉም በላይ ነፍስ በግዴለሽነት የምትታይ ስላልሆነችና ነፍስን የሚመለከት ነገር ሁሉ እርግጠኝነት ያለውና ታማኝነቱ በመለኮታዊ ሚዛን የተመሰከረለት እንዲሆን የተገባው ስለነበረ ነው፤ ከዚህም ባሻገር ስለነፍስ ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ሁሉ እግዚአብሔር ከሚፈልገው በላይ ወይም በታች መሆን ስለሌለበት እስራኤል ስለነፍሱ የሚያቀርበው ስጦታም መመዘን የነበረበት በሰው ሚዛን ሳይሆን በእግዚአብሔር ሚዛን ነው።

በዚህ ዘመንም ማንኛውም ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ውዳሴ ወይም ምስጋና ትክክለኛነት የሚመዘንበት ዋነኛው የመቅደሱ ሚዛን ከመጽሐፍ ቅዱስ በቀር ሌላ ሊሆን እንደማይችል የሕያው እግዚአብሔር ወዳጆች ሁሉ በውል ይገነዘቡታል። በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ አፈ ታሪክን በሚከተሉ ሰዎች ዘንድ «አበው መጻሕፍትን ከውኃና ከእሳት ጥለዋቸው ሳይርሱና ሳይቃጠሉ በመቅረታቸው ትክክለኛነታቸው ተረጋገጠ» እየተባለ መጻሕፍት በውኃና በእሳት ሊፈተኑ እንደሚችሉ ሲነገር ይሰማል። ነገር ግን ውኃና እሳት መጻሕፍቱን የማይምሩ በመሆናቸው አባባሉ እውነትን በሚፈልጉ ሰዎች ዘንድ እንደተረት ይቈጠራል። ትላንት እንደነበረው ሁሉ ዛሬም

መጻሕፍት የሚመዘኑት በትክክለኛነቱ በዘመናት መካከል ጥርጥር በሌለበት በእግዚአብሔር ቃል ማለትም በመጽሐፍ ቅዱስ ነው:: የሥጋ ሁሉ ነፍስ ይህን ልትክድ አትችልም:: የእግዚአብሔር ቃል ለማያምኑ የሚባላ እሳት ለሚያምኑት ደግሞ ከእድፍ የሚያጠራ ውኃ ነውና መጽሐፈ ሰዓታትን በእግዚአብሔር ቃል ልንፈትነው የተገባ ነው::

ቀደም ባሉት ዘመናት ቅዱሳት መጻሕፍት በእጅ የሚገለበጡ ስለነበሩ የአገራችን ምእመናን በተገኙት ድርሰቶች ሳይመረምሩ ሲጠቀሙ መኖራቸው እርግጥ ነው:: ዛሬ ግን ቅዱሳት መጻሕፍት ምእመናን በሚረዱት ቋንቋ ተተርጉመው በኅትመት ተባዝተው በምእመናን እጅ በመግባታቸው ሰው ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል እያወቀ ነውና የዚህን የሰዓታት መጽሐፍ ድርሰት ትክክለኛነት መመርመር መጽሐፍ ቅዱስ በእጁ ላለው ሰው ሁሉ የሚቻል ነው:: ሆኖም ብዙ የአገራችን ምእመናን መጽሐፈ ሰዓታት የተጻፈበትን የግእዝ ቋንቋ የማይችሉ በመሆናቸው ይበልጥ አጥንተው ፍሬውን ከገለባው እምነቱን ከክህደቱ ይለዩ ዘንድ ለማገዝ ሲባል ይህች አነስተኛ መጽሐፍ ተዘጋጅታለች:: ስለሆነም አንባቢያን በመጽሐፍ ቅዱስና በዚህች አነስተኛ መጽሐፍ በመታገዝ በመጽሐፈ ሰዓታት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚጣላውን ነውር የሆነ ትምህርት እንዲለዩ ሲባል የመጽሐፈ ሰዓታት ድርሰት ግእዙ ከነትርጓሜው አብሮ ቀርቧል:: የዚህች መጽሐፍ ዓላማም ይህ ነው እንጂ የማንንም የእምነት ድርጅት ለማንቋሸሽ አይደለም::

ምንም እንኳን በመጽሐፈ ሰዓታት ውስጥ የሚገኙት ትምህርቶች ለብዙ ዘመናት ሳይጣሩ አንድ ጻድቅ ወይም ቅዱስ እንደደረሳቸው ተቈጥረው ሰፊ ቦታ ይዘው ቢቆዩም ዛሬ ግን መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብ ማንኛውም ቅን አንባቢ «ሁሉን ፈትኑ» በሚለው የተቀደሰ መመሪያ ተነሳሥቶ መጽሐፈ ሰዓታትን ቢመረምር በመጽሐፍ ቅዱስ ሲመዘኑ ስህተትና ክህደት የሆኑ በርካታ የኑፋቄ ሐሳቦችንና የተዛቡ አምልኮዎችን ያገኛል፤ ስለሆነም በመጽሐፈ ሰዓታት ውስጥ የሚገኙ የስሕተት ትምህርቶች እጅግ ብዙ ከመሆናቸው የተነሣ ሁሉንም የያዛቸውን ስህተቶች በዚህች አነስተኛ መጽሐፍ መገምገም የማይቻል በመሆኑ የተወሰኑት ብቻ ተመርጠው ለአብነት በምዕራፍ አንድ ሲቀርቡ ቀሪውን የመጽሐፈ ሰዓታት ንባብ በመጽሐፍ ቅዱስ መመዘኑ ለምእመናን ተትቷል:: በተጨማሪም መጽሐፈ ሰዓታት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጣጣሙ ጥቂት ትምህርቶችን ይዟል፤ ይህም በብዙ ስህተቶች ውስጥ ጥቂት እውነቶችን አስገብቶ መያዙ መጽሐፉን ትክክለኛ እንደማያስብለው በሁሉ ዘንድ የታወቀ ነው:: ይሁን እንጂ እውነትን ከብዙ ስህተቶች መካከል ለይቶ ማውጣቱም አግባብነት ያለው ሆኖ በመገኘቱ መጽሐፈ ሰዓታት በውስጡ የያዛቸው ጥቂት እውነቶች በዚህች መጽሐፍ በአንድ ላይ ተሰብስበው በምዕራፍ ሁለት ቀርበዋል:: በሌላ በኩል ደግሞ መጽሐፈ ሰዓታት የማይጣጣመው

ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ብቻ ሳይሆን ከራሱም ጋር በመሆኑ እርስ በርሱ የሚፋለስባቸውን ንባባት ለአብነት ያህል መርጠን በምዕራፍ ሦስት አቅርበናቸዋል::

የመጽሐፈ ሰዓታት እትሞች በይዘት የተለያዩ ናቸው:: አንዱ በያዘው ላይ ሌላው ይጨምራል፤ እንዲሁም አንዱ ዓይነት መጽሐፈ ሰዓታት ከያዘው ላይ ሌላው ይቀንሳል:: በስፋት የሚታወቁት ሦስት ሲሆኑ እነርሱም ከደብረ አባይ የሚወጡ ደቀመዛሙርት በእጅ የሚጽፉት ቅጅ፣ በዘልማድ የአሥመራው ሰዓታት እየተባለ የሚጠራውና የተስፋ ገብረሥላሴ የመጽሐፈ ሰዓታት እትም ናቸው፤ በዚህች አነስተኛ ጽሑፍ ውስጥ ለጥናታችን መሠረት ያደረግነው በ1985 ዓ.ም. የታተመው እና 428 ገጾች ያሉት የተስፋ ገብረሥላሴ እትም ነው፤ ለጥናት የቀረበው የመጽሐፈ ሰዓታት ክፍል የተወሰደበት ገጽ ሲጠቀስ አንባቢው የግእዙን ሙሉ ንባብ ከዚሁ የተስፋ ገብረ ሥላሴ እትም ከሆነው መጽሐፈ ሰዓታት ውስጥ ያገኛል:: ይሁን እንጂ በጥቂት ቦታዎች በዚህ የተስፋ ገብረሥላሴ እትም የማይገኙ ነገር ግን በአሥመራው እትም የሚገኙት ክፍሎች ለጥናት በተወሰዱ ጊዜ በ1985 ዓ.ም. በኮከበ ጽባሕ ማተሚያ ቤት የታተመው የአሥመራ እትም መጽሐፈ ሰዓታት ከነገጹ ተጠቅሶ ይገኛል:: እንዲሁም በቃል የሚዜም ሆኖ በሕትመት ያልሰፈረ ክፍልም የተጠቀሰበት ቦታ አለ:: ሁሉንም በሰከነ ህሊና የሚያነብ ሰው እነዚህን የተጠቀሱ ክፍሎች በእግዚአብሔር ቃል እየመዘነ በሚያገኘው እውነት ሊታነጽ ይችላል ተብሎ ታምኖበታል::

በዚህች አነስተኛ መጽሐፍም የመጽሐፈ ሰዓታት ድርሰት በመቅደሱ ሚዛን ማለትም በመጽሐፍ ቅዱስ ሲመዘን ምን እንደሚመስል ለማሳየት ጥረት የተደረገ ስለሆነ ከዚሁ በመነሣት ርእሷ «መጽሐፈ ሰዓታት በመቅደሱ ሚዛን» የሚል ሆኗል:: በዚህም እውነትን የሚወዱና ዓመፃን የሚጠሉ ሁሉ ደስ ይላቸዋል::

በዚህች መጽሐፍ የተጠኑት የመጽሐፈ ሰዓታት ንባባት የተመዘኑባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት በ1954 ዓ.ም. በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ከታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: ጥቅሶች ከመዝሙረ ዳዊት ሲጠቀሱ የጥቅሱ ምዕራፍ በቅንፍ ውስጥ ያለው መሆኑን አንባቢው እንዲያስተውል ይጠየቃል::

ወገኖች ሆይ «ነገሩ እንዲህ ይሆንን? ብለው ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ» /ሐዋ17:10-12/ ተብሎ እንደተነገረላቸው እንደ ቤርያ ሰዎች ምንም ዓይነት የሕሊና ተጽዕኖ ሳያድርባችሁ ከንቱ የሆነ ልማድና ወግ ሳያስጨንቃችሁ ማወቅ የሚገባችሁን እንድታውቁ ጸሎታችን ነው፤ «በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው»/ሉቃ24:45/ እንደተባለ የአእምሮ ባለቤት እግዚአብሔር አእምሮውን ለብዎውን ያሳድርባችሁ፤ አሜን::

# ምዕራፍ 1

# የመጽሐፈ ሰዓታት ስህተቶች

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የምንመለከተው በመጽሐፈ ሰዓታት ውስጥ የሚገኙና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጋጩትን ጉልህ ስህተቶችን ነው፤ በታ ለመቆጠብ ሲባል ሁሉንም ስህቶተች በሙሉ ማውጣቱ አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፤ አንባቢው ግን በዚሁ መልክ ቀጣይ ጥናት ማድረግ እንደሚችል ታምኖበት በመጽሐፈ ሰዓታት ውስጥ በእኛ ግምት ጉልህ ሆነው ያገኘናቸውን ስህተቶች ብቻ መርጠን ማጥናቱን የተሻለ አማራጭ አድርገናል፤ ለአጠናን እንዲያመች፣ ስህተቶችን በየመደቡ ለማየት እንዲቻልና አንባቢው በቀላሉ ቀሪ ግድፈቶችን ማጥናት እንዲችል ለማድረግ እነዚህ የተመረጡት ስህተቶች ጠቅለል ባለ መልኩ በየክፍሉ ተከፍለው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## ስለ ሰንበት

«ሰዓሲ ስነ ሰንበተ ክርስቲያን ቅድስት፣ ስውሉደ ሰብእ መድኃኒት፣ ወእስከ ስዓስም ሰፋኒት»

«ስሰው ልጆች መድኃኒት የሆንሽ እስከ ዘስዓስምም ገዥ የሆንሽ የክርስቲያን ሰንበት ሆይ ስም□ስን /አማልጅን/»

/ሰዓሊ ስነ ከሚባስ ክፍስ - ገጽ 30/

የመጽሐፉ ደራሲ ሰንበተ ክርስቲያን የሚለው ዕለተ እሑድን እንደሆነ ከተለመደው አባባል ማወቅ ይቻላል። እሑድን በተመለከተ በግእዙ ሐዲስ ኪዳን «ወበእሑድ ሰንበት መጽአት ማርያም መግደላዊት» የሚል ንባብ ይገኛል/ዮሐ20፡1/። በአማርኛው ግን «ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን ማርያም መግደላዊት ገና ጨለማ ሳለ ማለዳ ወደ መቃብር መጣች» ይላል። ከሳምንቱ በፊተኛው ቀን የሚለው በግሪኩ «μια των σαββατων/ሚያ ቶን ሳባቶን/» የሚለው ቃል ሲሆን ትርጉሙም ያው «ከሳምንቱ በፊተኛው ቀን» የሚል ነው። በግእዙ «ወበእሑድ ሰንበት» የሚለው ንባብ ግን በግሪኩ ስለሌለ የትርጉም ስህተት መሆኑ ግልጽ ነው። እንዲሁም በሌላ በታ «ወበዕለተ እሑድ እንዘ ጉቡአን ንሕነ ከመ ንባርክ ማዕደ» /ሐዋ20፡7/ ይላል፤ ይህም በአማርኛው «ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን እንጀራ ለመቁረስ ተሰብስበን ሳለን...» ተብሎ የተተረጐመ

ሲሆን በዚህኛውም ሆነ በፊተኛው ምንባብ ያለው የግሪኩ ቃል እሁድ ሰንበት እንደሆነች የማያሳይ በመሆኑ ዕለተ እሑድ «ሰንበት» እንደሆነች የሚናገረው የግእዝ ንባብ የትርጉም ስህተት የወለደው መሆኑን እንገነዘባለን፡፡ ለብሉይ ኪዳን ሕዝብ እግዚአብሔር ዕረፍተ ሥጋ እንድትሆናቸው ዕለተ ሰንበትን ሰጥቷቸው ነበር፤ ይሁንና ሰንበት በጥላነት ክርስቶስን ታመለክት ነበር፤ ይህንንም መጽሐፍ ቅዱስ ሲያስረዳ «እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በዓል ወይም ስለ ወር መባቻ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ፤ እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና አካሉ ግን የክርስቶስ ነው» ይላል /ቈላ2:16-17/፡፡ ስለሆነም በአዲስ ኪዳን ሰንበተ ክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እንጂ ዕለተ እሑድ አይደለችም፡፡

ከዚህም ጋር ደግሞ «ንዑ ኀቤየ ኵልክሙ ስሩሐን ወጽዑራን ወአነ አአርፈክሙ ማለትም እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ»/ማቴ11:29/ የሚለውን ማስተዋል ያስፈልጋል፤ ይህንን በመረዳት አንዲት የማትሰማና ሕያዊት ያልሆነች የጊዜ ክፍልፋይ ዕለተ እሑድን ሰንበት ብሎ ማክበርን ትቶ አማናዊውን ሰንበት ክርስቶስን ማክበርና በእርሱም ማረፍ ይገባል፡፡

እጅግ የሚያሳዝነው ደግሞ ዕለቷ «ለውሉደ ሰብእ መድኃኒት ወእስከ ለዓለም ሰፋኒት» ማለትም «ለሰው ልጆች መድኃኒት ለዘለዓለም ገዥ የሆንሽ» መባሏ ነው፡፡ የኑፋቄውን ክፋት ለመረዳት ለዚህች ዕለት የተሰጡትንና መድኃኒት፣ ገዥ የሚሉትን ቃላት እንመርምር፡፡

መድኃኒት የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ቦታ እጅግ ከፍ ያለ ነው፤ ዳዊት ስለዚህ ሲናገር «እግዚአብሔር አምባዬ አለቴ መድኃኒቴ ነው»/2ሳሙ22:2/ ብሏል፡፡ በኢሳይያስ እንደበትም እግዚአብሔር ለእስራኤል ሲናገር «እኔ የእስራኤል ቅዱስ አምላክህ እግዚአብሔር መድኃኒትህ ነኝ... እኔ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔ ሌላም የሚያድን የለም»/ኢሳ43:3፣11/ ብሏል፡፡ እንደዚሁም ነቢዩ በሌላ ቦታ ሰዎች እግዚአብሔርን «የእስራኤል አምላክ መድኃኒት ሆይ...» ብለው እንደሚጠሩት ይናገርና በዚያው ክፍል ደግሞ እግዚአብሔርም ስለራሱ በነቢዩ አንደበት «እናንተ ከአሕዛብ ወገን ሆናችሁ ያመለጣችሁ ተሰብሰባችሁ ኑ፤ በአንድነትም ቅረቡ የተቀረፀውን የምስላቸውን እንጨት የሚሸከሙና ያድን ዘንድ ወደማይችል አምላክ የሚጸልዩ እውቀት የላቸውም፡፡ ይናገሩ ይቅረቡም በአንድነትም

ይማከሩ ከጥንት ይህን ያሳየ ከቀድሞስ የተናገረ ማነው? ያሳየሁም የተናገርሁም እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን? ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም እኔ ጻድቅ አምላክና መድኃኒት ነኝ ይላል»/ኢሳ45:15፣ 20:21/:: በሌሎች ነቢያትም «ከእኔም በቀር ሌላ አምላክና መድኃኒት የለም»/ሆሴዕ14:4/ እያለ እግዚአብሔር ያውጅ ነበር:: መድኃኒትነት የእርሱ ብቻ ነበርና ምንም እንኳን በብሉይ ኪዳን ሰንበት፣ በዓለ ሰዊት፣ በዓለ መጸለት፣ በዓለ ፋሲካ፣ በዓለ ናእት/የቂጣ በዓል/፣ ኢዮቤልዩ የሚባሉ ታላላቅ በዓላት ቢኖሩም ከእነዚህ አንዳቸውም መድኃኒት አልተባሉም:: ከእርሱ ከእግዚአብሔር ሌላ መድኃኒት እንደሌለ የተገነዘቡ የዘመኑ ነቢያትም «አንሥእ ኃይለከ ወነዓ አድኅነነ ማለትም ኃይልህን አንሣ መጥተህም አድነን»/መዝ80:2/ ይሉ ነበር እንጂ ሰንበትን መድኃኒታችን ነሽ አላሏትም:: በአዲስ ኪዳንም ድንግል ማርያም ጌታን በፀነሰች ጊዜ «ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፤ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች የባርያይቱን ውርደት ተመልክቷልና»/ሉቃ1:47/ ብላለች:: ጊዜው ደርሶ ጌታ በተወለደ ሰዓትም መላእክት በሌሊት መንጋ ለሚጠብቁ እረኞች «ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና ብለው አበሰሩ»/ሉቃ2:11/:: መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመካከላቸው ሲመላለስ ሕይወት ሰጪ ትምህርቱን የሰሙት የሰማርያ ሰዎችም ስለእርሱ ሲናገሩ «እኛ ራሳችን ሰምተነዋልና እርሱም በእውነት ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት እንደሆነ እናውቃለን» ሲሉ ክርስቶስ መድኃኒት መሆኑን ተናግረዋል /ዮሐ4:32/:: በእርግጥም ጌታ እኛን ለማዳን በመስቀል ላይ ሞቶ ወደ ከርሠ መቃብር ወርዶ ሞትን ድል ማድረግ ነበረበትና እንደ መጻሕፍት ሐሳብ በኃጢአተኞች እጅ ተሰጥቶ ሞተ:: እንደ እግዚአብሔር አሠራርም ሞትን አሸንፎ ተነሣ:: ይህንን በዓይናቸው ያዩና የተገነዘቡ ሐዋርያትም ጌታ ካረገ በኋላ ስለእርሱ ለአይሁድ ሸንጎ ሲናገሩ «እናንተ በእንጨት ላይ ሰቅላችሁ የገደላችሁትን ኢየሱስን የአባቶቻችን አምላክ አስነሣው፤ ይህን እግዚአብሔር ለእስራኤል ንስሐን የኃጢአትንም ሥርየት ይሰጥ ዘንድ ራስም መድኃኒትም አድርጎ በቀኙ ከፍ ከፍ አደረገው» ሲሉ ራስና መድኃኒት ስለመሆኑ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል/ሐዋ5:31/:: ኢየሱስ ማለት አዳኝ መድኃኒት ማለት ነው፤ ዕለተ ሰንበት ማዳን ብትችል ኖሮ ወልደ እግዚአብሔር ሰው መሆን ባላስፈለገው ነበር:: የሐዲስ ኪዳን ምእመናን ለመዳን

እጆቻቸውን ወደማንም አያነሡም፤ መዳን በክርስቶስ ካልሆነ በቀር በሌላ በማንም የለምና/የሐዋ.ሥራ4:12/:: እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን የሚያስችለውን ከክርስቶስ ሌላ አማራጭ ቢፈልግ ኖሮ ከሰንበት ይልቅ ብዙ ታላላቅ ፍጥረታት ነበሩት፤ ሆኖም ግን ከፍጥረት ወገን ለማዳን የሚበቃ አልነበረምና ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻውን ለሰው ልጆች መድኃኒት ሆነ::

እንደዚሁም በዚህ መጽሐፍ ሰንበት «ለዘለዓለም ገዥ» ተብላለች፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ስንመለከት ግን ሰንበት ለሰው ተፈጠረች እንጂ ሰው ስለሰንበት አልተፈጠረም:: ሰዎችንም ልትገዛ ከቶ አትችልም፤ ለዘለዓለምም የመኖር ዕድልም የላትም፤ የእርሷ የጥላነት ጊዜ አብቅቶ አካሉ ክርስቶስ ተገልሟልና::

መድኃኒትነትም ሆነ ገዥነት ያለው እርሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ «ብቻውን የሆነ ገዢ» የሚለው እርሱን ብቻ ነው/1ጢሞ6:15/:: እንደዚሁም «እግዚአብሔርሰ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም፣ ወገብረ መድኃኒተ በማዕከለ ምድር ማለትም እግዚአብሔር ግን ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው በምድርም መካከል መድኃኒትን አደረገ»/መዝ74:12/ የተባለለት የዘለዓለም ንጉሥ አንድ ጌታ ነው እንጂ ሰንበት አይደለችም::

እንደዚሁም ይህችው ሰንበት «ለምኝልን» ተብላለች:: አንዲት የማትሰማና የጊዜ መለኪያ ብቻ የሆነችው ዕለት አፍ አውጥታ እንድትናገርና በእግዚአብሔር ፊት ቆማ እንድታማልድ ወደ እርሷ እጅን ዘርግቶ መማፀን ወደ ልቡ ተመልሶ ላስተዋለው ሰው ምን ያህል አሳፋሪ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም:: ቃሉ ግን እኛ ራሳችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እግዚአብሔርን እንድንለምነው ሲያስተምረን እንደዚህ ይለናል፤ «ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ»/ዮሐ14:13/፤ «የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል»/ዮሐ15:7/፤ «እውነት እውነት እላችኋለሁ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል እስከ አሁን በስሜ ምንም ለልለመናችሁም ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ»/ዮሐ16:23-24/::

በዚህም መሠረት ወደ ማን መለመን እንዳለብን ግልጥ ነው፤ በአጠቃላይ ጸሎታችንና ልመናችን በኢየሱስ በኩል ወደ አብ እንዲደርስ እንጂ በሌላ በኩል ማለትም በሰንበት ወደ አብ መግባት እንደማይችል ልንረዳ ይገባል:: ጌታም «በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» ማለቱ ለዚሁ አይደለምን/ዮሐ14:6/?

# ስለ ቊስቋም

## /ታሪካዊ ስለሚባሉ ቦታዎች/

«ቊስቋም ተዓቢ እምኪሩቤል፣ ቊስቋም ትከብር እምሱፌል፣ እስመ ኅብአቶ በወርኃ ቀትል፣ ለወልደማርያም ድንግል»

«ቊስቋም ከኪሩቤል ትበልጣለች፣ ከሱራፌልም ትከብራለች በጦርነት /በስደት/ ጊዜ የድንግል ማርያምን ልጅ ሸሽጋዋለችና»

/የቊስቋም ኩሉሙ ከሚባል ክፍል - ገጽ 114/

ጸሐፊው በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ቊስቋም የተባለችውን ቦታ ከኪሩቤልና ከሱራፌል እንደምትበልጥ አድርጎ አቅርቧል፡፡ «ቊስቋም» ማን ናት? ብለን ብንመረምር በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ፈጽሞ የማትታወቅ ቦታ ናት፡፡ አንዳንዶች ግን በግብፅ በረኃ የምትገኝ ምድረ በዳ ናት ይላሉ፡፡ የሚያስደንቀው ቊስቋም የምትባል አገር አለች ወይስ የለችም የሚለው ሳይሆን ይህች ቦታ «ከኪሩቤልና ከሱራፌል ትበልጣለች» መባሏ ነው፡፡ ቊስቋም ከኪሩቤልና ከሱራፌል ትበልጣለች ከተባለ ጌታችን ታላላቅ ሥራዎች የሠራባቸው የእስራኤል ቦታዎች ኢየሩሳሌም፣ ቤተልሔም፣ ዮርዳኖስና ደብረ ዘይት ምን ሊባሉ ነው?

ጌታ በሥጋ ተገልጦ ሳለ አንዳንድ ሥራ የሠራባቸውና በተለያየ ምክንያት የተመላለሰባቸው እነዚህ ምድራውያን መካናትን/ቦታዎችን/ ገና ለገና ጌታ በአንድ ወቅት ነበረባቸው ብሎ ከእነዚህ ልዑላን ፍጥረታት በላይ ማስቀመጥ ታላቅ ድፍረት አይደለምን? እንደ ደራሲው አባባል ከሆነማ ጌታ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ በአህያይቱ ግልገል ተጭኖ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቷልና ቊስቋም የተባለችው ቦታም ብቻ ሳትሆን ይህቺም አህያ ከነግልገሏ ከኪሩቤልና ከሱራፌል ትበልጣለች ማለት ይሆናል፤ ጌታን ተሸክመዋለችና፡፡

ወገኖች ሆይ እስቲ ረጋ ብለን እንመርምር፤ እውን ቊስቋም ከእነዚያ ክቡራን ፍጥረታት ትበልጣለችን? እስኪ ኪሩቤልንና ሱራፌልን በሰማይ ቊስቋምን በምድር እዩአቸው፤ ኪሩቤልና ሱራፌል ከእግዚአብሔር ዙፋን ጋር በተያያዘ መልኩ የሚታወቁ ሰማያውያን ፍጥረታት ናቸው/ዘፍ3፡24፣ መዝ99፡1፣ ኢሳ6፡1-6፣ ሕዝ10/፡፡ ስለሆነም እንኳንስ በመጽሐፍ ቅዱስ የማትታወቀው ቊስቋም ትቅርና ጌታ የተሰቀለባት ቀራንዮም ከእነዚህ ፍጥረታት ትበልጣለች ተብሎ አልተጻፈልንም፤

ምክንያቱም ድንቅ ታሪክ ሠሪውን ጌታን ትተን ድንቅ ሥራ የተሠራባቸውን ቦታዎች እናመልክ ዘንድ የተገባ አይደለምና:: ስለሆነም ቀኅስቋምን ከኪሩቤል የሚያስበልጡ ሰዎች ከሚገባው በላይ ስለ እግዚአብሔር ዙፋን የሚናገረውን እውቀት አጥተዋልና ሊማሩ ይገባቸዋል:: ቅዱሳትና ታሪካዊ ናቸው የሚባሉ አንዳንድ መካናትን/ቦታዎችን/ ከፍ ባለ ክብር የሚያቀርበው ይህ ትምህርት በተለይ በአገራችን የበርካታ ሰዎችን ዓይን ከእግዚአብሔር ላይ አንሥቶ ወደ ተራሮች፣ ዋሻዎችና ኮረብታዎች እንዲመለከት አድርጓል:: በልባቸው ወደ ቅዱሱ እግዚአብሔር በመመለስ ፈንታ የክርስትና ታሪክ አላቸው ወደሚባሉና በሰው ቅዱስ ተብለው ወደተሰየሙ ቦታዎች በመሄድ ከትቢያና ከድንጋይ በረከትና ጽድቅ የሚሹ ምንኛ ብዙዎች ናቸው! በእርግጥ ለዚህ ሁሉ ስሕተት የተጋለጡት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ባለመሄዳቸው ነው:: ቃሉን ቢሰሙ ለቃሉም ቢታዘዙ ተሳስተው ለማሳሳት ባልተገፋፉና ባልተሸቀዳደሙ ነበር፤ አሁንም ቢሆን ያለ ማወቃቸው ወራት አልፎ ለንስሐ ራሳቸውን ያዘጋጁ እንላለን/ሐዋ.ሥራ17:31/::

## ስለ ማርያም

1ኛ. «ንትፌሣሕ ኵልነ በዝክረ ስምኪ ጥዑም፣ ወደመ አስካልኪ መዓድም፣ ቅድስት ማርያም ቤዛዊተ ኵሉ ዓለም»

«የዓለም ሁሉ ቤዛ የሆንሽ ቅድስት ማርያም ሆይ ጣፋጭ በሆነው በስምሽ መታሰቢያ ያማረ በሆነ በደምሽ ፍሬም እንደሰታለን»::

/ኵሉሙ ዘእግዝእትነ ማርያም ከሚባለ ክፍል-ገጽ 105/

በዚህ ረዥም ዓረፍተ ነገር ውስጥ ደራሲው ማርያምን «የዓለም ሁሉ ቤዛ የሆንሽ» ብሏታል:: ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ የዓለም ሁሉ ቤዛ የሚለው ማንን ነው? ቤዛ ማለትስ ምን ማለት ነው? እነዚህንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ አሁንም ማየት ያለብን ከዚያው ከእግዚአብሔር መጽሐፍ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለቤዛ ምንነት የሚናገረው ከመጀመሪያዎቹ የሙሴ መጻሕፍት ጀምሮ ነው:: መቅሠፍት እንዳይሆንባቸው እያንዳንዱ እስራኤላዊ ስለነፍሱ ግማሽ ሰቅል ብር ቤዛ አድርጎ እንዲያቀርብ ታዞ ነበር/ዘጸ30:11-16/:: በእግዚአብሔር ፊት መቅረብ ለማይችል ንጹሕ ላልሆነ እንስሳም ቤዛ ይከፈል ነበር

/ዘሌዋ27:27/:: በእነዚህ ምንባባት መሠረትም ቤዛ ስለ ነፍስ የሚከፈል ዋጋ እንደሆነ እንረዳለን:: የተሸጠ ባሪያንም ነጻ ለማውጣት የሚከፈል ክፍያም ቤዛ ነው:: ከሁሉም በላይ የሰው ልጅ ራሱን ለኃጢአት የሸጠ በመሆኑ ነፍሱን ከበደል ባርነት አውጥቶ አርነትን የሚያጎናጽፈውን ቤዛ የሚጠባበቅ ፍጡር ሆኖ ለዘመናት ኖሯል:: በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጠው ሰው ኃጢአተኛ ብቻ ሳይሆን የኃጢአትም ባሪያ ነውና/ዮሐ8:34/:: የሰው ልጅ ቢፈልግ እንኳን ነጻነትን ለራሱ ሊያስገኝ የማይችል ጎስቋላ ሆኖ በኃጢአት ታስሮ ይኖራል:: ይህንንም አርነት ለሰው ልጆች ይሰጥ ዘንድ ከሰው ልጆች ለአንዳቸውም የሚቻለው ሆኖ ባለመገኘቱና ይህም ለፍጡር የማይቻል በመሆኑ የቆሬ ልጆች «ወንድም ወንድሙን አያድንም ሰውም አያድንም ቤዛውን ለእግዚአብሔር አይሰጥም» ሲሉ በተስፋ መቁረጥ ዘምረዋል /መዝ49:7/:: ይህንንም ችግር ያየ ጻድቅና ሁሉን ቻይ አምላክ የሰውን ዘር ለሞትና ለሲኦል ባርነት ሊተወው አልፈቀደም ነበርና በነቢዩ አንደበት «ከሲኦል እጅ እታደጋቸዋለሁ ከሞትም እቤዣቸዋለሁ ሞት ሆይ ቸነፈርህ ወዴት አለ? ሲኦል ሆይ ማጥፋትህ ወዴት አለ?» ሲል ተስፋውን ሰጠ/ሆሴ13:14/:: ስለሆነም እኛ ባሪያዎች ሆነን ሳለን «የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግ በታች የተወለደውን ልጁን ላከ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ ከሕግም በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ»/ገላ4:4-5/:: ወልድም ወደዚህ ዓለም መጥቶ ቅዱስና ጻድቅ ነፍሱን ስለብዙዎች አሳልፎ ይሰጥ ዘንድ ግድ ሆነ:: ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስም በማስተማር ዘመኑ «የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም» በማለት ሥጋን ለብሶ ወደዚህ ዓለም የመጣበት ዋናው ዓላማ ቤዛ ሊሆን እንደሆነ አስረድቷል/ማር10:45/:: በዚሁ መሠረትም እርሱም ሥጋን በመልበስ ራሱን ለሁሉ ቤዛ ሰጠ /1ጢሞ2:6/:: እኛም በስሙ በማመን በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን/ኤፌ1:7/:: ሐቁ ይህ ነው፤ ቤዛ የሚለው ቃል ትርጉምም ለሌላው አርነትን ለመስጠት ምትክ፣ ለውጥ፣ ፈንታ ሆኖ የሚሰጥ ማለት ከሆነ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በደል ሳይኖርበት አንዳች ኃጢአትም ሳይገኝበት ስለሌሎች ብሎ ነፍሱን በፈቃዱ አሳልፎ የሰጠ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ማን አለ? ማንም የለም:: ስለሆነም እውነትን ይከተሉ ዘንድ ልባቸውን ወደ እግዚአብሔር ቃል ያዘነበሉ ሁሉ እንደሚረዱት የዓለም ቤዛ ያለ ጥርጥር ኢየሱስ ብቻ ነው:: ለእያንዳንዱ ሰው ምትክና

ፈንታ ሆኖ በደሉን ተሸክሞለት በደለኛ ሊሞተው የተገባውን ሞት የሞተው እርሱ ብቻ ነው። በሰው ዘንድም ሆነ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ እንደሆነ የተመሰከረለት ጌታ እርሱ ብቻ ነው። ከዚህም የተነሣ ቤዛ ሊሆን በቅቷል። በእርግጥ ሌሎች ሰዎች ቤዛ መሆን ቢችሉ የእግዚአብሔር ልጅ በመስቀል ላይ መሞት ባላስፈለገውም ነበር። ስለዚህ ማናቸውም ሰው ይህን በክርስቶስ የተከናወነውን ቤዛነት ከማናቸውም ፍጡር ሊያገኝ አይችልም፤ እንደዚሁም «ብኪ ድኅነ ዓለም ማለትም ባንቺ ዓለም ዳነ/በአሥመራው እትም ገጽ409/»፣ «ብኪ ንድኅን ወነገዩ ማለትም ባንቺ እንድናለን እንኖርማለን»፣ «እግዝእትነ ወመድኃኒትነ ማለትም እመቤታችንና መድኃኒታችን» የሚሉ ሌሎች እውነትን የሚቃወሙ ቃላቶች ሁሉ የሚገለገሉባቸውን ሰዎች አማናዊውን ቤዛ እንዳያዩ ስለሚጋርዷቸው ወደ ብርሃን ሊወጡ አልቻሉም፤ ስለሆነም እነዚህ ሰዎች ከምን ጊዜውም ይልቅ ይህንን አስተውለው ሊነቁና ከሐሰትም ሊለዩ ያስፈልጋቸዋል።

በብሉይ ኪዳን ዘመን እያንዳንዱ ሰው ሲበድል እንደበደሉ ዓይነት ነውር የሌለበት ጠቦት ወደ ካህኑ ወስዶ በደለኛው ግለሰብ በጠቦቱ ላይ እጁን እንዲጭንበት ካህኑ ያዝዘዋል። ከዚህ በኋላ ያ ነውር የሌለበት ጠቦት በበደለኛው ፈንታ ይሞት ነበር፤ ያም በደለኛ ንጹሕ ነህ ተብሎ ወደ ቤቱ ይመለሳል። እንዲሁም እኛ ሁላችን ነውር ያለብንና በደለኞች ሆነን ሳለን የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግደው ነውር የሌለበት የእግዚአብሔር በግ ኢየሱስ ክርስቶስ በደላችንን ሊሸከም የሚችል ሆኖ ተገለጠ፤ «እኛም በደሙ የሚሆን ቤዛነታችንን አገኘን»። ይህም የዘለዓለም ደኅንነት ነው፤ በዚህም ምክንያት ሁላችን ጻድቃን ተባልን። ደሙ ከኃጢአት ሁሉ አንጽቶናልና «ወደሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያነጽሐነ እምኵሉ ኃጣውኢነ» እንዳለ ዮሐንስ ወንጌላዊ/1ዮሐ1፡7/።

በመሆኑም የዓለም መድኃኒት የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛ የዓለም ቤዛ እንደሆነና ከእርሱም ሌላ ማንም ቤዛ ሊሆን እንደማይችል መጻሕፍት እየነገሩን ድንግል ማርያምን «ቤዛዊተ ዓለም» ናት ማለት የወልደ እግዚአብሔርን ደም ከንቱ ማድረግ ይሆናል። ስለሆነም የመጽሐፈ ሰዓታት ተጠቃሚዎች ይህንን አውቀው ከዚህ የኑፋቄ ሐሳብ ሊላቀቁ ይገባል።

ከዚህም በተጨማሪ ጸሐፊው ድንግል ማርያምን «በስምሽ እንደሰታለን» በማለት ጽፏል። ይሁን እንጂ ከመሠረቱ ይህ ደስታ በሐሰት ላይ የተመሠረተ ከመሆኑም ሌላ የድንግል

ማርያም ስም የሰው ልጆች የደስታ ምንጭ አለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል:: ስለዚህም ጉዳይ ቢሆን የደስታችን መገኛ ማን እንደሆነ እግዚአብሔር በቃሉ ሳይነግረን አልተወንም:: በብሉይ ኪዳን ይኖሩ የነበሩ ሰዎችም እንኳን ይህን ጠንቅቀው ያውቁ ነበር:: ሐና ስትጸልይ «ልቤ በእግዚአብሔር ጸና ...በማዳንህ ደስ ብሎኛል» በማለቷ የደስታዋ ምንጭ የእስራኤል ቅዱስ መሆኑን መስክራለች/1ሳሙ·2:1/፤ ዳዊትም «ልቤም በመድኃኒትህ ደስ ይለዋል» በማለት ተናግሯል /መዝ13:5/:: እንደዚሁም «ጻድቃን ሆይ በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ ሐሤትም አድርጉ ልባችሁም የቀና ሁላችሁ እልል በሉ» ሲል ለሌሎችም አስገንዝቧል /መዝ32:11/:: ከዚህም ሌላ የእግዚአብሔር ቃልና ትእዛዛቱ ለቅዱሳን የልብ ደስታ መገኛዎች ነበሩ፤ ስለዚህም ዘማሪው «ብዙ ምርኮ እንዳገኘ በቃልህ ደስ አለኝ» ብሏል/መዝ119:162/:: ይሁን እንጂ ይህ በተነገረበት ዘመን ሁሉ የሰዎች ደስታ ፍጹም አልነበረም፤ ይህም ደስታቸው ፍጹም ይሆን ዘንድ ሕያው የእግዚአብሔር ቃል ሥጋን ለብሶ ወደ ሰዎች መጣ:: እናቱ ማርያምም «ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፤ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሤት ታደርጋለች» ስትል በእርሱ ያገኘችውን እውነተኛ ደስታ በምስጋና አበሰረች/ሉቃ1:47/:: ጌታም «ደስታችሁ ፍጹም ይሆን ዘንድ ይህን ነግሬአችኋለሁ» እያለ ለሐዋርያት አስተማረ/ዮሐ15:11/፤ እንደዚሁም «ስማችሁ በሰማያት ስለተጻፈ ደስ ይበላችሁ» ብሏቸዋል/ሉቃ10:20/:: ጳውሎስም በመልእክቱ «ሁል ጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ፤ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ» በማለት የደስታችን ምንጭ ጌታ እንደሆነ ይነግረናል/ፊልጵ4:4/:: እንግዲህ በዚህ ሁሉ በአንዱም ቦታ መጻሕፍት «በፍጡራን ደስ ይበላችሁ» ሲሉ አይታይምና በአማናዊው የደስታ ምንጭ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ደስ መሰኘትን ትተው «ጣፋጭ በሆነ በስምሽ አጠራር እንደሰታለን» የሚሉ ወገኖች በጌታ ወደሚገኘው ደስታ እንዲመለሱ ይጋበዛሉ::

2ኛ. «ኪሩቤል አፍራስ ፈማ፣ ወሱራፌል ዘራማ፣ ክሱላነ ሞገስ ወግርማ፣ ይሴብሑኪ ማርያም በሐዋዝ ዜማ»

«ግርማንና ሞገስን የተቀዳጁ የፌማ ፈረሶች ኪሩቤልና ራማዊው ሱራፌልም ባማረ ዜማ ማርያም ሆይ አንቺን ያመሰግኑሻል»

/ኵሉሙ ዘኪዳነ ምሕረት - ገጽ-109/

በዚህ ክፍል ደግሞ ደራሲው ኪሩቤልና ሱራፌል ባማረ ዜማ ማርያምን እንደሚያመሰግኑ ይናገራል:: በእርግጥ እነዚህ ቅዱሳን

ፍጥረታት ተጨማሪ አድርገው ወይም እግዚአብሔርን ትተው የሚያመሰግኑት ሌላ ተመስጋኝ ፍጡር እንደተመደበላቸው የሚያሳይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ የለንም። ደግሞም በሰማይ ፍጡር አይመሰገንም፤ ወደዚያች ከተማ የገባ ሁሉ የከተማዋን ባለቤት ያመሰግናል፤ እኔ ልመስገን የሚል ፍጡርም የለም።

ድንግል ማርያምም በሰማይ ከአእላፋት መላእክትና ከቅዱሳን ጋር ሆና ስለተደረገላት ነገር ፈጣሪዋን ታመሰግናለች። ከዚህ ውጪ ግን በዚያ በሰማይ ከኪሩቤልና ከሱራፌል ውዳሴን ትቀበላለች ብሎ ማሰብ በምድር እንኳን የተወገዘውን ፍጡራንን ማምለክ ወደ ሰማይ ለማውጣትና በሰማይም ተቀባይነት ያለው ለማስመሰል የተደረገ ጥረት እንደሆነ አስተዋዮች አያጡትም። የሰማይ አምልኮ በተገለጠበት በራእይ መጽሐፍም ቅዱሳን መላእክት በአንዱም አጋጣሚ ፍጡራንን ሲያመልኩ አለመታየታቸው ትምህርት ሊሆነን ይገባል።

የጌታችንን የኢየሱስን እናት የሕይወት ታሪክ በሚገባ የሚያውቁ ሐዋርያት እንኳ ምንም የጌታቸው እናት ብትሆንም እርሷ ምስጋናን ልትቀበል እንደሚገባት ለማመልከት አንድ ምዕራፍ ወይም አንድ አንቀጽ እንኳን ለመጻፍ አላሰቡም። «እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል»/ሉቃ1:49/ ብላ ራሷ ድንግል ማርያም የተናገረችው ቃልም ቢሆን እንደ ኤልሳቤጥ «ከጌታ የተነገረላት ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት»/ሉቃ1:45/ ብሎ ስለጌታ እናት በሦስተኛ መደብ ምስክርነት መስጠት ማለት ነው እንጂ እርሷ ከሞተች በኋላ በጸሎትና በውዳሴ በሁለተኛ መደብ «ማርያም ሆይ ብፅዕት ነሽ» ማለትን የሚያመለክት አይደለም። ሐዋርያትም ለእርሷ የሚሆን ውዳሴ አላቀረቡም፤ ይህንም አለማድረጋቸው በንቀት ሳይሆን ማድረግ የሚገባቸውን በውስጣቸው የሚኖር መንፈስ ቅዱስ ስለሚያሳያቸው ነው። በሰማይ ያሉ መላእክትም ባመሰገኑ ጊዜ ሁሉ እርሷን አለመጨመራቸው ይህን ማድረግ ስህተት ስለሆነ ነው። በመሆኑም የሰማይ ቅዱሳን ፍጥረታት የሚያመሰግኑትንንና ምስጋና የሚገባውን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ሲያመሰግኑ እንዲህ ይላሉ፤ «መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል ታርደሃልና በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ፣ ከቋንቋም ሁሉ፣ ከወገንም ሁሉ፣ ከሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው በምድርም ላይ ይነግሣሉ»/ራእ5:9-11/። በዚህ ክፍል ላይ ሲመሰገን የምናየው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እንጂ ማርያም

አይደለችም። በተጨማሪም እስቲ የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከታቸው/ራእ4:8፣ 7:9፣ 11:15፣ 12:10፣ 15:3፣ 19:1/። በእነዚህም ጥቅሶች ሁሉ ከጌታ በቀር ማንም አልተመሰገነም። በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው የጌታ ሰዎች የጻፉት ቅዱስ መጽሐፍ በሰማይ የሚመሰገነውን በዚህ ዓይነት አስቀምጦልናል። ስለሆነም ያላየነውንና ያልሰማነውን በመጽሐፍ ቅዱስም የሌለውን በሚያስተምሩ ሰዎች ላይ በእውነትና በመንፈስ የሚመለከው አምላክ ይፈርድባቸዋል። ከቅዱስ መጽሐፍ ሐሳብና እውነታ በተለየ መንገድ «በሰማይ ማርያም ትመሰገናለች፤ እነ ሱራፌል ያመሰግኗታል» ማለቱ ራስን ሐሰተኛ ምስክር ማድረግ ነው። ይህም በእግዚአብሔር ፊት ተጠያቂ ያደርጋል። ምክንያቱም በእውነተኛው ቅዱስ መጽሐፍ ባለመመዝገቡና እውነት ባለመሆኑ ነው። ስለሆነም ኪሩቤልና ሱራፌል እንዲህ ያለውን ስህተት ይፈጽማሉ ብሎ መመስከሩ የሐሰት ምስክር ያሰኛል እንጂ ማርያምንም ሆነ ኪሩቤልን ደስ ማሰኘት እንዳልሆነ መገንዘብ ይገባል። ዮሐንስ በራእይ ያን ሁሉ ምስጋና ሲያይ አንዴ እንኳ ማርያም ስትመሰገን አልሰማም። በመሆኑም ኪሩቤልና ሱራፌል «የታረደውን በግ» ብቻ እንደሚያመሰግኑ መመስከሩ በቂ ነውና እንዲህ የሚያደርጉትን «ከተጻፈው አትለፍ»/1ቆሮ4:6/ የሚለውን የተቀደሰ መመሪያ ተማሩ እንላቸዋለን።

3ኛ. «ሰአሊ ለነ ማርያም፣ ምዕዳው እምሠርም፣ ዘጽድቅ ተንከተም»

«ከረግረግ መሸጋገሪያ፣ የጽድቅ መሰላል የሆንሽ ማርያም ሆይ ለምኚልን»

/ሰዓሊ ለነ ከሚባል ክፍል ገጽ131/

በዚህ ክፍል ደግሞ ጸሐፊው ማርያምን «ከረግረግ መሸጋገሪያ/ድልድይ/» እንደዚሁም «የጽድቅ መሰላል» ብሏታል። እዚህ ላይ ምንም እንኳን በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሶ ባይገኝም «ረግረጉ» በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ለተፈጠረው የግንኙነት መቋረጥ ከተመሰለ «ድልድዩ» ደግሞ ይህንን ግንኙነት ዳግመኛ እንዲመሠረት ለሚያደርገው አካል ምሳሌና መጠሪያ ቅጽል ሆኖ ሊቀርብ ስለሚችል ምሳሌው በራሱ ችግር የለውም። ሆኖም በዚህ ረገድ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ለተፈጠረው ትልቅ ጠብና እኛንና እግዚአብሔርን ለለያየው ታላቅ የበደል ገደል ድልድይ ሆኖ ሰውን ዳግመኛ ከእግዚአብሔር ጋር ማገናኘት የሚቻለው ማነው? ጌታ ኢየሱስ

ወይስ የጌታ እናት? በትክክል ለመናገር በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ምንም እንኳን በየጊዜው የሚነሡ የእግዚአብሔር ሰዎች ቢኖሩም ከፍጡር ወገን ይህን ታላቅ ገደል የሚያሻግር ድልድይ አልተገኘም:: ስለዚህም ወልደ እግዚአብሔር ወደዚህ ዓለም መጣ፤ «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም» ሲል እርሱ ሬግረጉን የሚያሸጋግረን የሕይወት መንገድ መሆኑን አረጋገጠልን/ዮሐ14:6/::

«መሰላል» ደግሞ ከፍ ወዳለው ስፍራ መወጣጫ በመሆን ያገለግላል:: በዘፍጥረት 28 ቁጥር 12 ላይ ያዕቆብ ተኝቶ ሳለ መሰላል በምድር ላይ ተተክሎ ራሱም ወደ ሰማይ ደርሶ የእግዚአብሔር መላእክት ሲወጡበት ሲወርዱበት በሕልም እንዳየ እናነባለን:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ በማስተማር ዘመኑ መጀመሪያ ላይ «እውነት እውነት እላችኋለሁ ሰማይ ሲከፈት የእግዚአብሔርም መላእክት «በሰው ልጅ» ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ» ብሎ ተናግሯል /ዮሐ1:52/፤ በዚህ ንግግር ውስጥም «የሰው ልጅ» የተባለው ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነና እርሱም ለእኛ በምድር ላለነው ወደ ሰማይ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን የምንደርስበት፣ የእግዚአብሔርም ጸጋ ወደ እኛ የሚመጣበት አማናዊ የጽድቅ መሰላል እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነቡ ሁሉ በግልጥ ይገነዘቡታል:: ታዲያ እንዲህ ግልጥ ብሎ የተቀመጠውን እውነት ወደ ጎን ትቶ «ማርያም ሆይ ድልድይና መሰላል አንቺ ነሽ» ማለት በእግዚአብሔር ላይ መዘበት አይደለምን? መታረምስ አያስፈልገውምን? በሌላ በኩል ደግሞ ድልድይ፣ መሰላል የሚለው ምሳሌ ለማርያም ከተሰጣት ጌታን ከመውለዷ አስቀድሞም በእርሷ ድልድይነትና መሰላልነት ወደ አብ መድረስ ይቻል ነበር ያስብላል፤ ይህ ከሆነ ደግሞ የኢየሱስ ሰው መሆን ትርጉም የለሽ ይሆናል::

ሁለቱንም ማለትም ጌታንም ማርያምንም ድልድይና መሰላል ማድረግ ደግሞ አይቻልም፤ ምክንያቱም «በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ እርሱም ሰው የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» ተብሎ ተጽፏልና/1ጢሞ2:5/:: ስለሆነም እግዚአብሔር ያቆመውን መሰላልና ድልድይ ትተው በራሳቸው ሐሳብ ሌላ መሰላልና ድልድይ ያቆሙ ቢኖሩ ለሚደርስባቸው ጥፋት ተጠያቂዎች ናቸው:: ይሁን እንጂ ወደ እውነተኛው መሰላል ቢመለሱ ያለጥርጥር ወደ እግዚአብሔር ሊደርሱ ይችላሉ::

4ኛ. «ሰአሊ ለነ ማርያም አክሊለ ንጹሐን፣ ብርሃነ ቅዱሳን»

«የንጹሐን አክሊል፣ የቅዱሳን ብርሃን ማርያም ለምኚልን»

/ሰዓሊ ለነ ከሚባል ክፍል ገጽ-131/

እዚህ ላይም ጸሐፊው ማርያምን «የንጹሐን አክሊል» «የቅዱሳን ብርሃን» ብሏታል። አክሊልን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ ክብር ይሆንላቸው ዘንድ የአክሊል ሽልማትን እንዳዘጋጀላቸው በተደጋጋሚ ተጽፏል። ይህም የሆነው ከዘመናት በፊት በክብር የነበረው የእግዚአብሔር ልጅ እኛን ያከብረን ዘንድ በኃጢአተኞችና በዘባቾች እጅ የእሾህ አክሊል በራሱ ላይ በመደፋቱ ነው /ማቴ27:29/። ይህም አክሊል እግዚአብሔር በልጁ ደም ለተዋጁት ስለ አገልግሎታቸው የሚሰጣቸው ሽልማት ነው። ስለዚህም ጳውሎስ የማይጠፋውን አክሊል ለማግኘት እንድንሮጥ አሳስቦናል/1ቆሮ9:24-25/። ዳግመኛም ጳውሎስ «የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል» ብሏል/2ጢሞ4:8/። ጴጥሮስ ደግሞ «የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ» በማለት ይናገራል/1ጴጥ5:4/። ያዕቆብም ያንኑ የሽልማት አክሊል «የሕይወት አክሊል» ብሎ ጠርቶታል /ያዕ1:12/። እነዚህ ሁሉ በተለያየ መጠሪያ ይጠሩ እንጂ ሁሉም እግዚአብሔር ወደ ፊት ከራሱ ጋር ሊያከብራቸው በቃሉ ለጠራቸው ስላዘጋጀው ክብር የሚናገሩ ናቸው። በዚህ ሁሉ ግን አንድ ጊዜም ማርያም ለቅዱሳን የክብር አክሊል ሆና ተሰጥታለች የሚል አናነብም። «እነሆኝ የጌታ ባሪያ»/ሉቃ1:38/ ብላ እምና ተገኝታለችና ከሌሎች ቅዱሳን ጋር የክብርን አክሊል እንደምትቀበል እንጂ እርሷ አክሊል ሆና ለሌሎች እንደምትሰጥ መጽሐፍ ቅዱስ አያሳየንም፤ አይነግረንምም። ጌታም እስከ ሞት ለታመኑት «የሕይወትን አክሊል እሰጣቸዋለሁ»/ራእ2:10/ አለ እንጂ «እናቴን አክሊል አድርጌ እሰጣችኋለሁ» አላለም። ከላይ የተጠቀሱትን ጥቅሶች ብናነብ የአክሊሉ ሰጪ ባለቤትም ጌታ ራሱ እንጂ ሌላ አይደለም።

አሁን ደግሞ ደራሲው «ብርሃነ ቅዱሳን» በማለት ማርያምን የሚያወድስበትን ቃል እንመልከት። በብሉይ ኪዳን ነቢዩ ስለ ምድራዊቷ ጽዮን ሲናገር «ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር የዘለዓለም ብርሃንሽ አምላክሽም ክብርሽም ይሆናልና ፀሐይ በቀን ብርሃን አይሆንልሽም የጨረቃም ብርሃን በሌሊት አያበራልሽም እግዚአብሔር የዘላለም ብርሃንሽ ይሆናልና... ሕዝብሽም ሁሉ

ጻድቃን ይሆናሉ»/ኢሳ60፡19-21/ ብሎ ነበር። ይህም ትንቢት በአዲስ ኪዳን ከሰማይ በምትወርደው ቅድስቲቱ ከተማ ፍጻሜ እንደሚያገኝ መገንዘብ እንችላለን። በዮሐንስ ራእይ መጽሐፍ ውስጥ በጉ ራሱ ለከተማዋና በውስጧ ለሚኖሩ ቅዱሳን መብራቷ እንደሆነ በግልጥ የተጻፈልን በመሆኑ የቅዱሳን ብርሃን ራሱ ጌታ እንደሆነ ለማወቅ ይቻላል/ራእ21፡13/። ይህም የሚያሳየው ለሁሉም የሚያበራው የብርሃናት ፈጣሪ እርሱ ጌታ ራሱ መሆኑን ነው። በሰማይ አንዱ ለአንዱ አያበራም፤ አንዱም ለአንዱ አክሊልን አይሰጠውም፤ አንዱም ለሌላው አክሊል አይሆነውም፤ ሁሉም ግን በእግዚአብሔር ጸጋ ከእርሱ በሚቀበሉት አክሊል ከብረው ይኖራሉ፤ በእርሱም ብርሃን ይመላለሳሉ።

እርሱ ጌታ ለሁላችንም አክሊላችን፣ ብርሃናችን፣ ንጽሕናችን፣ ቅድስናችን፣ ሞገሳችን በአጠቃላይ ሁለንተናዊ ክብራችን ነው። የሰው ሐሳብ ያልተጨመረበት የእግዚአብሔርን የዘላለም ምክር ብቻ የያዘው እውነተኛ ቅዱስ መጽሐፍ እርሱ ብቻውን ብርሃናችንና ክብራችን እንደሆነ ያረጋግጥልናል።

5ኛ. «ጸሎታ ለማርያም ወስእለታ ያድኅነነ እመዓተ ወልዳ»

«የማርያም ጸሎትና ልመና ከልጇ ቍጣ ያድነን»

/የውዳሴ ማርያም መርገፍ፣ ማሳረጊያ «ወትቤ ማርያም» ከመባሉ በፊት ውዳሴማርያም ከተደገመ በኋላ የሚባል ነው፤ ገጽ-132፣ ወይም በአሥመራው እትም ገጽ 399/

ይህ ልመና ለማናቸውም ምስጋና እንደ መደምደሚያ ሆኖ ያገለግላል፤ በቅዳሴና በማኅሌት በዜማም ሆነ በቃልና በመጽሐፍ ለሚደገሙ እንዲሁም በግልና በኅብረት ለሚከናወኑ ሥርዓቶች ሁሉ ማሳረጊያ ነው። ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ቃል ስንመለከተው እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣ ያደረገውን የማዳን ሥራና የከፈለውን መሥዋዕትነት የሚቃወም ልመና ነው። መጻሕፍትን ስናጠና እንደ እግዚአብሔር ያለ ቸርና ርኅሩኅ ከሰውም ሆነ ከመላእክት አንድ ስንኳ የማይገኝ መሆኑን እንረዳለን። ለምሳሌ ስለእግዚአብሔር ምሕረት ከሚናገሩት ጥቅሶች ጥቂቶቹን ቀጥሎ እንመለከታለን። ወደ ኤፌሶን በተላከው መልእክት ውስጥ «ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳን በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወትን ሰጠን፤ በጸጋ ድናችኋልና»/ኤፌ2፡4/ ተብሎ ስለእግዚአብሔር መሐሪነት ተገልጧል። ጴጥሮስም እንደዚሁ «እንደ ምሕረቱ ብዛት ሁለተኛ የወለደን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ

ይባረክ»/1ጴጥ1:3-5/ በማለት እግዚአብሔር በምሕረቱ ያደረገልንን ጽፏል:: በመዝሙር መጽሐፍም እንደዚሁ «እግዚአብሔር መሐሪና ይቅር ባይ ነው፤ ከቍጣ የራቀ ምሕረቱም የበዛ፤ ... ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል እንዲሁ እግዚአብሔር ምሕረቱን በሚፈሩት ላይ አጠነከረ፤ ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ እንዲሁ ኃጢአታችንን ከእኛ አራቀ:: አባት ለልጁ እንደሚራራ እንዲሁ እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራል»/መዝ103:8-13/ የሚል ይገኛል፤ በተጨማሪም «እግዚአብሔርን አመስግኑ ቸር ነውና ምሕረቱም ለዘለዓለም ነውና»/መዝ136:26/ የሚል ከዚሁ የመዝሙር መጽሐፍ እናነባለን:: ኤርምያስም «ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ነው፤ ርኅራኄው አያልቅምና»/ሰቆ3:22/ ብሏል፤ እንደዚሁም «ጌታ ለዘለዓለም አይጥልምና ቢያሳዝንም እንደ ምሕረቱ ብዛት ይራራልና የሰውን ልጆች ከልቡ አያስጨንቅም አያሳዝንምም»/ሰቆ3:31-33/ በማለት የእግዚአብሔርን ምሕረት ያብራራል:: በአዲስ ኪዳንም የእግዚአብሔር ልጅ ለምሕረት እንደመጣ ሲናገር «ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና»/ዮሐ3:17/ ይላል:: የጌታ እናት ማርያምም ራሷ «ምሕረቱም ለሚፈሩት እስከ ትውልድና ትውልድ ይኖራል»/ሉ1:50/ አለች እንጂ ልጄ ቍጡ ስለሆነ የምትድኑት በእኔ ርኅራኄ ነው አላለችም:: ጌታም ራሱ ሲናገር «...ወይስ ከእናንተ ልጁ እንጀራ ቢለምነው ድንጋይን የሚሰጠው ከእናንተ ማን ሰው ነው? ዓሣስ ቢለምነው እባብን ይሰጠዋልን? እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠትን ካወቃችሁ በሰማያት ያለው አባታችሁ ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መልካም ነገርን ይሰጣቸው?» ብሏል/ማቴ7:9-11/::

በዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር ርኅራኄ ከሰው ርኅራኄ እንደሚበልጥ የእግዚአብሔር ቃል እየተናገረ በአንጻሩ ደግሞ ስለሰው ልጅ ክፋት የሚናገረውን እንመልከት:: ራሱ እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል፤ «የሰው ልብ ከታናሽነቱ ጀምሮ ክፉ ነውና»/ዘፍ8:21/:: ከሰው መካከል እንደ እግዚአብሔር የሚሆን መሐሪ እንደሌለ ሲናገርም «.. ..ቸርነትን የሚያደርግ የለም አንድ ስንኳ የለም»/ሮሜ3:12/ ይላል::

ታዲያ የሰው ትክክለኛ ማንነት እንዲህ እየተገለጠ ሰውን ከእግዚአብሔር የተሻለ ርኅሩኅ አድርጎ ማስቀመጡ ስህተት አይደለምን? ጌታም በዚህ ምድር ሲያስተምር ሳለ የሰማርያ

ሰዎች እንዳልተቀበሉት ባዩ ጊዜ ያዕቆብና ዮሐንስ እሳት ከሰማይ ወርዶ የሰማርያ ሰዎችን እንድትበላቸው መጠየቃቸውንና ጌታም «ምን ዓይነት መንፈስ እንደሆነላችሁ አታውቁም የሰው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም»/ሉቃ9:51-56/ ብሎ እንደመለሰላቸው የሚናገረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ያነበበ ሁሉ የሰውን ክፋት የጌታን ምሕረት ይረዳል። በዚህ ብቻ ሳያበቃ በሰማያት ያሉ ነፍሳት እንኳን ሳይቀሩ በታላቅ ድምፅም እየጮኹ «ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከመቼ አትበቀልም»/ራእ6:10/ የሚሉ መሆናቸውን ሲሰሙ ከጌታ ይልቅ በሰው ምሕረት የሚታመኑ ምንኛ ይደነግጡ ይሆን! ስለሆነም ይህንን የሰማይ ራእይ ያነበበ ሁሉ ዓይኖቹን ከሰው አንስቶ ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ ዞር ለማድረግ አይዘገይም። የጌታ እናት ምንም ርኅርኅት ብትሆን ከጌታ ይልቅ ለሰው ትራራለች ማለት አይቻልም። የጌታን እናት ቸርና ርኅርኅት፣ ጌታን ደግሞ መዓተኛና ምሕረት የሌለው አድርጎ በማሰብ የእርሷ ጸሎት ከልጇ መዓት የሚያድን እየመሰላቸው «ጸሎታ ለማርያም ያድኅነነ እመዓተ ወልዳ ማለትም የማርያም ጸሎት ከልጇ ቊጣ ያድነን» እያሉ ጸሎትን ሁሉ መቋጨት የእግዚአብሔርን የምሕረቱን ባለጠግነት አለመረዳት ነው። ከዚህም ሌላ «እግዚአብሔር ለቊጣ አልመረጠንምና ነገር ግን በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ነው እንጂ» ተብሎ ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረን ነው/1ተሰ5:9/። ይህ ደግሞ በራሱ እግዚአብሔርን የሚያሳዝነው ስለሆነ መታረሙ አስፈላጊ ነው።

6ኛ. «ሰላም ለሥዕልኪ ወለሥዕለ ወልድኪ ዘሰዓሞ፣ ዮሐንስ ርኁ ዮሐንስ ቀናንሞ፣ ... ማርያም ሀብኒ በእዴኪ እንዘ ትጼውኢ ስሞ፣ ሥጋሁ ቅዱሰ ወክቡረ ደሞ»

«በመዓዛው ርኁና ቀናንሞ የሆነ ዮሐንስ ለሳመው ሥዕልሽና ለልጅሽ ሥዕል ሰላም እላለሁ...ማርያም ሆይ ስሙን እየጠራሽ ሥጋውንና ደሙን በእጅሽ ስጭኝ»

/መልክአ ሥዕል ከሚባል ክፍል ገጽ-232/

በዚህ ንባብ ደራሲው ለሥዕል ሰላምታ ያቀርባል። ስለ ሥዕሉ ምንነት ለይቶ ሲያስረዳ ዮሐንስ የሳመው ሥዕልሽ በማለት ገልጿል። በእርግጥ ይህ የተባለው ሥዕልስ ነበረን? ዮሐንስስ ይህን የተባለውን ሥዕል ስሟልን? የእነዚህን ጥያቄዎች

መልስ ለአንባቢው እንተወውና የሥዕልን ምንነት እናጥና:: ሥዕል ወርድ፣ ቁመትና ስፋት ያለው አካል በቀለም በዝርግ ሰሌዳ ወይም ግድግዳ ላይ በቀለም ተሥሎ ለተመልካች የሚቀርብ የአንድ አካል ምስል ነው:: ስለዚህም ውክልናው ሙሉ በሙሉ ለአካሉ ሲሆን አካሉን የመምሰሉ ደረጃም በሠዓሊ ችሎታ ላይ የተሞረከዘ ነው:: ሥዕሉ ከአካሉ ጋር ያለው ዝምድና አካሉን መምሰሉ ብቻ እንጂ አካሉን ወክሎ መናገርም ሆነ መስማት ወይንም ከአካሉ ጋር ሐሳብ መለዋወጥ አለመሆኑን ሰው ሁሉ ያውቀዋል:: ሥዕሉን ለማናገር መሞከርም አካሉን ከማናገር ጋር ምንም ግንኙነት የለውም:: ሥዕሉን መሳምም አካሉን ከመሳም በእጅጉ የራቀ ነው:: አካሉም በመንፈስ በሥዕሉ ላይ ተገልጦ አይሰማም፤ አያይምም፤ አይሳምም:: ሥዕልን መሳምስ አግባብነት አለውን? አሕዛብ የአማልክቶቻቸውን ምስል ቀልጦ ከተሠራ ብረት ነክ ማዕድን ወይም ከእንጨትና ከድንጋይ ጠርበው ይሠሩ እንደነበር በታሪክም በመጽሐፍ ቅዱስም ይታወቃል:: ሕዝበ እስራኤል ግን አምላካቸውን በሚታዩ ነገሮች መስለው ለማምለክ ከመጣር እንዲቆጠቡ ለማስቻል እንደዚህ የሚል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው ነበር፤ «እግዚአብሔር በኮሬብ በእሳት ውስጥ ሆኖ በተናገራችሁ ጊዜ መልክ ከቶ አላያችሁምና እጅግ ተጠንቀቁ እንዳትረክሱ፤ የተቀረፀውን ምስል የማናቸውንም ምሳሌ በወንድ ወይም በሴት መልክ የተሠራውን በምድር ላይ ያለውን የእንስሳን ሁሉ ምሳሌ ...እንዳታደርጉ»/ዘዳ4:15-19/:: በዚህ ንባብ መሠረት የራሱ የእግዚአብሔርንም ምስል ሆነ ከሰው ወገን የወንድ ወይም የሴት ምስል አድርጎ ለአምልኮ መጠቀም ታላቅ ስህተት መሆኑ እርግጥ ነው:: ሰው የማይናገሩ ጣዖታትን ደስ እንዳሰኘው አድርጎ በሥዕልም ይሁን በቅርጻ ቅርጽ በኩል ሊያመልክ ይችላል፤ ሆኖም ግን በዚህ መንገድ ሰው እግዚአብሔርን ላምልክ ቢል እግዚአብሔር የዚህ ዓይነቱን አምልኮ የሚቀበል አምላክ አይደለም፤ በምትኩም ስለአምልኮው መለኮታዊ ሥርዓትንና መንገድን የሚያውጅ፣ ከቃሉም ውጪ የሚያመልከውን የሚቀጣ አምላክ ነው እንጂ::

ማንበብና መጻፍ የማይችሉት ሰዎችን ታሪክ ለማስተማሪያ ከመጠቀም ውጭ ሥዕልን ለአምልኮ ቢያውሉት ስህተት መሆኑ ግልጥ ነው:: እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ የሰው እጅ ውኃን ከቀለም አዋሕዶ በብዕር አማካኝነት ከሰሌዳ ላይ ላሳረፈችው ምስል መስገድ፣ ያንን ምስል መሳም የእስራኤልን ቅዱስ ለሚያመልኩ ምንኛ አጸያፊ ተግባር ነው! እየተሰገደለት

እንደሆነ ለማያውቅ ለሰው እጅ ሥራ መስገድ፣ ለማያሸት ሥዕል እጣን ማጠን፣ እየተሳመ መሆኑን የማያውቅን ሥዕል አጎንብሶ መሳም የጣዖት አምላኪዎች ትውፊት እንጂ በመንፈስና በእውነት ሕያውን አምላክ የሚያመልኩ እውነተኛ ምእመናን ታሪክ አይደለም።

አንዳንድ ልባቸው በእግዚአብሔር ቃል ያልተጎበኘ ሰዎች ከበሮ በኃይል ሲደለቅ ከሚፈጠረው የግድግዳ ንቅናቄ ወይም ከነፋስ የተነሣ የተንጠለጠለ ሥዕል ሲንቃነቅ አሊያም ትኩር ብለው በማየት በገዛ አእምሮአቸው የፈጠሩትን የቀን ቅዠት/ሀሉሲኔሽን/ እየተመለከቱ ሥዕሉ ሲንቀሳቀስ አየን እያሉ ስለሥዕል የሚያወሩትን ልበወለድ ወሬ ከእግዚአብሔር ቃል በላይ ታማኝ አድርጎ የሚቆጥርና በዚህም የሚመራ ቢኖር በእምነት ነገር የሳተ መሆኑን ያስተውል!

ደራሲው በዚህ ሳያበቃ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ አቋሙን በድርሰቱ ማንፀባረቁን ይቀጥላል። ይኸውም ማርያምን «ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን በእጅሽ ስጪኝ» ማለቱ ነው። ይህም መጽሐፍ ቅዱሳችን የክርስቶስን ሥጋና ደም ስለመብላትና ስለመጠጣት በዮሐ6:35 የሚያስተምረውን እውነት በእጅጉ የሚጻረር ነው። በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንደተገለጠው ሰው የክርስቶስን ሥጋና ደም የሚበላው በእምነት ክርስቶስን ወደ ሕይወቱ ሲያስገባ ነው። ይህም የሚፈጸመው በመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት እየተስጠለት ካለው ጌታ ጋር ኅብረት በማድረግ ነው/ዮሐ6:63/። የሚታኘክ ሥጋ ወይም የሚጠጣ ደም የለም፤ በእርግጥ የሚታኘክ አለ ብለው የሚያስቡ ቢኖሩ እንኳ ጌታ ራሱ «ሥጋ ምንም አይጠቅምም» ሲል የሰውነቱን ሥጋ በቀጥታ ይሰጠናል ብለው ላሰቡ ሰዎች የተናገረውን ያስተውሉ /ዮሐ6:63/። ደራሲው ለመናገር የፈለገው በማቴ26:26-28 የተገለጠውን ኅብስትና ወይን በእጅሽ ስጪኝ ለማለት ከሆነ ደግሞ ይህ የክርስቶስ ሥጋና ደም ምሳሌና መታሰቢያ የሚሆን የጌታ እራት ነው እንጂ የክርስቶስ ሥጋና ደም አይደለም /1ቆሮ11:23-26/፤ ሰይጣን አማኞች ሊተጉበት የሚገባውን «እንጀራ መቍረስ/የጌታ እራት/» እንዳያስተውሉ የሰውን አእምሮ ለማጨለም የሌለ ነገር ፈጥሮ አሁን በሥጋ ከሌለች ከማርያም እጅ የክርስቶስን ሥጋና ደም እንዲለምኑ ያደርጋል፤ ስለዚህ ይህንን ልመና ትቶ በስሙ በተሰበሰብን ጊዜ በመካከላችን ከሚገኘውና የእራቱ ባለቤት ከሆነው ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ እጅ የሥጋውንና የደሙን ምሣሌ የሞቱም መታሰቢያ የሆነውን ኅብስቱን/እንጀራውን/ እና ወይኑን በመንፈስ ወደምንቀበልበት ገበታ መመለስ ይገባል።

7ኛ. «ሰላም ለሥዕልኪ ሐፈ ማኅየዊ፣ በጸዳንያ ወግብፅ ዘአውኀዘት በኢሕሳዊ፣ ለመጸብሐዊ ማቴዎስ አንተ ረሰይኪዮ ወንጌላዊ»

«በጸዳንያና በግብፅ አዳኝ ወይም ፈዋሽ ሳብን ወዝን ያስሐሰት ሳመነጨች ሥዕልሽ ሰላም እላለሁ፤ ቀራጥ ማቴዎስን ወንጌላዊ ያደረግሽ አንቺ ነሽ»

/ርኅርኅተ ኀሊና ከሚባለው ክፍል -ገጽ 132-133/

ስለ ማቴዎስ ደራሲው «ቀራጭ ማቴዎስን ወንጌላዊ ያደረግሽ አንቺ ነሽ» ብሏል፡፡ ይሁን እንጂ ማቴዎስ ስለራሱ እንዴት እንደተጠራ ሲጽፍ «ኢየሱስ ከዚያ አልፎ በመቅረጫው ተቀምጦ የነበረ ማቴዎስ የሚባል አንድ ሰው አየና ተከተለኝ አለው ተነሥቶም ተከተለው»/ማቴ9፡9/ ብሏል፡፡ ይህ በሌሎች ወንጌላትም ተመዝግቧል/ማር2፡14፣ ሉቃ5፡27/፡፡ መጽሐፈ ሰዓታት ይህን እውነተኛ ታሪክ ውድቅ በማድረግ ማቴዎስን ወንጌላዊ ያደረገችው ማርያም እንደሆነች አድርጎ በድፍረት ይናገራል፡፡ በማስተዋል ለተመለከተው ሰው ይህ ኢየሱስን ከቅዱስ መጽሐፍ ለመሰረዝና በማርያም ለመተካት እንደዚሁም የእርሱን ታሪክ ለእርስዋ ለማድረግ ሆን ተብሎ የተደረገ ይመስላል፡፡ ቅዱስ መጽሐፍን ያነበበ ሁሉ ሳይገርመውና ሳይደንቀው አይቀርም፡፡ መጽሐፈ ሰዓታትን ስትጠቀሙ የነበራችሁና አሁንም በመገልገል ላይ ያላችሁ ሁሉ እስቲ አስተውሉ፤ እንዲህ ያለውን ዓይን ያወጣ ውሸት ለምን ትታገሣላችሁ? በውኑ ከዚህ የተነሣ የደራሲው ማንነትስ አያነጋግርምን? መቼም ማርያም ማቴዎስን ወንጌላዊ አደረገች የሚል ከመጽሐፈ ሰዓታት በቀር ሌላ አይገኝም፡፡ ከዚህ የበለጠ ውሸትስ ምን አለ?

ታዲያ ይህን የመሰለ የታሪክ መፋለስን ደብቆ ውሸት የሆነውን እያዜሙ የክርስትናን ትምህርት ሲቃወሙ ከመኖር ይልቅ ወደ እውነት መመለስ አይበጅምን? መጽሐፍ ቅዱስን ያነበበ ሁሉ ይታዘበኛል ሳይሉ አፍን ሞልቶ ማርያም ማቴዎስን ወንጌላዊ አደረገችው ማለት ትልቅ ሰይጣናዊ ግርዶሽ ነው /2ቆሮ4፡3-4/፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ባነበበ በማንም ሰው ዘንድም ከትዝብት የሚጥል ጉዳይ ነው፡፡ የሚገርመው መጽሐፉ እርማት እንዳይደረግበት በመንፈስ ቅዱስ ተደረሰ እየተባለ ትልቅ ቦታ መያዙ ነው፡፡ በውኑ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በሐሳብ የማይገናኝ ይልቁንም መጽሐፍ ቅዱስን የሚቃረን መጽሐፍ በአለብዎተ መንፈስ ቅዱስ ተደረሰ ማለትስ የመንፈስ ቅዱስን ስም ማጉደፍ አይደለምን? አንባቢያን ሆይ መቼም የሐሰት አባት ዲያብሎስ

እንደሆነ ተጽፏል/ዮሐ8:44/:: ከሐሰት ጋር መስማማት ደግሞ ከዲያብሎስ ጋር መስማማት ነው:: በመሆኑም ይህንን ሐሰት መተው ብቻ ሳይሆን መቃወምም ይገባል::

ደራሲው በዚህ ብቻ ሳያበቃ «ፊዋሽ ላብን/ወዝን/ ያለሐሰት ላመነጩች ሥዕልሽ ሰላም እላለሁ» በማለት ሐሰትን በሐሰት ላይ ይጨምራል:: በፈጠራ «ሥዕሏ የሚፈውስን ላብ አመነጨ» ብሎ መተረክ ይቻል ይሆናል:: ቁም ነገሩ ግን በእርግጥ እንደዚህ ያለ ሥዕል ነበረን? ከሚለው ጥያቄ አስቀድሞ በዚህ መልኩ ሰዎች እንዲፈወሱ የእግዚአብሔር እቅድ አለን? በእግዚአብሔርስ ቃል ውስጥ በዘመናት እንደዚህ ያለ ልምምድ ታይቶ ይታወቃልን? የሚሉ ጥያቄዎችን መመለሱ አግባብ ነው:: የእግዚአብሔር ቃል ማናቸውንም ምስል ለአምልኮ እንዳንጠቀም እየከለከለ በሌላ በኩል ደግሞ ሥዕል በተአምራት ወዝ አወጣ ማለት እግዚአብሔርን ከራሱ አሠራር ውጭ ማድረግ እንደሆነ እንመለከታለን:: በመሠረቱ እንደዚህ ዓይነት ሥዕል ኖሮ የማያውቅ ከመሆኑም ሌላ ቢኖርም እንኳን ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ ምክር ጋር የሚጋጭ በመሆኑ ቅዱሳን አይቀበሉትም:: በጥቅሉ ደራሲው «ማቴዎስን ማርያም ወንጌላዊ አደረገችው» ያለውና «ሥዕል ወዝ አወጣ» ብሎ የጻፈው ሐሰት ሁለቱም «በሬ ወለደ» መሆናቸውን የሚጠራጠር ማነው? «ማቴዎስን ወንጌላዊ ያደረገችው ማርያም ናት» ብሎ የሚዋሽ ደራሲ «ሥዕል ፊዋሽ ላብ ወይም ወዝ አመነጨ» ብሎ ሲያወራ «ሊሆን ይችላል» ብሎ የሚጠራጠር ቢኖር እርሱ ራሱን ለማባት የተዘጋጀ ሰው እንደሆነ ይወቅ፤ ይህንን ደግሞ ለእውነት የሚታዘዙና ሐሰትን የሚጠሉ አስተዋዮች ምንጊዜም አይስቱትም:: ስለሆነም በዚህ ዓይነት ወዝ የሚያወጡና እንባ እያፈሰሱ የሚያለቅሱ ብዙ ሥዕሎች አሉ እየተባለ በሚነገራቸው ሐሰት የሳቱ የዋሃን እናቶችና አባቶች፣ ወንድሞችና እህቶች ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ሰው ነቅተው ከተያዙበት ድንዛዜ ውስጥ በአስቸኳይ ሊወጡ ይገባቸዋል::

8ኛ. «ሰፍጣኒተ ረድኤት ማርያም በጊዜ ምንዳቤ ወስፀባ፣ ሰዓይን እምቀራንባ፣ ሰንቲ ውእቱ ረዳኢተ ያዕቆብ በቤተ ላባ»

«ከዓይን ሽፋሽፍት ይልቅ በችግርና ምንም ረዳት በሌለበት ጊዜ ማርያም እርዳታን ታፈጥኛለሽ፤ በላባ ቤት ሳለ ያዕቆብን የረዳሽው አንቺ ነሽ»

/ተፈስሒ ማርያም ከሚባለው ክፍል- ገጽ 247/

በላባ ቤት የነበረው የይስሐቅ ልጅ ያዕቆብ ነው:: ይህ ያዕቆብ የኖረው ብሉይ ኪዳን ባልተጻፈበትና አባቶች

እግዚአብሔርን በሕገ ልቡና ያመልኩ በነበረበት ዘመን ነው። ማርያም ደግሞ በሐዲስ ኪዳን ማለትም በዘመነ ወንጌል የነበረች ናት። ታዲያ ደራሲው ማርያምን «በላባ ቤት ሳለ ያዕቆብን የረዳሽው አንቺ ነሽ» ሲል ይህን የዘመናት ክፍተት በምን አጣጥሞ ነው? ወይስ በስመ ሞክሼ ያዕቆብ የዘብዴዎስን ልጅ የጠራ መስሎት ይሆን? እንደዚህ እንዳይባል ደግሞ ያዕቆብን የረዳችው በላባ ቤት እያለ መሆኑን ደራሲው ገልጾአል። በላባ ቤት የነበረው ያዕቆብ ደግሞ የይስሐቅ ልጅ ያዕቆብ እንደሆነ ከዘፍ29-31 ካሉት ምዕራፎች እንረዳለን። በዚህ በያዕቆብና በማርያም መካከል ቢያንስ ቢያንስ የ2000 ዓመት ልዩነት አለ።

በእውነት የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ይህን ያህል ሲስት በድርሰቱ የሚገለገሉ ሰዎች ይህን ያህል ዓመት ሙሉ አለማስተዋላቸውና አለመንቃታቸው እንዲሁም ለመቃወም አለመነሣሣታቸው ለምን ይሆን? የይስሐቅ ልጅ በትክክል ያዕቆብና የጌታችን እናት ማርያም በዘመን እንደማይገናኙ እየታወቀ ይኸው ንባብ እስከ ዛሬ ድረስ እየተዜመ መኖሩ ላስተዋለው ሁሉ ምንኛ ያሳዝናል!

ከዚህ ጋር አብሮ ሊሄድ የሚችል እንደ ገጠመኝ ሲወራ የሚሰማ አንድ ነገር አለ። ይህም እንዲህ የሚል ነው፤ አንድ ጊዜ በግንቦት 1/ልደታ/ አንድ ጨዋ/ያልተማሩ ወይም ክህነት የሌላቸው የሚባሉ/ መነኩሴ የዋሃን እናቶችን ሰብስበው ሲያስተምሩ «እያችሁ ምእመናን ቅድስት ሐና መካን በነበረችበት ጊዜ ወደ እመቤታችን ቤተክርስቲያን እየሄደች እመቤቴ ሆይ ልጅ ስጭኝ እያለች ዘወትር ትጸልይ ነበር፤ እመቤታችንም ጸሎቷን ተቀብላ ለሐና ልጅ ሰጠቻት ሐናም በዛሬዋ ዕለት ድንግል ማርያምን ወለደች አሉ» ይባላል። እንግዲህ ማርያም ሳትወለድ «በላባ ቤት ያዕቆብን ትረዳው ነበር» የሚለው አባባል ይህንን ከንቱ ተረት ይመስላል። የሚገርመው ደግሞ ይህ የሚዜምለት ሕዝብ የሚባለውን ሳይሰማና ሳያስተውል ከንፈሩን መጠ መሄዱ ነው።

በእርግጥም ሕዝቡ አሜን ብሎ ተቀብሎ ከመሄድ በስተቀር ይርገሙት፣ ይመርቁት ለምን? እንዴት? የሚል ጥያቄ ማንሳትን ይፈራል፤ ይህንን ማድረግንም እንደ ትልቅ ስሕተት ይቆጥረዋል፤ መሪዎችም የሕዝቡን ስሕተት ቢረዱትም አሥራቱን በኩራቱንና ቀዳምያቱን እስካላጓደለ ድረስ የሕዝቡ የሕይወት ጉዳይ አያሳስባቸውም። እግዚአብሔር ለሕዝቡም ለመሪዎቹም ማስተዋልን ይስጣቸው እንላለን።

9ኛ. «ተፈሥሒ ማርያም ሠርገ አሮን ሲዋዊ፣ ተፈሥሒ ማርያም ወለተ ዳዊት ሰንቃዊ፣ ሙካፈ ስዕለቱ ለኢዮብ አመ በቀስሉ ይደዊ»

«ከሴዊ ወገን የሆነ የአሮን ጌጥ ማርያም ደስ ይበልሽ፣ የዘማሪው የዳዊት ልጅ ማርያም ደስ ይበልሽ፣ ኢዮብ በቍስል በታመመ ጊዜ ስመናውን የተቀበልሽው አንቺ ነሽ»

/ተፈስሒ ማርያም ዘአሑድ -ገጽ 158/

ኢዮብ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረ ጻድቅ ሰው ነው:: እግዚአብሔር የኢዮብን ትዕግሥት ለመግለጥ ስለወደደ በሰይጣን እንዲፈተን ፈቀደ፤ መጽሐፈ ኢዮብ ከመጀመሪያው ጀምሮ ኢዮብ ብዙ መፈተኑንና ሰውነቱ በበሽታ መመታቱን ይገልጻል፤ ሆኖም በመጨረሻ እግዚአብሔር ከቀድሞው ይልቅ እንደባረከው ይናገራል/ኢዮብ32:14/::

በኢዮብና በማርያም መካከል የነበረው የዘመን ርቀት እጅግ ብዙ ነው:: ታዲያ ማርያም ባልነበረችበት ዘመን የኢዮብን ልመና ሰማች እንዴት ሊባል ይቻላል? ኢዮብስ ወደ ማርያም እንዴት ሊጸልይ ይችላል? መቼም ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ከመወለዱ በፊት የነበረና ያለ ማንም የለም:: ስለ እርሱ ግን ሥጋን ለብሶ በዚህ ዓለም ከመታየቱ በፊት ሕያውና የሁሉ ፈጣሪ ሆኖ ይኖር እንደነበር ተጽፎለታል/ዮሐ1:1-3/:: ራሱም ስለራሱ ሲናገር «እውነት እውነት እላችኋለሁ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ» ብሏል/ዮሐ8:58/:: ከፍጥረት ወገን ግን ከመወለዱ በፊት ኖሮ እንዲህ ሠራ የተባለለት ማንም የለም፤ ማርያምም ብትሆን ከእናቷና ከአባቷ በፊት ፈጽሞ አልነበረችም:: በአምላክ ሕሊና ታስባ ነበር ሊባል ቢችልም በአምላክ ሕሊና እርሷ ብቻ ሳትሆን ኢዮብም ሆነ እያንዳንዳችን ታስበን ነበር፤ ማንም ፍጥረት ቢሆን በእግዚአብሔር ሳይታሰብ በድንገት የመጣ የለምና:: ይሁን እንጂ በአምላክ ሕሊና ታስበን ስለነበርን ሁላችንም ከመወለዳችን በፊት ሕልውና ነበረን ለማለት አንችልም፤ ስለዚህም ማርያም በአምላክ ሕሊና ታስባ ስለነበረች ከመወለዷ በፊት በሥጋ እንደነበረችና የኢዮብን ልመና እንደተቀበለች ያዕቆብንም በላባ ቤት እንደረዳች አድርጎ ማየቱ እጅግ ድቅድቅ በሆነ ጨለማ ውስጥ መኖር ነው::

ከዚህም ጋር ተመሣሣይ የሆነ በጨዋታ መልክ ሲነገር የተሰማ አንድ ገጠመኝ ማቅረቡ ይህን ሐሳብ ለማብራራት ይረዳል:: «በአንድ ወቅት ለመጋቢት 5 ቀን በአንድ የአቦ ክብረ

በዓል ላይ «የሥቃይ ትርጒም» የሚል ርእስ የተሰጠውን መጽሐፈ ኢዮብን ይዘው የሚሸጡ አንድ ያልተማሩ መነኩሴ «ምእመናን አባቴ አቦ ኢዮብን እንደፈወሱት የሚናገር መጽሐፍ አያምልጣችሁ እያሉ ይሸጡ ነበር። ከመነኩሴ የተነገረው ሁሉ እውነት ነው ተብሎ ስለሚታመን ብቻ መጽሐፉን ሕዝቡ እየገዛ ይሄድ ነበር» ተብሎ ሲነገር ተሰምቷል። የገጠመኙ ትክክለኛነት በውል ባይታወቅም ማርያምን «የኢዮብን ቁስል የፈወስሽ» ብለው የሚያዜሙ ሰዎች አበም «ኢዮብን ፈውሰውታል» ከማለት እንደማይመለሱ መገመት ይቻላል። ድቅድቅ ጨለማ ይሏችኋል እንግዲህ ይህ ነው። የወንጌል ብርሃን በድምቀት እየበራ ባለበት በዚህ ዘመን በእንደዚህ ዓይነት ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ያሉት ወገኖች አንድ ቀን ለእነርሱም እንደሚበራላቸው ተስፋ እናደርጋለን።

10ኛ. «እምቅድመ ሰማያት ወምድር ሐልወትኪ፣ ፀሐይ ወወርኀ ኢቀደሙኪ፣ መሳእክተ ሰማይ ይትለአኩኪ»

«ከሰማይና ከምድር መፈጠር አስቀድሞ ነበርሽ፣ ፀሐይና ጨረቃም አልቀደሙሽም፤ የሰማይ መላእክትም ያገለግሉሽ ነበር።»

/ስብሐተ ፍቁር ዘማርያም - ገጽ 162/

ማርያምን በብሉይ ኪዳን ከነበሩት ከያዕቆብና ከኢዮብ በፊት እንደነበረች አድርጎ ሲያቀርብ የነበረው ደራሲ ከተናገርኩት አይቀር ይለይለት ብሎ ነው መሰል በዚህ ክፍል ውስጥ «ከሰማይና ከምድር መፈጠር አስቀድሞ ነበርሽ ፀሐይና ጨረቃም አልቀደሙሽም» በማለት ይናገራል፤ ዓይን ያወጣ መናፍቅነትና ክህደት ይሏችኋል ይህ ነው። እስካሁን ከተነገረው ሁሉ እጅግ ጽኑ የሆነው ድቅድቅ ጨለማም ይኸው ነው። ይህ ሁሉ ማርያምን ፈጣሪ አስመስሎ በማቅረብ ዓለማት ከመፈጠራቸው በፊት በነበረው በክርስቶስ ፈንታ ተክቶ ለማስመለክ ሲል የእውነት ጠላት በዚህ ጸሐፊ ተጠቅሞ የዘራው እንክርዳድ መሆኑን የእግዚአብሔር ወዳጆች ሁሉ ይገነዘቡታል። አለም ሳይፈጠር ነበረው ሁሉን የፈጠረ እግዚአብሔር ብቻ ነው/ነህ9:6፣ ኢሳ44:24፣ ራእ1:5እና8/። ልጁም ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ከአባቱ ጋር እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ አስረግጦ ይናገራል/ዮሐ1:1፣ 17:5/። ሆኖም ከፍጥረት ወገን ከሰማይና ከምድር መፈጠር በፊት የነበረ የለም። እንደ መጽሐፈ ሰዓታት ደራሲ እምነት ግን ማርያም የአዳምና የሔዋን

ዘር ሳትሆን ከሰማይና ከምድርም በፊት የነበረች ኃይል አርያማዊት ናት ማለት ነው፡፡ ማርያም የአዳምና የሔዋን ዘር ካልሆነች ደግሞ ደራሲው ክርስቶስ ከልዩ ፍጥረት ተወልዶ አዳነን ማለቱ አይደለምን? ይህ አባባሉ ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚያሳፍር ነው፤ ብሉም ትልቁና የመጨረሻው የክህደት ደረጃ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ «የያዘው የአብርሃምን ዘር ነው እንጂ የመላእክትን አይደለም» ብሎ በተናገረው አማናዊ ቃል መሠረት ማርያም የአብርሃም ዘር ናት/ዕብ2፡16/፤ እንደዚሁም የኤልሳቤጥ ዘመድ እንደነበረች ከመጽሐፍ ቅዱስ ማረጋገጥ ይቻላል/ሉቃ1፡36/፡፡ የተወለደችውም ሰማይና ምድር ከተፈጠሩ ከብዙ ሺህ ዓመታት በኋላ ነው፡፡ ሰማይና ምድርንስ እንኳን እርሷ አዳምም አልቀደማቸውም፤ ሰማይና ምድር በተፈጠሩ በስድስተኛው ቀን አዳም ተፈጥሯልና፡፡

ደራሲው ይህ አልበቃው ብሎት ማርያምን «የሰማይ መላእክት ይላላኩልሻል» ብሏታል፡፡ ሐቁ ግን ይህ ሳይሆን መላእክት የሚላላኩት «እነሆ መላእክት ቀርበው ያገለግሉት ነበር»/ማቴ4፡11/ ለተባለለትና እንደዚሁም «የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል»/ማቴ14፡41/ ተብሎ ለተጻፈለት ለእግዚአብሔር ልጅ ለኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል ያለ ማሻማት ይነግረናል፡፡ ስለሆነም ፀሐይና ከዋክብት በመገኘታቸው ያልቀደሙት ሕያው እግዚአብሔርን ነው እንጂ ማርያምን አይደለም፤ የሰማይ መላእክትም ለእግዚአብሔር እንጂ ለማርያም የሚላላኩ አይደሉምና የቀናውን ትምህርት መያዝ ይገባል፡፡

## ስለ ጊዮርጊስ

1ኛ. «ስቤተክርስቲያን ቅድስት ዘኮንከ ርእሳ፣ ጊዮርጊስ ውኩል ከመ አንበሳ፣ ዘዚአየ ሠራዩ ኃጢአት ወአበሳ»

«ስተቀደሰች ቤተ ክርስቲያን ራሷ የሆንህ፣ ጊዮርጊስ እንደ አንበሳ ታማኝ መታመኛ ነህ፣ የኔን አበሣና በደል የምታስተሰርይ ነህ»

/የጊዮርጊስ ስብሐተ ፍቁር በቃል የሚባለ፣ በንትመት ያልተካተተ/

ጊዮርጊስ ማን ነው? ጊዮርጊስ እንደ መጽሐፈ ገድሉ አተራረክ ልዳ በተባለች አገር ዞሮንቶስና ቴዎብስታ ከተባሉ ሰዎች የተወለደ ነው ተብሎ የሚነገርለት ሰው ነው፡፡ በዚሁ ታሪክ መሠረት አባቱ ዞሮንቶስ ሮማውያን ነገሥታት ኢየሩሳሌምን በቅኝ ይገዙበት በነበረበት ዘመን ባለሥልጣን ነበር

ይባላል። አባቱ ሲሞት ጊዮርጊስ በሮማውያን ነገሥታት ዕውቅናን ስለአገኘ ከጦር ሠራዊቱ ጋር አብሮ ታጣቂ እንዲሆን ተደረገ ተብሎም ይነገራል። ጊዮርጊስ ኃይለኛ ተዋጊ በመሆኑ ከጦር መኰንኖች እንደ አንዱ በመቆጠሩ ተወዳጅነትንም አትርፎ እንደኖረ በመጨረሻም በሰማዕትነት እንደሞተ በራሱ ተአማኒነት ባይኖረውም መጽሐፈ ገድሉ ይተርካል።

መጽሐፈ ገድሉ እንዲህ ይበል እንጂ ጊዮርጊስ የጦር ሜዳ ጀግና ይሁን ወይስ ሰማዕት በውል የሚታወቅ ነገር የለም። ነገር ግን ጊዮርጊስ የቤተክርስቲያን ራስ አለመሆኑን በግልጽ መናገር ይቻላል። ሊሆንም አይችልም፤ በቅዱስ መጽሐፍ እንደተዘገበው የቤተክርስቲያን ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው/ኤፌ5:23፤ 1:22/። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ ለምን የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደሆነ ሲያስረዳ «እርሱ የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ... ሁሉ በእርሱ ለእርሱ ተፈጥሮአል፤ ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል፤ እርሱም የአካሉ ማለት የቤተክርስቲያን ራስ ነው»/ቈላ1:15-18/ በማለት ይመሰክራል። በመሆኑም ራስ ወዳልሆኑት ነገሮች የተጠጋ ሰው ወደ ክርስቶስ አያድግም /ቈላ2:16-19/፤ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ቤተክርስቲያን ሌላ ራስ የላትምና። ምክንያቱም ከእርሱ ሌላ በእግዚአብሔር ቤት ላይ የተሾመ ሕያው ራስ የለምና ነው። ስለሆነም እግዚአብሔር ራስ አድርጎ የሾመውን ትቶ የቤተክርስቲያን ራስ ጊዮርጊስ ነው ማለት በእግዚአብሔር ልጅ ላይ በተቃውሞ መነሣት መሆኑን ወልድን የሚያፈቅሩ ወደ እርሱም የተጠጉት ሁሉ ይረዱታል።

ደግሞም ፀሐፊው «እንደ አንበሳ መታመኛ የሆንክ ጊዮርጊስ የኔን አበሳና በደል የምታስተሰርይ ነህ» ይላል። አበሳንና በደልን ከአንዱ ጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሊያስተሰርይ የሚችል የለም፤ ጌታም ራሱ ስለዚህ ነገር ሲናገር «ነገር ግን ለሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢአትን ሊያስተሰርይ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ...»/ ማር2:10/ ማለቱ የሰው ልጅ ሆኖ የተገለጠው ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ እርሱ ብቻ ኃጢአትን እንደሚያስተሰርይ ያስረዳል። ስለ ኃጢአታችን ሥርየትም ደሙን እንደሚያፈስ በስቅለቱ ዋዜማ ጌታችን ተናግሯል/ማቴ26:27/። በተጨማሪም የመጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ ክፍሎች የኃጢአት ስርየት የሚገኘው በክርስቶስ እንደሆነ እንደሚከተለው ይናገራሉ፤ «እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት

የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስሪያ አድርጎ አቆመው፤ ይህም በፊት የተደረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ስለመተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው»/ሮሜ3:25/ ይላል:: ዳግመኛም «እርሱም የኃጢአታችን ማስተስሪያ ነው፤ ለኃጢኣታችንም ብቻ አይደለም ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት እንጂ»/1ዮሐ2:2/ ይላል:: እንደዚሁም «ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደወደደን ስለኃጢአታችንም ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው አይደለም»/1ዮሐ4:10/ ተብሎ ተጽፏል:: ስለዚህ ክርስቶስን ትቶ ጊዮርጊስ ኃጢአትን ያስተሰርያል ማለት ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት መርገጥ ነው:: ፍጡር የኃጢአት ሥርየት ማስገኘት ቢችል ኖሮ ከክርስቶስ ልደት በፊት ስለ እግዚአብሔር ስም በእውነት በመጋዝ የተሰነጠቁ አልነበሩምን/ዕብ11:37/? ሆኖም የሚቻል ባለመሆኑ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን በመስቀል ላይ አሳልፎ ሰጠ:: ስለሆነም በዚህ የሳተ ልመና ውስጥ የሚገኙ ሁሉ በማዳኑና በቤተክርስቲያን ራስነቱ ወደታመነው ጌታ ኢየሱስ ይመለሱ ዘንድ ይጋበዛሉ::

2ኛ. «ጊዮርጊስ አብስከ ነገሀ ወሠርከ፣ እምሥርወ ልብየ አፈቅረከ፣ አርአየኒ ገጸከ ወአስምዓኒ ቃለከ፤ ፀሐይ ዘልዳ፣ ኮከብ ዘልዳ፣ ዘልዳ ንጉሥ ነዐ ጊዮርጊስ»

«ጊዮርጊስ ሆይ ጠዋትና ማታ ከውስጥ ልቤ አፈቅርሃለሁ፤ ፊትህን አሳየኝ ድምፅህንም አሰማኝ አልሃለሁ፤ የልዳው ፀሐይ፣ የልዳው ኮከብ፣ የልዳው ንጉሥ ጊዮርጊስ ና»

/የጊዮርጊስ ስብሐተ ፍቁር - ገጽ 211/

ይህ አንቀጽ የጊዮርጊስ ስብሐተ ፍቁር በሚባለው ክፍል በመጨረሻ ገደማ የሚዜም ነው፤ ደራሲው በዚህ ልመናው በሙታን ዓለም እንዳለ የሚታሰበውን ጊዮርጊስን «ፊትህን አሳየኝ ቃልህንም አሰማኝ» እያለ ጠዋትና ማታ እንደሚጠይቀው ገልጿል:: እንደዚሁም «ፀሐይ ዘልዳ ኮከብ ዘልዳ ዘልዳ ንጉሥ ነዐ ጊዮርጊስ» በሚለው አዝማች «ነዐ» ወይም «ና» እያለ በሕይወተ ሥጋ የሌለውንና ከብዙ ዘመናት በፊት እንደሞተ የሚያውቀውን ጊዮርጊስን ይጠራዋል፤ ይህም አዝማች የጊዮርጊስ ስብሐተ ፍቁር በሚባለው ክፍል በየአንቀፁ የሚባል ነው:: ጊዮርጊስ ወታደር ከመሆኑ በቀር ልዳ በምትባለው ሀገር ንጉሥ እንደነበረ የተረጋገጠ ማስረጃ ሳይኖር «ዘልዳ ንጉሥ ነዐ ጊዮርጊስ» እያሉ መጣራት የቱን ያህል አለማስተዋል እንደሆነ መረዳት ይቻላል::

አመጣጡም በፈረስ ተጭኖ እንዲሆን ሲለምን ደራሲው «ነዐ ጊዮርጊስ እንዘ ትጼአን በፈረስ ማለትም ጊዮርጊስ ሆይ በፈረስ ተጭነህ ና» ይለዋል/ገጽ201/፤ ጊዮርጊስ አሁን በዐፀደ ነፍስ እንዳለ እያመኑ «በፈረስ ተጭነህ ና» ማለት በመንፈሳዊው ዓለም የሌለውን ፈረስ ወደ ዓለመ ነፍስ በመውሰድ የጊዮርጊስን ነፍስና መንፈስ በፈረስ ላይ ማስቀመጥ ነው፤ ይህም ድርሰቱ ከማያስተውል አእምሮ የመነጨ ድርሰት እንደሆነ ያሳያል።

ደራሲውም ሆነ ሰዓታት ቋሚዎቹ በሙታን ዓለም እንዳለ የሚናገሩለትን ጊዮርጊስን «ነዐ» እያሉ የሚጠሩት በየአንቀፁ ነው፤ እንዲያውም በዚሁ የጊዮርጊስ ሰብሐተ ፍቁር በሚሉት ክፍል ውስጥ «ነዐ ጊዮርጊስ» እያሉ የሚጀምሩ በመጀመሪያው አካባቢ 3 አንቀጾች/ገጽ201/ ወደ መጨረሻው ደግሞ 5 አንቀጾች/ገጽ209-212/ አሉ። በእነዚህም አንቀጾች ደራሲውና የሚያዜሙት ሰዎች ጊዮርጊስን «ነዐ» እያሉ የሚጠሩት ከተለያየ ነገር እንዲያድናቸው ነው፤ ለምሳሌ «ነዐ ጊዮርጊስ ... ከመ ታድኅነነ እምቀታሊ ማለትም ከጠላት ታድነን ዘንድ ጊዮርጊስ ና»፣ «ነዐ ጊዮርጊስ ... ከመ ታድኅነነ ይእዜ እመቅሠፍት ማለትም ከመቅሠፍት ታድነን ዘንድ ጊዮርጊስ ና»፣ «ነዐ ጊዮርጊስ ... ከመ ታድኅነነ ይእዜ እምገሃነም ማለትም ከገሃነም ታድነን ዘንድ ጊዮርጊስ ና» የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል።

በዓለመ ሙታን የሚገኙ ነፍሳትን መጥራት በእግዚአብሔር ቃል በእጅጉ የተወገዘ የባዕድ አምልኮ ድርጊት ነው። እግዚአብሔር በቃሉ ሲናገር «...መናፍስትንም የሚጠራ፣ ጠንቋይም ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ» ብሏል/ዘዳ18፡11/። ታዲያ ይህንን እውነታ ተላልፎ ሙታንን ለእርዳታ መጣራት «እግዚአብሔር ሲርቀውና ጠላት ሲሆንበት» የሞተውን ነቢዩ ሳሙኤልን ለማማከር እንደሞከረው ሳኦል መሆን አይደለምን?/1ሳሙ28፡8-29/። ይህ መናፍስትን ለመጥራት መፈለግስ በራሱ በጠሪዎቹ ላይ እግዚአብሔር እንደራቃቸው ወይም እንደተጣላቸው ምልክት አይሆንባቸውምን? ሕያው እግዚአብሔር ጠላት ከሆነባቸውስ ማን ሊያድናቸው ይችላል?

የመጽሐፈ ሰዓታት ደራሲ በነበረበት ዘመንም ይሁን በአሁኑ ጊዜ ጊዮርጊስ በዓለመ ሙታን በአፀደ ነፍስ የሚገኝ እንደሆነ «ነዐ» እያሉ የሚጠሩት ሁሉ ያምናሉ፤ ታዲያ ከሞተ በኋላ «ና» እያሉ መጣራት ያው መናፍስትን መጥራት ወይም ሙታንን መሳብ አይደለምን? ይህ ደግሞ በጊዮርጊስ ስም

ለሚሠሩ መናፍስት ስፌ በር አይከፍትላቸውምን? ስለዚህ «ታድነን ዘንድ ና» እያሉ የጊዮርጊስን መንፈስ/ነፍስ/ የሚጠሩ ሁሉ «መናፍስት ጠሪ ... ሙታን ሳቢ በአንተ ዘንድ አይገኝ» በሚለው በዚህ እውነታ ተገሥፀው ንስሐ ቢገቡ መልካም ነው እንላለን። በምትኩም ለማናቸውም የማዳን ጥያቄም «ማዳን የእግዚአብሔር ነው»/መዝ3፡8/ ተብሎ የተነገረለትን አምላክ ብቻ ሊጠይቁ ይገባቸዋል፤ የሙታን መናፍስትን እንዲጠይቁ ለሚገፋፉአቸውም ሁሉ በትንቢተ ኢሳይያስ እንደተነገረው «ሕዝቡ ከአምላኩ መጠየቅ አይገባውምን? ወይስ ለሕያዋን ሲሉ ሙታንን ይጠይቃሉን?» የሚል ቁርጠኛ ምላሽ ሊሰጡ ይገባቸዋል/ኢሳ8፡19/።

3ኛ. «ዝርወ አባል አንተ በከተማ ደብር፣ አስአስከ በግዒር፣
ሰደኒ ነዓ በፍቅር፣ ኀበ ኢመዊት ሀገር»

«በከተማ ተራራ ሥጋህ የተበተነ አንተ በጩኸት አስምነሃስሁ ሞት ወደሌለባት ሀገር ና በፍቅር ውሰደኝ።»

/የጊዮርጊስ ስብሐተ ፍቁር፣ በአሥመራው እትም፣ ገጽ 225/

እዚህ ላይ ጸሐፊው ሞት ወደሌለበት ሀገር ለመሄድ ፈልጓል። ነገር ግን ወደዚያ እንዲወስድ የሚጮኸው ወደ ጊዮርጊስ ነው። ሞት የሌለባት ሀገር የት ናት? ወደዚያችስ ሀገር ሰውን መውሰድ የሚችል ማነው? ብሎ መጠየቁ ተገቢ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ሞት የሌለባት ሀገር ከእግዚአብሔር ዘንድ ልትወርድ ያላት ቅድስቲቱና አዲሲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም እንደሆነች ተገልጧል። የአሁኖቹ ሰማይና ምድር ሲያልፉ እርሷ ትመጣለች፤ ስለ እርሷም እንደዚህ ተብሏል፤ «ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፤ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፤ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና» /ራእ21፡1-4/። ወደዚህች ከተማ የሚገቡ ልብሳቸውን በበጉ ደም ያነጹ ብቻ ናቸው/ራእ7፡14፣ 22፡14/። «ርኵሰትንና ውሸትን የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም/ራእ21፡27/። በሁለተኛው ሞት እንዳይጎዱ የሚሹና ሞት ወደ ሌለባት ሀገር ሊገቡ የሚፈልጉ ሁሉ በሕይወት ሊያኖር ወደሚችልና ሞትን ድል ወደነሳው ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀርቡ በደሙም ከውሸታቸውና ከርኵሰታቸው ሊነጹ ይገባቸዋል። እንዲህ ቢያደርጉ በእርግጥ በኃጢአትና በሞት ላይ ሥልጣን ያለው ጌታ ኢየሱስ ከኃጢአት አንጽቶ ሞት ወደሌለባት ከተማ ያገባቸዋል።

4ኛ. «አማዕምቅቲሃ ስሲኦል ሶበ ጸዋዕኩከ፣ ታውጽእኒ ነዓ ማንጸንተከ፣ ጊዮርጊስ አዳዩ እጊዘከ»

«ከሲኦል የታችኛው ክፍል በጠራሁህ ጊዜ ጊዮርጊስ እኔን የአደራ ገንዘብህን እጄን ይዘህ ታወጣኝ ዘንድ ና»

/የጊዮርጊስ ስብሐተ ፍቁር ገጽ 208/

ጸሐፊው እዚህ ላይ ሲደርስ አስቀድሞ ሞት ወደሌለበት ሀገር ለመወሰድ የሎኸውን ጩኸት የሚጣላ ልመና ይለምናል:: በዚህ ልመናው መሠረት ጸሐፊው ወደሲኦል እንደሚወርድ እርግጠኛ ነው:: ሆኖም ግን ያላወቀው አንድ ትልቅ ቁምነገር አለ፤ ይኸውም ሰው ወደ ሲኦል ከገባ በኋላ ከዚያ መውጣት የማይችል መሆኑን ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ «ዛፍም ወደ ደቡብ ወይም ወደ ሰሜን ቢወድቅ ዛፉ በወደቀበት ስፍራ በዚያ ይኖራል»/መክ11:3/ እንደሚል ሰው ወደ ሲኦል ከወረደ በዚያው ይኖራታል እንጂ ያለበትን ስፍራ ለማሻሻል በጸሎትም ሆነ በሌላ በአንዳች መንገድ እንደሚችል የሚያሳየን የእግዚአብሔር ቃል የለም:: ጊዮርጊስ እንደሚባልለት ጻድቅ ሆኖ ቢገኝና አሁን የጻድቃን ነፍሳት ባሉበት ቦታ አለ ብንል እንኳን በወንጌል እንደተነገረው በሲኦል የሚኖር ወደ ጻድቃን ከተማ፣ በጻድቃን ከተማ የሚኖርም ወደሲኦል ሊደርስ ስለማይችል ልመናው ትረጉም የለሽ ነው:: ይህም ጌታ ስለሞተው ባለጠጋ ሰውና ስለአልዓዛር በተናገረው ይታወቃል፤ ባለጠጋውም ከስቃይ ስፍራ ሆኖ እየጮኸ «አብርሃም አባት ሆይ ማረኝ በዚህ ነበልባል እሣቀያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ» ባለ ጊዜ የአብርሃም ምላሽ «ልጄ ሆይ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደተቀበልህ አስብ፤ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል፤ አንተም ትሣቀያለህ፤ ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደእኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጓል» የሚል ነበር/ሉቃ16:24-26/:: በዚህ መሠረት ከሞተ-ሥጋ በኋላ በኃጥአንና በጻድቃን መካከል ግንኙነት የሌለ ከመሆኑም በላይ ማንም ማንንም ከሲኦል ሊያወጣ እንደማይችል እንረዳለን:: በመሆኑም ከሲኦል የሚድኑበትን የመዳኛ መንገድ ትተው ከወዲሁ ሳይሞቱ «ከሲኦል በጠራሁህ ጊዜ» እያሉ ወደሙታን መንፈሶች በመጽሐፈ ሰዓታት የሚያዜሙ ምንኛ ተሳስተዋል! ወደ ሲኦል እንደሚወርድ እያሰበ የሚዘምር እርሱ ቀድሞውኑ

አማኝ አይደለም፤ አማኙስ ከዳዊት ጋር ከሲኦል መዳኑን በማወቅ «ለዘላለምም ስምህን አከብራለሁ፤ ምሕረትህ በእኔ ላይ ታላቅ ናትና፤ ነፍሴንም ከታችኛይቱ ሲኦል አድነሃታልና» /መዝ86:12-13/ እያለ በእምነት እርግጠኝነት ይዘምራል:: ስለሆነም ወደ ሲኦል ከወረዱ በኋላ ለመዳን ተስፋ የሚያደርጉ በሞትና በሲኦል ላይ ሥልጣን እንዳለው ለመግለጥ «የሞትና የሲኦል መክፈቻ አለኝ»/ራእ1:18/ ያለውንና ያመኑትን ሁሉ ከሲኦል ለማዳን በመስቀል ላይ የሞተውን ጌታ ወደማመንና ወደመከተል ይምጡ እንላለን:: የእግዚአብሔር ቃል «በተወደደ ሰዓት ሰማሁህ በመዳንም ቀን ረዳሁህ ... እነሆ የተወደደ ሰዓት አሁን ነው፤ የመዳን ቀን አሁን ነው»/2ቆሮ6:2/ እያለ እንደሚያስተምረው እልከኝነታቸውን ትተው ነፍሳቸው ከሥጋቸው ተለይታ ወደሲኦል ሳትወርድ ከወዲሁ ከሲኦል ለማዳን ወደሚቻለው ጌታ ሽሹ እንላቸዋለን::

# ስለ ተክለሃይማኖት

1ኛ. «ዘአንገሠከ ክርስቶስ እምአጽናፈ ሰማይ ወምድር፣
በታሕቱሁ ለእግዚአብሐር፣ ሰዓሊ ለነ አቡነ»

«ከሰማይ እስከ ምድር ዳርቻ ከእግዚአብሔር በታች
ክርስቶስ ያነገሠህ አባታችን ለምንልን»

/የተክለሃይማኖት ስብሐተ ፍቁር -ገጽ 214/

ተክለ ሃይማኖት ማን ናቸው? ገድለ ተክለ ሃይማኖት የተባለው መጽሐፍ በሸዋ ክፍለሀገር በቡልጋ አውራጃ ዞረሬ በተባለች መንደር ተወልደው ያደጉና በተለያዩ ክፍላተ ሀገራት እየተዘዋወሩ ወንጌል ያስተማሩ መነኩሴ እንደነበሩ የሚናገርላቸው ሰው ናቸው::

የመጽሐፈ ሰዓታት ደራሲ እኝህን ሰው «ከእግዚአብሔር በታች ከሰማይ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ክርስቶስ ያነገሠህ» ይላቸዋል:: «ከእግዚአብሔር በታች» የሚለው ይህም አገላለጽ ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ሁለተኛው የሰማይና የምድር/የዓለም/ ንጉሥ ተክለሃይማኖት እንደሆኑ የሚናገር በመሆኑ ታላቅ ክህደት ነው:: በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ ክርስቶስ ፍጡር የሆኑትን ተክለሃይማኖትን ከእግዚአብሔር በታች አድርጎ አነገሣቸው መባሉ ነው:: ይህ የክርስቶስን ስም ማጥፋትና በክርስቶስ ላይ ማሬዝ ነው፤ ምክንያቱም ክርስቶስ ይህንን አያደርግምና ነው:: መጽሐፍ ቅዱሳችንም እግዚአብሔር

በንጉሥነቱና በጌትነቱ ገናና የሆነው «ብቻውን» እንደሆነ ሲናገር «ያንም መገለጡን በራሱ ጊዜ ብፁዕና ብቻውን የሆነ ገዥ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ያሳያል»/1ጢሞ6:15/ ይላል:: በእርግጥ በክርስቶስ ያመኑና ከእርሱም ጋር መከራን የተቀበሉ ሁሉ ክርስቶስ በክብር ሲገለጥ በኋለኛ ዘመን ከእርሱ ጋር እንደሚነግሡ የታወቀ ቢሆንም ይህ ደግሞ ለሁሉም አማኞች የተባለ ከመሆኑም ሌላ በኋለኛ ዘመን በክርስቶስ መንግሥት መካፈልን የሚያሳይ እንጂ በዚህ ባለንበት የቤተክርስቲያን ዘመን ከእግዚአብሔር በታች እንደራሴ ወይም ለእግዚአብሔር ሁለተኛ ንጉሥ ወይም ምክትል ሆኖ በሁሉ ላይ መንገሥን የሚያመለክት አይደለም/2ጢሞ2:11-12/:: በተጨማሪም የሰዓታት ደራሲ «ሰዓል ለነ አቡነ ማለትም አባታችን ለምንልን» እያለ ወደ ተክለሃይማኖት ይለምናል፤ ስለሆነም በእርግጥ ተክለሃይማኖት ከሞቱ በኋላ በአካለ ነፍስ ይህን ጸሎት ሰምተው ለሚጸልየው ሰው ልመና ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርቡለት ይችላሉን? ብሎ መጠየቁ አግባብነት አለው:: ምንም እንኳን በአካለ ሥጋ ያሉ አማኞች እርስ በርስ አንዱ ስለሌላው ወደ እግዚአብሔር መለመን እንደሚችሉ በእምላካውያት መጻሕፍት ቢነገርም በአካለ ሥጋ ያለ ሰው ወደ ሞተ ሰው መንፈስና ነፍስ እንደሚጸልይ የሚያሳይ አንዳችም መረጃ አይገኝም:: እንደዚሁም በአካለ ሥጋ ባለ ሰው ማሳሰቢያ ምክንያት በአጸደ ነፍስ ያለ ሰው በአካለ ሥጋ ላለው ሰው አንዳች ሊያደርግለት እንደሚችል የእግዚአብሔር ቃል አያስተምረንም:: ይልቁኑ የምናገኘው ከዚህ ተቃራኒ የሆነውን ነው፤ በመጽሐፈ መክብብ ምዕራፍ 9 ቁጥር 5 ላይ «ሕያዋን እንዲሞቱ ያውቃሉና ሙታን ግን አንዳች አያውቁም፤ .. .. ከፀሐይ በታች በሚሠራው ነገር ለዘላለም እድል ፈንታ ከእንግዲህ ወዲህ የላቸውም» ተብሎ እንደተጻፈው ከፀሐይ በታች በምድር ላይ የሚሠራውንም ሆነ የሚጸለየውን ልመና ሊያውቁ አይችሉም:: ቀደም ሲል እንደተጠቀሰውም በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 16:19-31 ባለው ክፍል የምናነበው ታሪክ እንኳንስ በዓለመ ነፍስ ያሉት በዓለመ ሥጋ ያሉትን ሊረዱ ቀርቶ በዓለመ ነፍስ ያሉትም ቢሆኑ እርስ በርስ ሊረዳዱ እንደማይችሉ በግልጥ ያሳያል:: ሰው ለሰው ቢማልድም ሁለቱም በሕይወተ ሥጋ ሳሉ እንጂ ከሁለቱ አንዳቸው ወይም ሁለቱም ከዚህ ዓለም ሲለዩ አይደለም፤ የሙታንን መናፍስት መጥራት በሕይወተ ሥጋ ላሉ ቅዱሳን የተገባቸው አይደለም፤ እንዲህ የሚያደርጉ ቢኖሩም ይህን ተግባራቸውን ከእምላካውያት

መጻሕፍት እንዳላገኙት ሊታወቅ ይገባል:: እንደዚሁም በአንድ ጊዜ በሁሉ ስፍራ የመገኘት ባሕርይ የሌላቸው ፍጡራን የማንን ልመና ሰምተው የማንን ይተዉ ይሆን ብሎ ማሰብስ ተገቢ አይደለምን? እንደ እግዚአብሔር በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ መገኘትና የሁሉንም ጸሎት መስማት እንደሚችሉ ማሰብስ ፍጡራንን ፈጣሪ ማድረግ አይደለምን? ስለሆነም ሰዎች ከእንዲህ ዓይነቱ የሙታን መናፍስት ጥሪ ወጥተው ምሉዕ በኩለሄ ወደ ሆነው ወደ ሕያው እግዚአብሔር መለመንና ወደ እውነተኛው ንጉሥ ወደ እርሱ ሊደርሱ እንደሚገባቸው ያውቁ ዘንድ በማሰብ ይህንን እውነት በህሊናቸው ፊት እናኖራለን::

2ኛ. «ዘተሰብረ ዐፅምከ፣ ወዘተከዐወ ደምከ፣ በእንተ ኵሉሙ ቅዱሳኒከ፣ ቤዝዎሙ አባ ለሕዝብከ»

«ስለ ቅዱሳንህ ሁሉ አጥንትህ የተሰበረ ደምህም የፈሰሰ አባ ሕዝብህን ተቤዣቸው»

/የተክለሃይማኖት ስብሐተ ፍቁር - ገጽ 214/

ቀደም ሲል የማርያም ስብሐተ ፍቁር በሚባለው ክፍል እንደተመለከትነው ደራሲው ማርያምን «ቤዛዊተ ኵሉ ዓለም» ብሏት ነበር፤ አሁን ደግሞ በዚህ ንባብ ውስጥ ተክለሃይማኖትን «አባ ሕዝብህን ተቤዣቸው» እያለ ይለምናል፤ በጣም የሚያስገርመው ደግሞ የተክለሃይማኖት አጥንት የተሰበረውና ደማቸውም የፈሰሰው ቅዱሳኑን/ሕዝቡን/ ለመቤዠት እንደሆነ መገለጡ ነው:: ደራሲው ተክለሃይማኖት ቤዛ እንደሆኑ አድርጎ የገለጠው በዚህ አንቀጽ ብቻ አይደለም፤ ከዚህም ጠንከር ባለ መልኩ ተክለሃይማኖት የተወለዱት ለኃጥአን ቤዛ ለመሆን እንደሆነ ለማመልከት ሲናገር «በፈቃደ እምላክ ተወልደ ተክለሃይማኖት ዕንቍ፣ ለቤዛ ኃጥኣን ንጹሕ እምወርቅ፣ ሠረቀ ለነ ፀሐየ ጽድቅ» ብሏል፤ ትርጓሜውም «ከወርቅ ይልቅ ንጹሕ የሆነ፣ ዕንቍም የሆነ ተክለሃይማኖት ለኃጥኣን ቤዛ እንዲሆን በአምላክ ፈቃድ ተወለደ፤ የጽድቅም ፀሐይ ወጣልን» ማለት ነው/የተክለሃይማኖት ስብሐተ ፍቁር ገጽ 216/:: በእርግጥ የኢየሱስ ክርስቶስን ብቸኛ ቤዛነት የማያምን ሰው የተለያዩ ቤዛዎችን ሲያቀርብ ህሊናውን ትንሽም እንኳን ሊሰቀጥጠው አይችልም፤ ለሕዝብ ቤዛ ለመሆን የፈሰሰው ደም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው እንጂ የፍጡር ደም አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስ ቤዛነት የተከናወነው በክርስቶስ ደም እንደሆነ ሲገልጥ «በውድ ልጁም እንደጸጋው ባለጠግነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን» ይላል/1ቆሮ1:7/፤ በዚህም

መሠረት ደሙ ቤዛ ሊሆን የቻለው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ በመሆኑ ነው። እውነቱ ይህ ሆኖ እያለ የተክለሃይማኖት አጥንት የተሰበረው ደሙም የፈሰሰው ለሕዝቡ ቤዛ እንዲሆን ነው ብሎ ማመን የእግዚአብሔርን ልጅ ደም መርገጥ የጸጋውንም መንፈስ ማክፋፋት ነው፤ እንዲህ የሚያምነውን ሰው «በቀል የእኔ ነው» ያለው እግዚአብሔር ይበቀለዋል/ዕብ10:28-31/። በመሠረቱ የተክለሃይማኖት ደም ምን ጊዜ እንደፈሰሰ በመጽሐፈ ገድላቸውም ሆነ በታሪክ አይታወቅም፤ ሲሞቱ ነው እንዳይባል በገድላቸው የሞቱት በተቅማጥ በሽታ እንደሆነ በግልጥ ተተርኳል /ገድለ ተክለሃይማኖት፥ ትንሣኤ የመጻሕፍት አሳታሚ ድርጅት፤ ሦስተኛ እትም፤ 1973 የታተመ፤ ምዕራፍ 57፣ ቁጥር 23፣ ገጽ 179/። በሌላ በኩል ደግሞ የመጽሐፈ ሰዓታት ተጠቃሚዎች ራሳቸውም ቢሆኑ በሌላ መጽሐፋቸው ላይ «ሰላም እብል ለንዋየ ውስጥ ምሕረትክሙ፣ ትሩፋተ ገድል ኩኑኒ ሥላሴ አምጣነ ትሩፋት አንትሙ፣ ሰበ ሐርኩስ ከመ እሳተፍ ገድሎሙ፣ ጊዮርጊስ ኢወሀበኒ መጠነ ነጥበ ጠል እምደሙ፣ ወተክለሃይማኖት ክልአኒ ሰባረ እምዐፅሙ» በማለት ሲጸልዩ ይገኛሉ፤ የዚህ ትርጉምም «ሥላሴ ሆይ በውስጣችሁ ላለው፣ ንዋይ ለሆነ ምሕረታችሁ ሰላምታ አቀርባለሁ፤ እርስዎ ትሩፋት ነዎትና የገድል ትሩፋት ሁኑኝ፤ ከገድላቸው ያሳትፉኝ ዘንድ በሄድኩ ጊዜ ጊዮርጊስ ጤዛ የምታክል የደሙን ጠብታ አልሰጠኝም፤ ተክለሃይማኖትም የዐፅሙን ስባሪ ከለከለኝ» ማለት ነው/መልክአ ሥላሴ፣ በተስፋ ማተሚያ ቤት በ1970 የታተመ፤ ገጽ 12/። ስለሆነም በአንድ በኩል ሰዓታት በሚቆምበት ጊዜ «ስለ ቅዱሳንህ ሁሉ አጥንትህ የተሰበረ ደምህም የፈሰሰ አባ ሕዝብህን ተቤዣቸው» እየተባለ በሌላ በኩል ደግሞ መልክአ ሥላሴ ሲባል «...ተክለሃይማኖት ክልአኒ ስባረ እምዐፅሙ ማለትም ተክለሃይማኖት የዐፅሙን ስባሪ ከለከለኝ» መባሉ በአንድ ራስ ሁለት ምላስ መሆን ነው፤ አንዱ ሰዓታት ቋሚ ራሱ በሌላ ጊዜ መልክአ ሥላሴንም ይደግማልና።

በሌላ በኩል ደግሞ የተክለሃይማኖት ደማቸው ፈሷል ቢባል እንኳ ኃጢአት የማያውቀው ንጹሕ ደም አይደለም። ምንም እንኳን የመጽሐፈ ሰዓታት ደራሲ «ከወርቅ ይልቅ ንጹሕ የሆነ» በማለት ተክለሃይማኖትን ቢያወድስም ተክለሃይማኖት እናትና አባት ያሏቸው አዳማዊ ሰው ስለሆኑ ንጹሕ ሊሆኑ አይችሉም፤ ምክንያቱም «ከሴት የተወለደ ሰው የሕይወቱ ዘመን ጥቂት ነው፤ መከራም ይሞላዋል .... ከርኩስ ነገር ንጹሕን ሊያወጣ ማን ይችላል? አንድ እንኳ የሚችል የለም» በማለት

የእግዚአብሔር ቃል ይናገራልና/ኢዮ14:1-4/:: እንደዚሁም «ንጹሕ ይሆን ዘንድ ሰው ምንድን ነው? ጻድቅስ ይሆን ዘንድ ከሴት የተወለደ ምንድን ነው? እነሆ በቅዱሳኑ እንኳ አይታመንም» በማለት ሰው ንጹሕ ሊሆን እንደማይችል ያረጋግጣል/ኢዮ14:14-15/፤ ስለዚህ ተክለሃይማኖት ሰው በመሆናቸውና እንደማንኛውም ሰው በሩካቤ ዘበሥጋ ከአባትና ከእናት የተወለዱ በመሆናቸው ንጹሕ ሊሆኑ አይችሉም፤ ከዚህም በላይ «ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ .... ልዩነት የለምና ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል» /ሮሜ3:11-23/ የሚለው የእግዚአብሔር አዋጅ የሚመለከታቸው ናቸው:: ስለሆነም ተክለሃይማኖት ራሳቸው ቤዛ የሚያስፈልጋቸው ናቸው እንጂ ቤዛ ሊሆኑ የሚችሉ አይደሉም:: ገድለ ተክለሃይማኖት እንደተባለው መጽሐፍ አተራረክ ከሆነ «ከዚህ በኋላ አባታችን ተክለሃይማኖት አስቦ ወዮልኝ ወዮታ አለብኝ እውነተኛው ዳኛ በመጣ ጊዜ በዚያች ቀን ምን እመልሳለሁ፤ የሰማዩ አባቴን ፈቃድ ከሚሠራ በቀር ወደመንግሥት ሰማያት የሚገባ የለም ያለውን ቃሉን አላሰብሁምና አለ፤ ወዮ ያን ጊዜ ወዴት እሸሻለሁ ከሕያው እግዚአብሔር ከቊጣው ፊትስ ወዴት እሄዳለሁ ወዮልኝ ወዮታ አለብኝ፤ ለሰማያዊ ሙሽራ ሠርግ በበጎ ሥራ ያልተሸለምኩ እኔ ወዮልኝ ... ለዓለም አበራሁ ለራሴ ግን ጨለምኩ አለ» የተባለላቸው ሰው ናቸው/ገድለ ተክለሃይማኖት፤ ትንሣኤ የመጻሕፍት አሳታሚ ድርጅት፤ ሦስተኛ እትም፤ 1973 የታተመ፤ ምዕራፍ56፣ ቁጥር1-3፣ ገጽ175/:: ይህ ከሆነ ደግሞ ለራሱ ወዮታ ያለበት ሰው ለሌላው እንደምን ቤዛ ሊሆን ይችላል? እውነተኛው ቤዛ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን አንድ ቀንም ተጸጽቶ የማያውቅና «ከእናንተ ስለኃጢአት የሚወቅሰኝ ማነው?» ብሎ ለአይሁድ መናገር የተቻለው ነው/ዮሐ8:46/፤ ሰው ከመሆኑም ጀምሮ «ኃጢአት ያላወቀው» ነው/2ቆሮ5:21/:: ስለሆነም ደሙ ነውርና እድፍ የሌለበት ንጹህ ደም ነው፤ ቤዛ የሆነንም/የዋጀንም/ በዚህ ንጹሕ ደሙ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ሲገልጥ «ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደበግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደተዋጃችሁ ታውቃላችሁ» ይላል/1ጴጥ1:19/:: «ቅዱስና ያለተንኰል የሆነ ነውርም የሌለበት፣ ከኃጢአተኞችም የተለየ» ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ ማንም የለም/ዕብ7:26/፤ ስለሆነም ፍጹም ንጹሕ የሆነና ለቤዛነት የሚበቃ ከእርሱ ሌላ የለም::

የመጽሐፍ ሰዓታት ደራሲ የኑፋቄውን ክፋት በማሳደግ ተክለሃይማኖት «በአምላክ ፈቃድ ለኃጥአን ቤዛ እንዲሆን ተወለደ» በማለት ይናገራል፤ ይህም የኃጥአን ቤዛ እንዲሆን የተወለደውና ወደዚህ ዓለም የመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለመሆኑ የሚናገረውን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት በቀጥታ የሚቃረን ነው:: በማርቆስ ወንጌል ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም» በማለት ስለራሱ የተናገረውን እናነባለን/ማር10:45/:: ጌታችን ኢየሱስ እንዲህ ብሎ እየተናገረ «ተክለሃይማኖት ለኃጥአን ቤዛ እንዲሆን ተወለደ» ብሎ የሚናገር በክርስትና እውነት ላይ የተነሣ የክህደት ትምህርት እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም:: ከሁሉም የሚያሳዝነው ደግሞ ይህንኑ ክህደት በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ በማስታከክ «በአምላክ ፈቃድ ለኃጥአን ቤዛ እንዲሆን ተክለሃይማኖት ተወለደ» መባሉ ነው:: በአምላክ ፈቃድ ለብዙዎች ቤዛ እንዲሆን ወደዓለም ስለተላከው ስለኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ ሐዋርያው ሲናገር «...ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ» ይለናል/ገላ4:4-5/:: ለእኛ ቤዛነት የሞተው ሞትም በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ የተገነዘቡት ደቀመዛሙርትም ሲጸልዩ «በቀባኸው በቅዱሱ ብላቴናህ በኢየሱስ ላይ ሄሮድስና ጴንጤናዊው ጲላጦስ ከአሕዛብና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር እጅህና አሳብህ እንዲሆን አስቀድመው የወሰኑትን ሁሉ ሊፈጽሙ በዚች ከተማ በእውነት ተሰበሰቡ» በማለት ሁሉም የደረሰበት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ገልጠዋል/ሐዋ.ሥራ4:27-28/፤ ጌታም በጌቴሴማኒ «አባት ሆይ ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ» ብሎ ከጸለየ በኋላ ያችን የሞት ጽዋ መጠጣቱ ማለትም ቤዛ እንዲሆን መሞቱ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ያሳያል/ሉቃ22:43/:: ጴጥሮስም እንደዚሁ በክርስቶስ ደም እንደተዋጀን በጻፈበት ክፍል «ዓለም ሳይፈጠር እንኳ አስቀድሞ ታወቀ»/1ጴጥ1:19-20/ ማለቱ የኢየሱስ ቤዛነት አስቀድሞ በአምላክ የሚታወቅና በአምላክ ፈቃድ የተከናወነ እንደሆነ ያስረዳል፤ ስለሆነም የመጽሐፈ ሰዓታት ደራሲ ይህንን እውነት በመጣስ «በአምላክ ፈቃድ ተክለሃይማኖት ለኃጥአን ቤዛ ሊሆን ተወለደ» በማለት እግዚአብሔርን የኑፋቄው ተባባሪ ለማድረግ በመጣሩ ከሚመጣበት ፍርድ ማን ያድነዋል?

የደራሲው ድፍረት መች በዚህ ብቻ ያበቃና! ተክለሃይማኖትን «የጽድቅ ፀሐይ ወጣልን» በማለት ያወድሳል፤ በትንቢተ ሚልክያስ «...ነገር ግን ስሜን ለምትፈሩ ለእናንተ የጽድቅ ፀሐይ ትወጣላችኋለች፤ ፈውስም በክንፎችዋ ውስጥ ይሆናል...»/ሚል4:2/ ተብሎ የተነገረለት የጽድቅ ፀሐይ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ለሚያምኑ ሁሉ ተክለሃይማኖትን «የጽድቅ ፀሐይ» ማለት በእጅጉ የሚዘገንን ነው:: ሰው ጻድቅ ሊሆን የማይችል ከሆነ/ኢዮ4:17፣ 25:4/፣ የሰውም ጽድቅ የመርገም ጨርቅ ከተባለ/ኢሳ64:6/ ተክለሃይማኖት እንደምን የጽድቅ ፀሐይ ሊሆኑ ይችላሉ? ጻድቅ ናቸው ብለን ብንቀበልና «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» በተባለው መሠረት ብናስብም ክርስቲያን ከፀሐየ ጽድቅ ክርስቶስ ያገኘውን ብርሃን በሕይወቱ ተቀብሎ ለዓለም የሚያበራ ነው ማለት እንጂ እያንዳንዱ በራሱ ፀሐይ ነው ማለት እንዳይደለ ከማንም የተሰወረ አይደለምና እውነተኛውን ፀሐይ ትተው ብርሃን ፍለጋ ወደ ሟች ሰው የሚመለከቱትን ዳግመኛ ወደ ኢየሱስ እንዲመለሱ በፍቅር እናሳስባቸዋለን::

4ኛ. «መነ መነ ተክለሃይማኖት መነ፣ ዐሠረ ወንጌል ዳገነ፣
ወበጸሎቱ ዓለመ አድኃነ»

«ተክለሃይማኖት መነ፤ የወንጌልን ፈለግ ተከተለ፤ በጸሎተ
ም ዓለምን አዳነ»

/የተክለሃይማኖት ስብሐተ ፍቁር -ገጽ 215/

ከላይ በተጠቀሰው አንቀጽ ደግሞ ተክለሃይማኖት አዳኝ ሆነው ቀርበዋል፤ «በጸሎቱ ዓለምን አዳነ» ማለት በክርስትና እምነት ላይ አቻ በማይገኝለት ክህደት መነሣት ነው፤ በሕይወተ ሥጋ ያሉ አማኞች በሕይወተ ሥጋ ላሉ ወዳጆቻቸው ሊጸልዩላቸው ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ በጸሎቱ ማንም ማንንም ማዳን አይችልም:: «በጸሎቱ ዓለምን አዳነ» የሚለው አባባል ግን ዓላማው አንድና ቀጥተኛ ነው፤ ይህም ኢየሱስ ብቻውን የዓለም መድኃኒት እንደሆነ የሚናገረውን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ማስካድ ነው:: «እኛም አይተናል አባት ልጁን የዓለም መድኃኒት ሊሆን እንደላከው እንመሰክራለን»/ዮሐ4:14/ የሚለውን ምስክርነት ጠላት ሰይጣን አይወደውም፤ «መዳንም ከእርሱ በቀር በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ ስም የለምና» /ሐዋ.ሥራ4:12/ የሚለውን የታመነ እውነት ለመደበቅ

በየዘመናቱ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ከመቀየስ ያረፈበት ጊዜ የለም። ተክለሃይማኖት «በጸሎቱ ዓለምን አዳነ» የሚለውም የዚህ ጥረቱ አንደኛ አካል ነው። ስለሆነም ሰዎች በዚህ ክፋት ላይ ነቅተውበት ከእግዚአብሔር ወደተሰጣቸው አዳኝ ወደኢየሱስ ክርስቶስ ፊታቸውን እንዲመልሱ ይጋበዛሉ። ዓይኖቻቸውንም ሊያድኗቸው ከማይችሉ ፍጡራን ላይ አንሥተው «በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል» /ዕብ7፡25/ ተብሎ ወደተነገረለት የእግዚአብሔር ልጅ እንዲያደርጉም ይመከራሉ፤ ምክንያቱም ቃሉ «ስለዚህ ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ የሃይማኖታችን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ» በማለት ያዛቸዋልና/ዕብ3፡1/።

5ኛ. «ተክለሃይማኖት ፀሐይ ለዓለም ብርሃና፣ ለነፍስየ ዛቲ ኢትመንና፣ እመንሱት ዕቀባ ወአድኅና»

«ለዓለም ብርሃንዋ የሆንክ ፀሐይ ተክለሃይማኖት ይህችን ነፍሴን አትናቃት፤ ከፈተናም አድናት»

/የተክለሃይማኖት ስብሐተ ፍቁር -ገጽ 217/

ደራሲው ተክለሃይማኖትን የዓለም አዳኝ አድርጎ ከማቅረቡም ሌላ ነፍስን ከፈተና የሚያድንም አድርጎ አቅርቧል። ይህንንም «ነፍሴን አትናቃት፤ ከፈተናም ጠብቃት አድናትም» በማለት ይናገራል፤ ነፍስን ከፈተና መጠበቅም ሆነ ማዳን የእግዚአብሔር መግቦት እንጂ ከፍጡራን የማይገኝ እንደሆነ አምላካውያት መጻሕፍትን የሚያጠኑ ሁሉ ያውቁታል። ስለሆነም ደራሲው የቀድሞውን ስህተቱን እንደደገመ እንመለከታለን።

ከፈተና መዳንን በተመለከተ ጌታችን ወደ ማን መጸለይ እንዳለብን «አቡነ ዘበሰማያት» ብሎ የሚጀምረውን ጸሎት ባስተማረ ጊዜ በግልጥ አስቀምጦታል፤ በዚያም «ስትጸልዩ እንዲህ በሉ፤ በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ .... ከክፉ አድነን እንጂ ወደፈተና አታግባን....»/ማቴ6፡8፣13/ በማለት ከፈተና ለመዳን ወደሰማዩ አባታችን እንድንጸልይ አስተምሮናል። ዳግመኛም በጌቴሴማኒ «ለደቀመዛሙርቱ ወደፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ» ያለው ወደ እግዚአብሔር እንጂ ወደሞቱትና በእስራኤል ወደሚታወቁት የእግዚአብሔር ሰዎች አልነበረም፤ ተክለሃይማኖት ማንንም ከፈተና ማዳን የማይችሉ በመሆናቸው ከፈተና ለመዳን ወደ ተክለሃይማኖት መለመን የፍጡራንን ውስንነት አለማወቅ ነው። ጌታ ኢየሱስ ግን የእርሱ የሆኑትን

ከፈተና ለማዳን ብቃት ያለው እንደሆነ የተረጋገጠ ነው፤ በጀልባ ውስጥ ተኝቶ ደቀመዛሙርቱ በባሕር ማዕበል በተጨነቁ ጊዜ ማዕበሉንና ነፋሱን በሥልጣን አዝዞ ጸጥ በማድረጉ/ማር4:35-41/፣ በሌላም ጊዜ ብቻቸውን ሳሉ በባሕር መካከል ሌሊቱን ሙሉ በማዕበል ሲጨነቁ ማንም ሳይጠራው መፈተናቸውን ተረድቶ በውኃ ላይ እየተራመደ ወደነበሩበት ማዕበል ገብቶ በማዳኑ /ማር6:45-52/፣ በኋላም ሰይጣን ደቀመዛሙርቱን እንደስንዴ ሊያበጥራቸው በለመነ ጊዜ ጌታ ለጴጥሮስ «እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለአንተ አማለድሁ/ወአንሰ ሰአልኩ.../» ባለው መሠረት ከመድረሱ በፊት ሊመጣ ያለውን ችግር አስቀድሞ አውቆ በማማለዱና ጴጥሮስም ከመጣበት ፈተና መመለስ በመቻሉ/ሉቃ22:31-32/ የኢየሱስ እውነተኛ ረዳትነት ተረጋግጧል::

ኢየሱስ ወደ አባቱ ቀኝ ካረገም በኋላም ከፈተና እንደሚታደግ መጽሐፍ ቅዱስ ሲያስረዳ «እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና» ይላል /ዕብ2:18/፤ ዳግመኛም ቃሉ «እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ስላለን ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ፤ ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደእኛ የተፈተነ ነው እንጂ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀካህናት የለንም፤ እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ»/ዕብ4:14-16/ በማለት የሚረዳንን ጸጋ ሊያሰጠን ወደሚችል ወደሚራራ ጌታ ይመራናል::

በፈተናችን የሚራራውን፣ ሊረዳንም የሚቻለውን ሊቀካህናት መደገፊያ ማድረግ ምንኛ የተባረከ ምርጫ ነው! በሁሉም ስፍራ በማናቸውም ጊዜ በፈተናችን ውስጥ መገኘት የሚችል ሕያው ሊቀካህናትን ትቶ ርዳታን ለማግኘት ወደ ፍጡራን መለመንስ ምንኛ የሚያሳዝን አለማወቅ ነው! እርሱ ኢየሱስ ከዘላለም ሞትም ሆነ ከዕለታዊ ፈተናችን የምንድንበት ብቸኛ መዳኛችን ነውና::

# ምዕራፍ 2
# መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ የመጽሐፈ ሰዓታት ውዳሴዎችና ልመናዎች

ባለፈው ምዕራፍ የተመለከትነው መጽሐፈ ሰዓታት በብዙት ከያዛቸው ስህተቶች ውስጥ ጥቂቶቹን ብቻ ነበር። አሁን ደግሞ ከቅዱስ መጽሐፍ ጋር ዝምድና አላቸው የምንላቸውንና በውስጡ የያዛቸውን አንዳንድ ትክክለኛ ውዳሴዎችንና ልመናዎችን ለማሳየት እንሞክራለን። በዚህ ምዕራፍ እነዚህን ከእውነት ጋር የሚስማሙ ውዳሴዎችንና ልመናዎችን ስናሳይ እውነትነት የሚታይበት አካባቢ አልፎ አልፎም ስለሆነ ንባቡ ከሚገኝበት ቦታ ላይ የተወሰኑ ዓረፍተ ነገሮችን ብቻ በመውሰድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እንዴት ሊስማማ እንደሚችል በማመልከት እንደሆነ አንባቢው ከወዲሁ ሊገነዘብ ያስፈልጋል።

መጽሐፈ ሰዓታት እውነት የሆነ መልካም ነገርን ከሚናገርባቸው ክፍሎቹ መካከል በመጀመሪያ የምንመለከተው «ይትባረክ» በማለት የሚጀምረውንና «ቅዱስ ቅዱስ» እያለ የሚቀጥለውን ክፍል ነው። «ቅዱስ ቅዱስ» ብለው የሚጀምሩ ከአንድ በላይ ክፍሎች ስላሉትም የመጀመሪያ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ «ቅዱስ ቅዱስ» በማለት ለሦስት ክፍለን እንመለከታቸዋለን፤

## የመጀመሪያው ቅዱስ ቅዱስ

ከመጀመሪያው ቅዱስ ቅዱስ ውስጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚስማሙትን ክፍሎች አንባቢው እንዲመለከተው በማለት በከፊል መርጠን እንደሚከተለው አቅርበናል።

1ኛ. «ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ እስራኤል ዘገብረ ዓቢየ ወመንክረ ባሕቲቱ፤ ወይትባረክ ስመ ስብሐቲሁ ቅዱስ ወይምላዕ ስብሐቲሁ ኵሉ ምድረ ለይኩን ለይኩን»

«የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ፤ ብቻውን ታላላቅ ነገሮችንና ተአምራትን ያደረገ ልዩ የሆነ የምስጋና ስሙ ይባረክ፤ ምስጋናው ምድርን ሁሉ ይሙላ ይሁን ይደረግ»/ገጽ-7/

ይህ ዝማሬ ከመዝሙረ ዳዊት የተወሰደ መሆኑ ግልጽ ነው/መዝ41፡13፣ 72፡18-20/። በተለይ መዝሙር 72፡18ን

**ስንመለከት ሙሉ ቃሉን እናገኛለን:: «ብቻውን ተአምራትን የሚያደርግ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ፤ የምስጋናው ስም ለዓለምና ለዘለዓለም ይባረክ፤ ምስጋናው ምድርን ሁሉ ይሙላ ይሁን ይሁን» ተብሎ ተጽፎ ይገኛልና፡ በመሆኑም ይህ አንቀጽ ትክክለኛና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ነው እንላለን::**

2ኛ. «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሐር ጸባዖት ፍጹም ምሉዕ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ»

«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አሸናፊ እግዚአብሔር የተቀደሰ ምስጋናህ ሰማይንና ምድርን ሁሉ ሞልቷል»/ገጽ-7/::

**ይህም ምስጋና በትንቢተ ኢሳይያስ «አንዱም ለአንዱ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች»/ኢሳ6፡3/ ተብሎ ከተጻፈው ጋር ተመሳሳይነት አለው::**

3ኛ. «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘእምቅድመ ዓለም ሀሎ ወይሄሉ እስከ ለዓለም»

«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ከዓለም አስቀድሞ የነበረ እስከ ዘለዓለም የሚኖር»/ገጽ8/

**በዚህ አንቀጽ ስለ እግዚአብሔር ዘላለማዊነት የሚናገረው ይህ እውነት በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ በብዙ ቦታ ተመዝግቦአል፤ ለምሳሌ ያህልም የሚከተሉት ይገኛሉ፤ «ያለና የሚኖር» /ዘጸ3፡14/፣ «ያለውና የነበረው የሚመጣው...አልፋና ኦሜጋ» /ራእ1፡18/፣ «እንስሶቹም በዙፋን ላይ ለተቀመጠው ከዘለዓለምም እስከ ዘለዓለም በሕይወት ለሚኖረው...»/ራእ4፡9-11/፣ «ፊተኛውና መጨረሻው...»/ራእ2፡8/፣ «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የነበረውና ያለው የሚመጣውም...»/ራእ4፡8-9/ የሚሉት ናቸው፤ ይህንንም የመሰለ ብዙ ማቅረብ ይቻላል:: ባጠቃላይ «ቅዱስ ቅዱስ» የተባለው ምስጋና 19 አንቀጽ ያለው ሆኖ ከቅዱስ መጽሐፍ ጋር የሚስማማ ነው::**

**ከዚሁ ተያይዞ የሚገኘውም «ግነዩ» በማለት የሚጀምረው ምስጋና ሲሆን እርሱም ከመዝሙረ ዳዊት የተወሰደና የተዘጋጀ ነው፤ ለምሳሌ:**

«ግነዩ ለእግዚአብሔር ወጸውዑ ስሞ ሃቢ ሉያ ወንግርዎሙ ለአሕዛብ ምግባሮ»

«እግዚአብሔርን አመስግኑ ስሙንም ጥሩ ሃሌሉያ ለአሕዛብም ሥራውን ንገሩ»

**የሚል እናገኛለን/ገጽ8/::**

ይህን የምስጋና መዝሙር በዳዊት መዝሙር 105፡1-2 ውስጥ ሙሉ ቃሉ እንዲህ ተጽፎ እናገኘዋለን፣ «እግዚአብሔርን አመስግኑ ስሙንም ጥሩ ለአሕዛብም ሥራውን አውሩ»፤ በዚህ መልኩ መጽሐፈ ሰዓታት በመካከሉ እንደ አዝማች «ሃሌ ሉያ» የሚለውን የምስጋና ቃል እየተጠቀመ ከመዝሙረ ዳዊት ብዙ ዝማሬዎችን ይዟል። በአጠቃላይ ይህን የመሰለ ባለ 20 አንቀጽ «ግነዩ» የሚል ከመዝሙረ ዳዊት የተወሰደ ዝማሬ አለው። ይህም ትክክለኛና አግባብነት ያለው ዝማሬ ነው።

በመቀጠልም «እገኒ ለከ» ብሎ የሚጀምር ምስጋና ይገኛል። ይህም እገዛልሃለሁ ማለት ሲሆን ለምሳሌ ያህል እንደሚከተለው ቀርቧል።

1ኛ. «እገኒ ለከ እግዚኦ አስመ መሐሪ አንተ እግዚኦ ወመስተሣህል ሃሌ ሉያ»

«መሐሪ የምትሆን አንተ አቤቱ እገዛልሃለሁ፤ አቤቱ ይቅር ባይ ነህና ሃሌ ሉያ»/ገጽ12/

2ኛ. «እገኒ ለከ እግዚኦ ርኁቀ መዓት ወብዙኅ ምሕረት ወጻድቅ ሃሌሉያ»

«መዓትህ የራቀ ምሕረትህ የበዛ ጻድቅ አቤቱ እገዛልሃለሁ ሃሌ ሉያ»/ገጽ12/

በዚህ መልኩ ተመሳሳይ የሆኑና ከመዝሙረ ዳዊት የወጡ ሐረጎችን እየተጠቀመ እገዛልሃለሁ በማለት ምስጋናውን ይቀጥላል።

## ሁለተኛው ቅዱስ ቅዱስ

ይህ ሁለተኛ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር በአንድነት በሦስትነት በአንክሮ የሚመሰገን፣ የሚመለክ መሆኑን የሚገልጥና እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ መሆኑን የሚያሳይ ክፍል ነው። ከመነሻው በቀር አስቀድመን እንደተመለከትነው እንደ መጀመሪያው «ቅዱስ ቅዱስ» ይህም ክፍል «ቅዱስ ቅዱስ» እያለ የሚጀምር ምስጋና ነው። መነሻውም እንደዚህ ይነበባል፤

«ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ለዘበስብሐተ ቅዱሳን ይሴባሕ ዘኪያሁ ይሴብሑ ማኅበረ መላእክት ፍሡሐን፣ ሎቱ ይትቀነዩ ነፍሳተ ጻድቃን፣ ወሎቱ ትሰግድ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን፣ እንዘ ትብል ስብሐት በአርያም ወሰላም በምድር ለዘሠምሮ ሰሰብእ»

«በቅዱሳን የሚመሰገን እግዚአብሔርን እናመሰግነው፤

ደስተኞች የሆኑ የመላእክት ማኅበር እርሱን ያመሰግናሉ፤ የጻድቃን ነፍሳትም ለእርሱ ይገዛሉ፤ ቅድስት ቤተክርስቲያንም ለእርሱ ትሰግዳለች፤ እንዲህ እያለች በአርያም በሰማይ ምስጋና ሰላምም ዕርቅም በምድር ሰውን ስወደደ»/ገጽ 24/

*ይህ በሉቃ2:14 ላይ የተመዘገበውን የመላእክት ምስጋና ያያዘ ምስጋና ነው፤ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ሁሉ የሚመሰገን መሆኑንና ሁሉም የሚገዛለት እንደሆነ ያስተምረናል:: ይልቁንም ቅድስት ቤተክርስቲያን ማለትም የምእመናን ኅብረት ጌታ በበረት ተወልዶ ሳለ የተመሰገነውን ምስጋና ታመሰግን በማለቱ ደስ የሚያሰኝ ነው:: በተጨማሪም ይህ ምስጋና እግዚአብሔር በልጁ ዓለምን እንደታረቀ የሚያበስር ነው::*

*በመቀጠልም በዚህ ክፍል «ቅዱስ ቅዱስ» በማለት የሚጀምሩትን 7 የውዳሴ አንቀጾችን እንመለከታለን::*

1ኛ. «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘበአርያም የኀድር፣ ወከርሠ ቀላያት ይኔጽር፣ ግሩም በላዕሉ፣ ነጽሮተ ገጽ ኪሩቤል ኢይክሉ፣ በአክናፈ እሳት ይትኬለሉ፣ ኢያውዕዮሙ ነበልባሉ»

«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር በአርያም በሰማይ የሚያድር፣ የጥልቁንም ሆድ ከርሠ ምድርን የሚመለከት፣ እርሱ በላይ በሰማይ ግሩም ነው፤ ኪሩቤል ፊቱን ማየት አይችሉም፤ ነበልባሉ እንዳያቃጥላቸው በእሳት ክንፎች ይጋረዳሉ»/ገጽ 24/::

*በዚህ አንቀጽ ላይ የምንመለከታቸው ሁለት ነገሮች አሉ:: አንደኛው እግዚአብሔር ሁሉን የሚመለከት መሆኑ ነው:: ይህም አባባል በዕብራውያን መልእክት ተጽፎ ከሚገኘው ሐሳብ ጋር ይመሳሰላል፤ ምክንያቱም «እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖቹ ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም» ይላልና/ዕብ4:13/:: ሁለተኛው ደግሞ ኪሩቤል በክንፎቻቸው ፊታቸውን እንደሚሸፍኑ መገለጡ ነው፤ ይህም በትንቢተ ኢሳይያስ ከተጻፈው ጋር ይመሳሰላል/ኢሳ6:2-3/::*

2ኛ. «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘበሠለስቱ ገጻዊ፣ ወዘበአሐዱ ሕላዌ፣ አኃዜ ዓለም ዘበአሐቲ ምክር፣ ጽምረተ ትሥልስቱ በኩላ ሕዱር»

«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር በሦስት ገጽ እና በአንድነት አኗኗር፣ በአንዲት ምክርም ዓለምን የያዘ፣ የሦስትነቱ ጽምረት በሁሉም ያለ ነው»/ገጽ 24/

***ይህም ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር የሚስማማና የሥላሴን ትምህርት የሚያብራራ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል/ማቴ28:19 ኤፌ4:5-6/::***

3ኛ. «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ዘበተዋሕዶ ይሤለስ፣ እም ኀበ ትጉሃን ይትቄደስ፣ እሳተ ሕይወት ዘኢይትገሰስ፣ ወዘኢይጤየቅ ለዓይን ረቂቅ መንፈስ፣ ንሰግድ ለትሥልስቱ አሐተ ስግደተ፣ ወሎቱ ናቄርብ ስብሐታተ»

«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ በአንድነቱ ሦስትነት ያለው፣ በትጉሃን ዘንድ የሚመሰገን፣ የማይዳሰስ የሕይወት እሳት፣ የማይመረመርና ለዓይን የረቀቀ መንፈስ፣ አንዲት ስግደትን ለሦስትነቱ እንሰግዳለን፣ ለእርሱም ምስጋናዎችን እናቀርባለን» /ገጽ24:25/::

***ይህም ንባብ ከክርስትና ትምህርት ያልወጣ መሆኑ ይታያል:: ለሥላሴ ሊቀርብ ስለሚገባው አንዲት ስግደት ወይም አምልኮ የሚናገር እውነት ነውና::***

4ኛ. «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ዓረፍተ ጽርሑ ዘነድ፣ ወጸፍጸፈ ቤቱ በረድ፣ ኅቡር ኅላዌሁ ዘኢይተበአድ፣ ሎቱ ለባሕቲቱ ይደሉ ሰጊድ»

«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አዳራሹ የእሳት ግድግዳ፣ የቤቱ ጣሪያ በረዶ የሆነ፣ አኗኗሩ የማይለያይ ነው፤ ለእርሱም ብቻ ስግደት ይገባል»/ገጽ 25/

***እዚህ ላይም ምንም እንኳን ደራሲው ለምስጋና የተጠቀመባቸው መነሻ ሐሳቦች እውነተኛነት ባይታወቅም እግዚአብሔርን ለማድነቅ ይህን ብሏል:: ከዚህም በላይ ደራሲው ስግደት ለእግዚአብሔር ብቻ እንደሚገባ «ሎቱ ለባሕቲቱ ይደሉ ሰጊድ ማለትም ለእርሱ ብቻ ስግደት ይገባል» ብሎ ትክክለኛ ምስክርነትን ሰጥቷል፤ ይህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏልና» ብሎ ከተናገረው ጋር ይስማማል/ማቴ4:10/::***

5ኛ. «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ጽርሐ አርያም ማኅፈዱ፣ መካነ ትጉኃን አጸዱ፣ ካህናተ ሰማይ ቅውማን በአውዱ፣ አክሊላቲሆሙ ያወርዱ፣ ቅድመ መንበሩ እንዘ ይሰግዱ ይርዕዱ፣ ወኢይዝብጠሙ ሰበ ይበርቅ ነዱ»

«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ መጋረጃው የአርያም አዳራሽ የሆነ፣ መመስኪያው በትጉኃን ስፍራ የሆነ፣ የሰማይ ካህናት በዙሪያ ቆመዋል፤ በመንበሩ ፊት ሲሰግዱ አክሊላቸውን ያወርዳሉ፤ የእሳቱ ብልጭታ እንዳያቃጥላቸው ይንቀጠቀጣሉ»/ገጽ 25/

*ይህም ሐሳብ በዮሐንስ ራእይ ከተገለጠው የሰማይ አምልኮ የተወሰደ እንደሆነ ይታያል/ራእ4:10-11/::*

6ኛ. «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ መብረቀ ስብሐት ጽርሑ፣ ሰሃዜ ዓለም እራሑ፣ ጎቡር ጎሳዊሁ፣ ፈለገ እሳት ይውኅዝ ቅድሜሁ፣ ወዲበ ኪሩብ ያንበሰብል በርሁ»

«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አዳራሹ የምስጋና መብረቅ የሆነ፣ መዳፉ ዓለምን የያዘ፣ በአንድነቱ ጸንቶ የሚኖር፣ የእሳት ወንዝ በፊቱ ይፈሳል፣ በኪሩብ ላይም ብርሃኑን ያንበለብላል»/ገጽ 25/

*ይህም ስለእግዚአብሔር ግርማና ሞገስ የሚናገር ሲሆን እግዚአብሔር ሁሉን የያዘ እንደሆነ ከሚናገረው እውነት ጋርም የሚስማማ ነው::*

7ኛ. «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘኢይነውም ትጉህ፣ በውስተ ቅዱሳን ስቡሕ፣ ከመ ቀስተ ደመና የአውደ ሡራሒ፣ ሎቱ ለባሕቲቱ ይደሉ ስባሔ»

«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ትጉህ የማይተኛ፣ በቅዱሳን ዘንድ የተመሰገነ፣ እንደ ቀስተ ደመና ብርሃን ይከበዋል፤ ለእርሱ ብቻም ምስጋና ይገባል»/ገጽ 26/::

*በዚህ ክፍል ላይ የምንመለከተው «ትጉህ የማይተኛ» የሚለውን ነው:: ይህ ክፍል በመዝሙረ ዳዊት መዝ121:3-4 ከሚገኘው ቃል ጋር ይመሳሰላል ነው::*

*እንደዚሁም በዚህ ክፍል ውስጥ ሊተኰርበት የሚገባው ዋነኛ ነጥብ «ሎቱ ለባሕቲቱ ይደሉ ስባሔ» ማለት «ለእርሱ ለብቻው ምስጋና ይገባል» የሚለው ነው:: መጽሐፈ ሰዓታት የያዘው እንዲህ ያለ እውነት ብቻ ቢሆን መልካም ነበር፤ ምክንያቱም ለጌታ ብቻ ምስጋናና ስግደት እንደሚገባ ቅዱስ መጽሐፍም በእርግጥ ይመሰክራልና:: በኢሳ42:8 ላይ «እኔ እግዚአብሔር ነኝ ስሜም ይህ ነው፤ ክብሬንም ለሌላ ምስጋናዬንም ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም» በማለት እግዚአብሔር ብቻውን መመስገን እንደሚፈልግ የተነገረው ቃል ተመዝግቧል:: ስለዚህ በመጽሐፈ ሰዓታት ውስጥ የተገኘው ማለትም «ለእርሱ ለብቻው ምስጋና ይገባል» የሚለው አባባል ትክክለኛና በመጽሐፍ ቅዱስም የተደገፈ እውነት ነው::*

# ሞገስነ

ከዚህ በማስከተል የምንመለከተው ክፍል ደግሞ እጅግ ማራኪና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ «ሞገስነ» በመባል የሚታወቅ ድርሰት ይሆናል። ይህም ድርሰት «ሞገስነ ወክብርነ» ብሎ በመጀመር የሚነሣ ሲሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ሁለንተናዊ ብቃት ያለውና ልንመካበት የሚገባ መሆኑን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በመተባበር ያስተምረናል። ይህ ክፍልም 12 አንቀጾች ያለው ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹን ብቻ እንደሚከተለው እናያለን።

1ኛ. «ሞገስነ ወክብርነ፣ ቀርነ መድኃኒትነ፣ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ»

«ሞገሳችንና ክብራችን የመድኃኒታችንም ቀንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው»/ገጽ 121/

ይህም ቃል በሉቃስ 1:68-71 ከምናገኘው ቃል ጋር ይመሳሰላል። በዚህ ክፍል ካህኑ ዘካርያስ ስለክርስቶስ ሲናገር «በዳዊት ቤት የመዳን ቀንድ አስነስቷልና» ብሏል። በእርግጥም ጌታ ሞገስና ክብር የመዳን ቀንድም ነው።

2ኛ. «ትዕምርተ ሰላምነ ዘኪያሁ ንትአመን፣ ዓረፍተ መድኃኒትነ በዘቦቱ ናሰምክ ዕብነ ሕይወት ርእሰ ማዕዘንት ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ»

«በእርሱ የምንታመንበት የሰላማችን ምልክት፣ በእርሱ የምንደገፍበት የመዳናችን ግንብ፣ የሕይወት ድንጋይ፣ የማዕዘን ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው»/ገጽ 121/

ይህ ክፍል ኢየሱስ ክርስቶስን «የሕይወት ድንጋይ፣ የማዕዘን ራስ» በማለት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ሲተባበር እንመለከታለን። መጽሐፍ ቅዱስ «ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ»/ማቴ21:42/ ይላል። ይህን ቃል ጌታ ለራሱ አድርጎ ከመናገሩ አስቀድሞ በመዝሙረኛው በዳዊት በኩል የተነገረው ለእርሱ እንደነበረ አረጋግጦልናል /መዝ118:22-23/። በኢሳይያስ 27:16 ላይ ይኸው ቃል ተነግሯል። እንዲሁም ጴጥሮስ በ1ኛ መልእክቱ 2:6 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ «የማዕዘን ራስ የሕይወት ድንጋይ» መሆኑን አብራርቷልና ይህ አንቀጽ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ዝምድና ያለው በመሆኑ ተቀባይነት አለው።

3ኛ. «ወርቅ ዘተመከዓበ፣ ወመድፍን ዘተረክበ፣ ምናን ዘበዝኃ፣ ወመክሊት ዘረብኃ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ»

«የተከማች ወይም የተሰበሰበ ወርቅ፣ ተሰውሮ የተገኘ መዝገብ፣ የበዛ ትርፋችን፣ የበረከተ መክሊታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው»/ገጽ 121/

አማኝ ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው የራሱ የሆነ አንዳች የሌለውና ለማናቸውም ነገር በእግዚአብሔር ፊት የሚታይለት ሀብቱ ኢየሱስ ስለሆነ ደራሲው «ወርቅ፣ መዝገብ፣ የበዛ ትርፍ፣ መክሊት» እያለ ኢየሱስ ክርስቶስን በምሳሌ መግለጡ መልካም ነው እንላለን።

4ኛ. «ፍናት ሰንበ አቡሁ፣ አንቀጽ ዘመንገለ ወሳዲሁ፣ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ»

«ወደ አባቱ የሚያደርስ መንገድ፣ ወደ ወላጅ አባቱም የሚያስገባ በር ኢየሱስ ክርስቶስ ነው»/ገጽ 122/

ይህም ንባብ ጌታ ስለ ራሱ መንገድነትና በርነት ከተናገረው በቀጥታ የተወሰደ ምስጋናና ምስክርነት ነው /ዮሐ10፡1-18፣ 14፡6/። ይህም የመዳን መንገድና በር ክርስቶስ መሆኑን የሚገልጽ እውነት ነው። የመጽሐፉ ሰዓታት ተጠቃሚዎችም ይህንን መንገድና ይህንን በር በማስተዋል እንዲያዩት ይጋበዛሉ።

5ኛ. «ሊቀካህናት ዘይቀውም ሱሙ ለቅዱሳን በደብተራ ስምዕ እንተ እግዚአብሔር ተከላ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ»

«እግዚአብሔር በተከላት በምሥክር ድንኳን ውስጥ ለቅዱሳን የሚቆምላቸው ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው»/ገጽ 122/

በዚህ ንባብ ደራሲው የክርስቶስን ሊቀ ካህናትነት አውጇል። በእግዚአብሔር ድንኳን ውስጥ ለቅዱሳን የሚቆምላቸው መኾኑንም ማለትም አማላጅነቱን መስክሯል። ደራሲው እዚህ ላይ በእርግጥ ክርስቶስ ኃጢአተኛን የማዳኑን ሥራ ፈጽሞ ስለእኛ ሊያማልድ በአባቱ ቀኝ እንደተቀመጠ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን እውነት ገልጿል፤ ምክንያቱም «ለቅዱሳን የሚቆምላቸው» ብሏልና። ይህም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ይስማማል። ጌታ በመስቀል ላይ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶ በስሙ የሚያምኑትን ለዘላለም ፈጽሞ አድኖአቸዋል፤ ይህንንም በተመለከተ «ተፈጸመ» ብሎ ቅድስት ነፍሱን ሰጥቶ በሦስተኛው

ቀን ከሙታን ተነሥቶ በአባቱ ቀኝ ተቀምጧል/ዕብ1፡3፣ 10፡12/፡፡ በደሙና በመንፈሱ ተቀድሰው የዳኑትን ቅዱሳንን ደግሞ ዕለት ዕለት ሊያግዛቸው፣ በመከራቸው ሊራዳቸውና፣ ጸጋን ሊያሰጣቸው፣ በክህነቱም ወደ አባቱ ሊያቀርባቸው የሰይጣንን ክስ ውድቅ ሊያደርግላቸው፣ በአጠቃላይም ሊያማልዳቸው ስለ ቅዱሳን የሰው እጅ በተከላት ድንኳን ውስጥ ሳይሆን በሰማይ እግዚአብሔር በተከላት የምስክር ድንኳን ውስጥ አሁንም እንደቆመ ለዚህም በሕይወት እንደሚኖር ቃሉ ይመሰክርልናል ይህ ምስጋና ይበል የሚያሰኝ ነው/ዕብ9፡11፣ 7፡25፣ 8፡1-2 ሮሜ8፡34፣ ሐዋ. ሥራ7፡56/፡፡

6ኛ. «ኮከበ ብርሃን ጽብሐዊ፣ ፀሐየ ጽድቅ አርያማዊ፣ ዘበንጽሕ መርዓዊ፣ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ»

«ምሥራቃዊ የንጋት ኮከብ፣ አርያማዊ የጽድቅ ፀሐይ፣ በንጽሕና የተሞሸረ ሙሽራ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» /ገጽ 122/

ጌታ የንጋት ኮከብ እንደሆነ ራእ22፡16 ይነግረናል፣ ፈውስን በክንፎቹ የያዘ እውነተኛ የአርያም የጽድቅ ፀሐይ መሆኑንም ሚልክ4፡2 ይገልጥልናል፤ በተጨማሪም ጌታ በንጽሕና የተሞሸረ ሙሽራ መሆኑን መዝ18፡5 እና ዮሐ3፡29 የሚያስረዱ ስለሆነ ይህ እጅግ መልካም ውዳሴ ነው እንላለን፡፡

7ኛ. «ዘበኀበ አብ ወወልድ ዘበመንፈስ ቃል ወእምድንግል ሕፃን ዘበነቢያት ነቢይ ዘበሐዋርያት ሀዋርያ ዘበሰማዕታት አክሊል መምህር ሊቀ ማኅበር ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ»

«በአብ ዘንድ ልጅ፣ መንፈስ የሆነ ቃል፣ ከድንግል የተገኘ ሕፃን፣ የነቢያት ነቢይ፣ የሐዋርያት ሐዋርያ፣ የሰማዕታት አክሊል፣ መምህር፣ የማኅበረ ምእመናን አለቃ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው»/ገጽ 121-123/

አዎ በእርግጥ ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔር አብ ልጁ ሲሆን/ዮሐ1፡18/ መንፈስ የሆነ ቃልም ነው/ዮሐ1፡1-14፣ 2ቆሮ3፡17/፡፡ ደግሞ ዘመን የማይቆጠርለት እርሱ በሰው ማኅፀን አድሮ ሕፃን ሆኖ መወለዱ/ማቴ2፡11/፣ የነቢያትን ትንቢት ሊፈጽምና የቀረውን ሁሉ ሊነግረን በዘመነ ነቢያት ፍጻሜ ስለሕዝቡ የተነሣ የነቢያት ነቢይ መሆኑ/ዘዳ18፡15-18፣ሐዋ3፡22/፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሃይማኖታችን ሐዋርያ ሆኖ ወደ እኛ መላኩ/ዕብ3፡1/፣ እውነተኛና ብቸኛ ሊቅና መምህር መሆኑ

/ማቴ23:8-10/ እና የቤተ ክርስቲያኑ ራስ ማለትም የማኅበረ ምእመናኑ አለቃ መሆኑ/ቆላ1:18/ በመጽሐፍ ቅዱስ ተመስክሮአልና ይህ አንቀጽ መልካምና ትክክለኛ ውዳሴ ነው።

8ኛ. «ለእለ ቦተ አመነ፣ ወእለ ኪያሁ አምለክነ፣ ሰላም ወሣሕል እምኅበ አቡሁ ይርከበነ»

«እርሱን ለአመንንና እርሱንም ለአመለክን ለእኛ ሰላምና ይቅርታ ከአባቱ ዘንድ ይሁንልን»/ገጽ 123/

በክርስቶስ ኢየሱስ ከሆንን የእግዚአብሔርን ሰላምና ይቅርታ እንደምናገኝ በመጽሐፍ ቅዱስም ተነግሮአልና ይህም ግሩም ልመና ነው/ሮሜ5:1፣ ፊልጵ3:7/።

«ሞገስነ» የተባለው ምስጋናም በዚሁ ይደመደማል። ይህ ክፍልም በመጽሐፈ ሰዓታት ውስጥ የአዲስ ኪዳን ይዘት ያለው ውዳሴ በመሆኑ መልካም ነው ማለት ይቻላል፤ እያንዳንዱ አንቀጽም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐሳብ ያለበት ነውና።

## ሦስተኛው ቅዱስ ቅዱስ

ከዚህ በማያያዝ የምንመለከተው ደግሞ አስቀድሞ እንደተመለከትናቸው ያሉ ቅዱስ ቅዱስ የሚል መነሻ ያላቸው ባለ 7 አንቀጽ ምስጋናዎችን የያዘውን ሦስተኛውን «ቅዱስ ቅዱስ» ሲሆን እርሱም የሚገኘው ሞገስነ ከተባለው ክፍል ቀጥሎ ነው። ለማስረጃ ያህልም ከዚህ በታች እንመለከታለን።

1ኛ. «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት አምላክነ እምኅበ ኪሩቤል ይሴባሕ፣ ወእምሱራፌል ይትቄደስ፣ ወእምሊቃናት ይትዌደስ፣ ስብሐተ መንግሥቱ ዘንጽሕ እምርኩስ»

«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አሸናፊ አምላካችን እግዚአብሔር፣ በኪሩቤል ዘንድ ይመሰገናል፤ በሱራፌል ዘንድም ይቀደሳል፤ በሊቃናት ዘንድም ይወደሳል፤ የመንግሥቱም ክብር ከርኩስ የነጻ ነው»/ገጽ 129/

2ኛ. «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት አምላክነ፣ ዘበአፍራስ እሳት ይጼአን፣ ወዘባነ ደመናት ይከይድ፣ ደባትሪሁ ዘነድ፣ ወሠረገላሁ መርዕድ»

«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አሸናፊ አምላካችን እግዚአብሔር፣ በእሳት ፈረሶች ይጫናል፤ የደመናትን ጀርባ ይረግጣል፤ ድንኳኖቹ የእሳት፣ መንኰራኵር ሠረገላውም የሚያንቀጠቅጥ ነው»/ገጽ 129/

***ይህም በክፊል በዘዳ33:26 ላይ «በደመናት ላይ በታላቅነት የሚሄድ» ተብሎ ከተነገረው ጋር ይቀራረባል።***

3ኛ. «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት አምላክነ ዘበፀዓዕ ይተነከር፣ ወእመባርቅት ይተአኰት፤ ወይትናበብ በእሳት፣ ድምፀ ነጐድጓዱ በሠረገላት»

«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አሸናፊ አምላካችን እግዚአብሔር በትሎች በነፍሳት ይደነቃል፤ በመብረቆችም ይመሰገናል፤ በእሳትም ይናገራል፤ የድምፁ ነጐድጓድም በሠረገላዎች ውስጥ ነው»/ገጽ 129/

4ኛ. «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት አምላክነ ስብሐቲሁ ዘእምኀቤሁ፣ ወውዳሴሁ እምኢአሁ፣ አኃዜ አለም ስሲሁ፣ ሰይፈ በቀል ውስተ እዴሁ፣ ፍትሐ ግፉአን ይወጽእ እምጽርሑ»

«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አሸናፊ አምላካችን እግዚአብሔር፣ ምስጋናው ከእርሱ ዘንድ ነው፤ ውዳሴውም ከራሱ ነው፤ ብቻውን ዓለምን የያዘ ነው፤ በእጁ የበቀል ሰይፍ አለ፤ ለተገፉት ከአዳራሹ ውስጥ ፍርድ ይወጣል»/ገጽ 129/

5ኛ. «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት አምላክነ ሚጠተ ብርሃናት ዘሠርዐ ወሙሳዳቲሆም የአምር፣ ዘይጼውዓ ለጎሕ፣ ለያሠርቆ ለበርህ»

«ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አሸናፊ አምላካችን እግዚአብሔር፣ የብርሃናትን መመላለስ የሠራ፣ ዑደታቸውንም የሚያውቅ፣ ማለዳን የሚጠራ፣ ብርሃንን የሚያወጣ» /ገጽ 129-130/

6ኛ. «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት አምላክነ በተነ ጊሜ ረቂቀ ዘየዓቍር ለማይ፣ የዐርጎ እምቀላይ፣ ወያወርዶ እምኑኃ ሰማይ»

«ቅዱስ ቅዱስ አሸናፊ አምላካችን እግዚአብሔር፣ በረቂቅ የጉም ተን ውኃን የሚያቍር፣ ከውቅያኖስ አውጥቶ አሳርጎ ከሰማይ ርቀት የሚያወርድ»/ገጽ 130/

7ኛ. «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት አምላክነ ዘያንሥር ለዕቡይ፣ ወያሴዕሎ ለነዳይ፣ ያረጥባ ለምድር፣ ወያየብሳ ለባሕር»

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ አሸናፊ አምላካችን እግዚአብሔር፣ ትዕቢተኛውን የሚያዋርድ፣ ምስኪኑን ከፍ ከፍ የሚያደርግ፣ ምድርን የሚያረሰርስ፣ ባሕርንም የሚያደርቅ»/ገጽ 130/

በዚህ በ3ኛው «ቅዱስ ቅዱስ» ክፍል ውስጥ ያለው እንደዚህ ያለ የአድናቆት ምስጋና ነው:: እስከ አሁን በዚህ ክፍል ከላይ የተመለከትናቸው ምስጋናዎች ከፈጣሪ በቀር ሌላ ማንም ፍጡር ጣልቃ ያላስገቡ ከመሆናቸውም በላይ ፈጣሪንም በልጁ በኩል ስለአደረገልን ደኅንነት ማወደስና እንደዚሁም እግዚአብሔርን በፈጠረው ፍጥረት ማድነቅ እንዳለብን የሚያሳዩን ናቸው::

ከዚህ በማያያዝ የምናየው ደግሞ እስከ አሁን ካየናቸው ጸሎቶች ይልቅ እጅግ የሚደንቅና የመጽሐፈ ሰዓታት ተጠቃሚዎች በእጅጉ የሚቃወሙትን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የያዘ ነው:: ይኸውም በመጀመሪያ በኢየሱስ ስም እግዚአብሔርን የሚለምን መሆኑና ሁለተኛ ደግሞ ኢየሱስን አማላጅ አድርጎ ማቅረቡ ነው:: ይህን አባባል እንደሚከተለው ሰፋ አድርገን እንደ እግዚአብሔር ቃል እንመለከታለን::

## በኢየሱስ ስም የቀረቡና የኢየሱስን አማላጅነት የሚገልጹ ልመናዎች

ይህንን በተመለከተ መጽሐፈ ሰዓታት «ኦ አብ በእንተ ኢየሱስ ርድአነ፣ ክርስቶስ ኀበ አቡከ ጌር አማኅፀነነ፣ መንፈስ አብ ወወልድ ናዝዘነ» ይላል፤ ትርጉሙም «አብ ሆይ ስለ ኢየሱስ ብለህ እርዳን፤ ክርስቶስ ሆይ ወደ ቸር አባትህ አማልደን፤ የአብና የወልድ መንፈስ ሆይ አረጋጋን» ማለት ነው/ስብሐተ ፍቁር ዘአምላክ ገጽ 222/::

በዚህ ክፍል ደራሲው እንደ ጻፈው «አብ ሆይ ስለኢየሱስ ብለህ እርዳን» ተብሎ ይጸለያል:: ይህም የጸሎት ሥርዓት መጽሐ ፍ ቅዱሳዊ ነው:: ለዚህም ምስክር ይሆን ዘንድ ቃሉ «እነሆ እውነት እውነት እላችኋለሁ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ»/ዮሐ16:24/:: እንደዚሁም «አብ ስለወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ ማናቸውም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ» ይላል/ዮሐ14:13/:: በተጨማሪም «እግዚአብሔር አብን በእርሱ እያመሰገናችሁ በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት»/ቈላ3:17/ ይለናል:: «በእርሱ» የሚለውን ቃል ልብ ብለን እንመልከተው፤ «እግዚአብሔር አብ ሆይ በልጅህ በኢየሱስ ስም ብለህ ይቅር በለን፤ በልጅህ በኢየሱስ ስም ተመስገን» ማለትን ያሳያል:: ከዚህ

የተነሣ መጽሐፈ ሰዓታት «አብ ሆይ ስለ ኢየሱስ ብለህ እርዳን» ማለቱ መጽሐፍ ቅደሳዊ በመሆኑ «መልካም»፣ «ይበል» የሚያሰኝ ነው::

የክርስቶስ አማላጅነትንም በተመለከተ መጽሐፈ ሰዓታት «ክርስቶስ ኀበ አቡከ ኄር አማኅፀነነ»/ገጽ 222/ ይላል:: ፍቺውም «ክርስቶስ ሆይ ወደ ቸር አባትህ አማልደን» ማለት ነው:: መጽሐፈ ሰዓታት በዚህ አነጋገሩ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ገልጧል:: ከዚህ በፊት እንደተመለከትነውም «ሊቀ ካህናት ዘይቀውም ሎሙ ለቅዱሳን በደብተራ ስምዕ እንተ እግዚአብሔር ተከላ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ማለትም እግዚአብሔር በተከላት በምስክር ድንኳን ለቅዱሳን የሚቆምላቸው ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» በማለት ክርስቶስ ስለቅዱሳን የሚቆም ሊቀካህናት መሆኑን ገልጿል::

ትምህርታቸው ያልጠራ ሆኖ ለመጥቀስ ያስቸግራል እንጂ ይህን የመሰለውን እውነት ሌሎችም የትውፊት መጻሕፍት ተናግረዋል:: ለምሣሌ ያህል በመጽሐፈ ዚቅ «ይቤሎሙ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ አዓርግ ሰማየ ኀበ አቡየ ኀበ እስእል ምህረተ በእንተ እሊአየ ማለትም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የእኔ ስለሆኑት ምህረትን ወደ ምለምንበት ወደ አባቴ አርጋለሁ አላቸው» የሚል ይገኛል/መጽሐፈ ዚቅ፣ ዘሰኔ ሚካኤል ገጽ 189/:: እንደዚሁም ውዳሴ ማርያም የሚባለው መጽሐፍ «ወኮነ ዓራቄ ለሐዲስ ኪዳን ማለትም የሐዲስ ኪዳን አስታራቂ ሆነ» ሲል ከሌላው ስሕተት ጋር ደባልቆ ስለኢየሱስ አስታራቂነት መስክሯል/ውዳሴ ማርያም ዘእሑድ/:: በተጨማሪም በአገራችን ካሉት ቅዳሴያት አንዱ የሆነው ቅዳሴ ማርያም «አንቃዕደወ ሰማየ ኀበ አቡሁ ወአስተምሐረ ወላዲሁ፣ ወአማኅፀነ አርዳኢሁ፣ ከመ ይዕቀቦሙ እምኵሉ እኩይ ማለትም ወደሰማይ ወደ አባቱ ዘንድ ቀና ብሎ አየ፤ የወለደውንም ማለደ፤ ደቀመዛሙርቱንም ከክፉ ሁሉ ይጠብቃቸው ዘንድ አደራ አስጠበቀ» ሲል የምልጃውን ታላቅ ምስክርነት በብዙ ስህተቶች መካከል አስገብቶ አቅርቧል/መጽሐፈ ቅዳሴ፤ አሳታሚ ትንሥኤ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት፤ በ1984 የታተመ፤ ቅዳሴ ማርያም ቁጥር 103 ገጽ 89/:: ዳግመኛም በዘልማድ የሐዋርያት አመክንዮ ተብሎ በሚታወቀው ጽሑፍ ውስጥም «ወዐረቀ ትዝምደ ሰብእ ምስለ እግዚአብሔር ሊቀ ካህናቲሁ ለአብ ማለትም የአብ ሊቀ ካህናት የሰውን ወገን ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ» በማለት ይናገራል/መጽሐፈ ቅዳሴ በሥርዓቱ ክፍል ቁ.43/:: ቅዳሴ ሐዋርያት የተባለውም «ወናሁ ደመ መሢሕከ

ይኬልህ ህየንቴየ ማለት እነሆ የልጅህ ደም በእኔ ፋንታ ይጮሃል» ብሏል/ቅዳሴ ሐዋርያት ቁ.106/::

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ስህተት ያልተቀላቀለበቱ የእግዚአብሔር መጽሐፍ ስለክርስቶስ ምልጃ የሚናገረውን እንመልከት:: ይህም ከላይ ስለኢየሱስ አማላጅነት በመጽሐፈ ሰዓታት የተጠቀሰው ትክክለኛ ትምህርት እንደሌላው የመጽሐፈ ሰዓታት ክፍል ሁሉ የተሳሳተ ድርሰት እንዳልሆነና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆነ አንባቢው ያስተውል ዘንድ ነው:: ጌታም ራሱ ካረገ በኋላ መንፈስ ቅዱስን ለማስጠት ወደ አብ ስለሚያቀርበው ልመና ሲያቀርብ «ወአነ እስእሎ ለአብ ወይፌኑ ለክሙ ጰራቅሊጦስሃ ካልአ ከመ ይንበር ምስሌክሙ ለዓለም ማለትም እኔም አብን እለምነዋለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል» ሲል ተናግሯል/ዮሐ14:15/:: ዳግመኛም ሐዋርያው ጳውሎስ በመልእክታቱ «...ወይትዋቀስ በእንቲአነ ማለትም ስለ እኛ ይማልዳል/ይከራከራል/»/ሮሜ8:34/ በማለት ትናንትም ሆነ ዛሬ ስላለው ስለ ክርስቶስ አማላጅነት በግልጽ ተናግሯል::

አንዳንዶች ክርስቶስ ያማልዳል የሚለውን ትምህርት ክብሩን የሚያሳንስ አድርገው ይቈጥሩታል፤ ይሁን እንጂ ክርስቶስ ይማልዳል ማለት ከእርሱ ዘንድ የጎደለ አለ ወይም አብ ከእርሱ የሚበልጥ ነው ማለት ሳይሆን የእኛን ደካማ ባሕርይ ገንዘብ ስላደረገና በእኛ አካል ተገብቶ እኛ ማግኘት ያልቻልነውን በረከት በእርሱ አማካይነት እናገኝ ዘንድ ስለእኛ ይለምናል ማለት ነው:: በመሠረቱም ሰው የመሆኑ ምሥጢር ለዚህ ነው፤ ይህንንም በተለይ የዕብራውያን መልእክት ሲያብራራ «ስለዚህ የሕዝብን ኃጢአት ለማስተስረይ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት እንዲሆን በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው፤ እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ስለተቀበለ የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና»/ዕብ2:17/ በማለት ሰው የሆነው እኛን ሊረዳ እንደሆነ አስረግጦ ይነግረናል:: ሞቶ ካዳነንም በኋላ ወደ ሰማይ ወጥቶ ወደ መጋረጃው የገባው ስለእኛ እንደሆነ ሲናገር «ይህም ተስፋ እንደ ነፍስ መልሕቅ አለን፤ እርሱም እርግጥና ጽኑ የሆነ ወደ መጋረጃውም ውስጥ የገባ ነው:: በዚያም ኢየሱስ እንደመልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘለዓለም ሊቀካህናት የሆነው ስለ እኛ ቀዳሚ ሆኖ ገባ»/ዕብ6:17/ ይላል፤ ዳግመኛም በዚያ ስለእኛ የሚያከናውነው አገልግሎቱ ምልጃ እንደሆነ ሲያስረዳ «...እርሱ ግን ለዘለዓለም የሚኖር ስለሆነ

የማይለወጥ ክህነት አለው። ስለእነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል»/ዕብ7፡23-25/ ይለናል። የምልጃውንም መልክና ጠባይ ሲያስረዳም «ክርስቶስ በእጅ ወደተሠራችው የእውነተኛይቱ ምሳሌ ወደምትሆን ቅድስት አልገባምና ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ አሁን ይታይ ዘንድ ወደ እርሷ ወደሰማይ ገባ»/ዕብ9፡24/ በማለት ይገልጣል፤ በተጨማሪም መታየቱ እንደምን እንደሆነ ሲገልጥ «እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሠዋ በኋላ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት ይታይላቸዋል»/ዕብ9፡28/ ይላል። ይህም ማለት አስቀድሞ የሕዝብን ኃጢአት በመስቀል ላይ በመሸከም እንደታየ ሁሉ አሁን ደግሞ ኃጢአታቸውን ለተሸከመላቸው ያለኃጢአት በአባቱ ፊት ይታይላቸዋል ማለት ነው። ይህ ስለእኛ ያለ ኃጢአት መታየቱም እኛን በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ያለ ኃጢአት ለመቅረብ ያስችለናል፤ ከዚህም በላይ ጌታ ኢየሱስ በተሟላ የክህነት አገልግሎቱ ያመኑበትን የሚያገለግል አገልጋይ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ሲያስረዳ «ከተናገርነውም ዋና ነገሩ ይህ ነው፤ በሰማያት በግርማው ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀካህናት አለን፤ እርሱም የመቅደስና የእውነተኛይቱ ድንኳን አገልጋይ ነው» ይላል/ዕብ8፡1-2/። በሰማያት መቅደስ እየታየ የሚሰጠው ይህ አገልግሎቱም የምልጃ አገልግሎት መሆኑ ግልጥ ነው። ወደሰማያዊቱ አገር በመጓዝ ላይ የሚገኘው፣ በብዙ ፈተና የተከበበውና ዕለት ዕለት የሚረዳውን ጸጋ የሚያስፈልገው ሕዝብ ያለዚህ ሊቀካህን አማላጅነት ይህንን የምድረበዳ ዓለም እንደምን ሊያልፈው ይችላል?

ስለሆነም ምልጃው የማያጠራጥርና ይህንንም ለመፈጸም ሁል ጊዜ በሰማያዊቱ መቅደስ በዝግጁነት የሚኖር፣ ሳይገደድም በፈቃዱ ደስተኛ ሆኖ የእርሱ ለሆኑት በነጻ የሚያማልድ ብቸኛና ብቁ አማላጅ እርሱ ካህናችን የሆነ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን በማወቅ በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የተነገረውንና መጽሐፈ ሰዓታትም እንኳ ሊያስተባብል ያልቻለውን የኢየሱስን ምልጃ በመቀበል የመጽሐፈ ሰዓታት ተጠቃሚዎች ወደእውነተኛው አማላጅ ዘወር እንዲሉ ይጋበዛሉ።

# ምዕራፍ 3
# የመጽሐፈ ሰዓታት ልመናዎችና ውዳሴዎች እርስበርሳቸው ሲፋለሱ

በዚህች አነስተኛ መጽሐፍ በምዕራፍ አንድ ውስጥ መጽሐፈ ሰዓታት የያዛቸው የስህተቶች ለተጠቃሚዎቹ ያላቸውን ጎጂነት እንደ እግዚአብሔር ቃል አመልክተናል። በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ደግሞ መጽሐፈ ሰዓታት በያዛቸው ብዙ ውሸቶች መካከል አልፎ አልፎ የሚናገራቸው እውነቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያላቸውን ዝምድና አሳይተናል። አሁን ደግሞ በዚህ በአንድ መጽሐፍ ውስጥ እርስበእርሳቸው በግልጽ የሚጋጩትን ክፍሎች በማስተያየት የተጠቃሚዎቹን ኅሊና ለማንቃት እንሞክራለን።

## 1ኛ. ቅድመ ዓለም ስለመኖር

ይህን በተመለከተ ደራሲው «የመጀመሪያው ቅዱስ ቅዱስ» በተባለው ክፍል ውስጥ እግዚአብሔር ቅድመ ዓለም የነበረ እንደሆነ ሲናገር እንደዚህ ይላል፤ «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘእምቅድመ ዓለም ሀሎ ወይሄሉ እስከ ለዓለም ማለትም ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ከዓለም በፊት የነበረ፤ እስከ ዘለዓለም የሚኖር» ይላል/ገጽ 8/።

ይህ እውነት ሆኖ ሳለ ደራሲው «ስብሐተ ፍቁር» በተሰኘው የመጽሐፉ ክፍል ደግሞ ይህን ከቅድመ ዓለም በፊት መኖርን ለጌታ እናት ሲሰጥ፤ «እምቅድመ ሰማያት ወምድር ሀልዎትኪ፣ ፀሐይ ወወርኀ ኢቀደሙኪ ማለትም ከሰማያትና ከምድር በፊት ነበርሽ፤ ፀሐይና ጨረቃም አልቀደሙሽም» በማለት ጽፏል/ገጽ 162/። በዚህ አባባሉም ለእግዚአብሔር ብቻ ሊሰጥ የሚገባውን ቅድመ ዓለም የመኖርን እውነታ ለማርያም በመስጠት የተናገረውን እውነት ሲያፋልስ እንመለከታለን።

## 2. በኪሩቤል፣ በሱራፌልና በመላእክት ስለመመስገን

ይህንንም በተመለከተ ደራሲው ሁለት የሚጣሉ ሐሳቦችን አቅርቧል፤ በአንድ በኩል እነዚህ ሰማያውያን ፍጥረታት እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግኑ ሲናገር በይበልጥ በቀዳሚው ቅዱስ ቅዱስ ክፍል እንደዚህ ጽፏል፤ «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ዘይሴባሕ እምትጉሃን፣ ወይትቄደስ እምቅዱሳን ...ዘይፌርሕዎ ኪሩቤል፣ ወእምግርማሁ ይርዕዱ ሱራፌል/ገጽ8/ ...ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ዘይሴብሕዎ መላእክት ወየአኵትዎ ሥልጣናት/ገጽ10/»

ይላል፤ «ትርጓሜውም ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ በትጉሃን የሚመሰገን በቅዱሳንም የሚቀደስ ...ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ኪሩቤል የሚፈሩት ከግርማውም የተነሣ ሱራፌል የሚንቀጠቀጡለት ..ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ መላእክት የሚያከብሩት ሥልጣናት የሚያመሰግኑት» ማለት ነው:: በዚያው ተቃራኒ ደግሞ ኵሎሙ በሚባለው ክፍል የእነዚህን ፍጥረታት ምስጋና ለጌታ እናት ሲሰጥ «ኵሎሙ ሠራዊተ መላእክት ይሴብሑኪ፣ ዘእምቅድመ ዓለም ሀልዎትኪ» ሲል ይገኛል:: ይህም ማለት «የመላእክት ሠራዊት ሁላቸው ያመሰግኑሻል፤ ከዓለም አስቀድሞ ነበርሽና»/ገጽ124/ ማለቱ ነው:: እንደዚሁም የቀኙቋም ኵሎሙ በሚባለው ክፍል ማርያምን «አእላፈ አእላፋት መላእክት፣ ወትእልፊተ አእላፋት ሠራዊት፣ መናብርት ወሥልጣናት፣ አጋዕዝት ኃይላት፣ ይዌድሱኪ ማርያም በውስተ ውሳጤ መንጦላዕት» ብሏል/ገጽ112/:: ይህም ማለት «የብዙ ብዙ የሆኑ መላእክትና ሠራዊት መናብርትና ገዢዎችና ኃይላትም ማርያም ሆይ በመጋረጃ ውስጥ ያመሰግኑሻል» ማለት ነው:: ዳግመኛም በዚሁ ክፍል የእነዚህ ፍጥረታት የሥራ ድርሻ ማርያምን ማመስገን እንደሆነ ሲገልጥ «ኪሩቤል ሰባሕያን፣ ወሱራፌል መዘምራን፣ ምሉዓነ ጸዳል ወብርሃን፣ ይቄድሱኪ ማርያም በአሐቲ ልሳን» ብሏል/ገጽ112/:: የዚህም ትርጒም «ማርያም ሆይ አመስጋኞች የሆኑ ኪሩቤል፣ ዘማሪዎች የሆኑ ሱራፌል ፈጽመውም የሚያበሩ፣ በአንድ ቃል ያመሰግኑሻል» ማለት ነው:: በመሆኑም ይህንንና ይህን በመሳሰለው ሁሉ እነዚህ ሰማያውያን ፍጥረታት አንድ ጊዜ የፈጣሪ አገልጋዮች ሆነው ሲቀርቡ በሌላ ጊዜ ደግሞ የማርያም አገልጋዮች ሆነው ቀርበዋል:: በዚህም ደራሲው ሁለት የሚፋለሱ ሐሳቦችን አቅርቧል፤ እነዚህ ፍጥረታት በምስጋና የሚያገለግሉት ለእግዚአብሔር ብቻ ነውና::

## 3. ስግደትና ምስጋናን በተመለከተ

መጽሐፈ ሰዓታት ምስጋናና ስግደት ለማን መሰጠት ይገባል በሚለው ሐሳብ ላይም እንደዚሁ ሁለት የሚጋጩ ክፍሎችን ይዟል:: በሁለተኛው «ቅዱስ ቅዱስ» ክፍል ውስጥ «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዐረፍተ ጽርሑ ዘነድ፣ ወጸፍጸፈ ቤቱ በረድ፣ ሕቡር ሕላዌሁ ዘኢይትበአድ፣ ሎቱ ለባሕቲቱ ይደሉ ሰጊድ» ተብሎ ይገኛል/ገጽ 25/፤ ይህም ማለት «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር የአዳራሹ ግድግዳ እሳት፣ የቤቱ ጣሪያ በረዶ የሆነ፣ ያለመለየት የሚኖር ለእርሱ ብቻ

ስግደት ይገባል» ማለት ነው:: እዚህ ላይ የእሳቱ ግድግዳና የበረዶው ጣሪያ በውል ባይታወቅም «ለእርሱ ብቻ ስግደት ይገባል» ማለቱ ተገቢ ሆኖ ሳለ በተቃራኒው ደግሞ ስብሐተ ፍቁር ዘማርያም በሚባለው ክፍል «ንዑ ንስግድ ለባሕቲታ፣ ለማርያም ድንግል ስመ መንታ፣ ለአግብርታ ወለአእማታ ትኩነነ ወልታ» ይላል/ገጽ 172/፤ ይህም ማለት «ስመ መንታ ለሆነች ለድንግል ማርያም ለእርስዋ ብቻ ኑ እንስገድ፤ ለወንድና ለሴት ባሮቿ ጋሻ ትሁነን» ማለት ነው፤ በመሆኑም ደራሲው ስግደት ለማርያም ብቻ ሊሰገድ ይገባል በማለቱ አስቀድሞ ለእግዚአብሔር ብቻ ስግደት ይገባል ያለውን ሐሳብ አፍርሷል:: «ተፈስሒ» ተብሎ በሚታወቀው ክፍል ደግሞ «እሰግድ ቅድመ ማርያም ለዝክረ ስምኪ በጽዋዔ፣ ወእሰግድ ካዕበ ለድንግልናኪ ክልኤ፣ ወእሰግድ ሥልሰ ማርያም ለስእልኪ ቅድመ ጉባኤ፣ ዘኢሰገደ ለሥዕልኪ አስሪያ ምግኤ፣ በሥጋሁ ወበነፍሱ ኢይርከብ ትንሣኤ»/ገጽ247-248/ ብሏል:: ይህም ማለት «ማርያም ሆይ አስቀድሞ የመታሰቢያ ስምሽን በመጥራት እሰግዳለሁ፣ ዳግመኛም ለሁለቱ ድንግልናሽ/የሐሳብና የሥጋ/ እሰግዳለሁ፣ ሦስተኛም በጉባዔ ፊት ለሥዕልሽ እሰግዳለሁ፤ በልቡ ፈቃድ ለሥዕልሽ ያልሰገደ ግን በሥጋውና በነፍሱ ትንሣኤን አያግኝ» ማለት ነው:: በዚህ ብቻ ሳይበቃ ስብሐተ ፍቁር በተሰኘው ክፍል «ንዑ ንስግድ ወንግነይ ላቲ፣ ለማርያም ድንግል ወለተ ማቲ፣ እስመ ተስፋነ ንረክብ እምይእቲ» ሲል ይገኛል/ገጽ171-172/:: ይህም «ኑ እንስገድላት እንገዛላት፣ ለማቲ ልጅ ለማርያም ድንግል፣ ከእርሷ ተስፋችንን እንቀበላለንና» ማለት ነው:: ይህ ሁሉ ቃል መጽሐፈ ሰዓታትን በሚገለገሉ ሰዎች ዘንድ ማርያም እንድትመለክ ያደረገና በአምልኮተ እግዚአብሔር ላይ የተነሣ ድርሰት ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ በሁለተኛው ቅዱስ ቅዱስ ውስጥ ምስጋና ለእግዚአብሔር ብቻ እንደሚገባ ሲናገር «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘኢይነውም ትጉሕ፣ በውስተ ቅዱሳን ስቡሕ፣ ከመ ቀስተ ደመና የዓውዶ ሱራሔ፣ ሎቱ ለባሕቲቱ ይደሉ ስባሔ/ገጽ25-26/ ይላል፤ ይህም «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ትጉሕ የማይተኛ፣ በቅዱሳን ዘንድ የተመሰገነ፣ ብርሃን እንደቀስተ ደመና ይከብበዋል፣ ለእርሱም ብቻ ምስጋና ይገባል» ማለት ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ የተአምረ ማርያም መርገፍ ወይም ማሳረጊያ በሚባለው ክፍል «ስብሐት ለኪ ማርያም በኑልቈ መላእክት ዘአርያም» ይላል፤ ይህም ማለት

«ማርያም ሆይ በአርያም በሚገኙ መላእክት ቁጥር ምስጋና ይገባሻል»/ገጽ239/ ማለት ነው። በዚህም ለእግዚአብሔር ብቻ የተባለው ምስጋና ለእግዚአብሔር ከተባለው በላይ ለማርያም እንደተሰጠ ይታያል።

## 4. ምሕረትን በተመለከተ

በዚህ ርእስ ላይም ሁለት የሚቃረኑ ሐሳቦች በመጽሐፈ ሰዓታት ቀርበዋል። ለምሳሌ ያህል ለመመልከትም «ግነዩ» ተብሎ በሚጠራው ክፍል ውስጥ ስለ ጌታ ርኅራኄ «ርኁቀ መዓት ወብዙኃ ምሕረት ወጻድቅ ሃሌ ሉያ» ተብሎ ይገኛል/ገጽ12/። ይህም «መዓትህ የራቀ ምሕረትህ የበዛ ጻድቅ» ማለት ሲሆን የውዳሴ ማርያም መርገፍ በሚባለው ጸሎት ደግሞ «ጸሎታ ለማርያም ወስዕለታ ያድኅነነ እመዓተ ወልዳ» ይላል። ይህም ማለት «የማርያም ጸሎት ከልጇ ቍጣ ያድነን» ማለት ነው። በዚህም ማርያም ርኅርኅት ጌታ ደግሞ ቍጡ መዓተኛ ሆኖ በመቅረቡ «መዓትህ የራቀ ምሕረትህ የበዛ» ከሚለው ትክክለኛ ቃል ጋር ይፋለሳል።

## 5. አማላጅነትን በተመለከተ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በጣም በሚደንቅ ሁኔታ የተገለጠ እውነት ቢኖር ስለክርስቶስ አማላጅነት ሊያስረዳ የሚችለው የጸሎት ክፍል ነው። ይህም «ኦ አብ በእንተ ኢየሱስ ርድአነ ክርስቶስ ኀበ አቡከ ጌር አማኅፀነነ» የሚለው ነው/ገጽ222/። ይህም «አብ ሆይ ስለኢየሱስ እርዳን ክርስቶስ ወደቸር አባትህ አማልደን» ማለት ነው። ነገር ግን የዚህ ተቃራኒ «ስአሊ ለነ፣ አስተምሕሪ ለነ፣ ስአሉ ለነ፣ አስተምሕሩ ለነ ማለትም ለምኚልን፣ አማልጂን፣ ለምኑልን አማልዱን» የሚሉ ብዙ ክፍሎች በመጽሐፈ ሰዓታት ውስጥ ይገኛሉ/ገጽ27-30/። ብቃት ያለውን ብቸኛ አማላጅ ክርስቶስን ትቶ እንደእኛው ድካምን የሚለብሱና ለእነርሱ ለራሳቸው የክርስቶስ አማላጅነት የሚያስፈልጋቸውን አማላጅ ማድረግ ወይም በክርስቶስ ላይ ተጨማሪ አማላጅ አድርጎ ማዳበል ትልቅ ውድቀት ነው። በአንድ መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ የሚጋጭ ነገር መታየቱም መጽሐፉ ተአማኒነት ሊኖረው የማይችል መኾኑን ያስረዳል።

## 6. ለእግዚአብሔር መገዛትን በተመለከተ

በዚህም ረገድ «ግነዩ» በሚባለው ክፍል ለእግዚአብሔር ስለመገዛትና እግዚአብሔርን ስለማመስገን ተጽፏል። በዚህም ክፍል ከመዝሙረ ዳዊት የተወሰዱ ምስጋናዎች እንደተጠናቀሩ በምዕራፍ ሁለት አይተናል። በዚያም እያንዳንዱ ምስጋና የሚጀምረው «ግነዩ

ለእግዚአብሔር» ማለትም «እግዚአብሔርን አመስግኑ» በሚል አዝማች ቃል ሲሆን ምስጋናውም ሙሉ በሙሉ ከመዝሙረ ዳዊት የተወሰደና የተቀናበረ መሆኑን ተመልክተናል /ገጽ 11-12/:: ከዚያም በመቀጠል በአንደኛ መደብ አነጋገር ደራሲው «እገኒ ለከ» በሚል አዝማች የሚሄድ ምስጋና ይቀጥላል:: ለምሳሌ ያህል አንዱን ብንመለከት፤ «እገኒ ለከ እግዚአ በኵሉ ልብየ ሃሌ ሉያ ወእነግር ኵሎ ስብሐቲከ ማለትም አቤቱ አምላኬ በሙሉ ልቤ እገዛልሃለሁ ምስጋናህንም እናገራለሁ» ይላል/ገጽ12/:: ይህንን የሚጻረር ቃል ደግሞ በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል ለምሣሌ «ገነይነ ለኪ አ ወለተ ዳዊት ዳግሚት ሰማይ፣ ሙጻአ ፀሐይ፣ ወላዲቱ ለአዶናይ» እያለ ለፍጡር የሚቀርብ ምስጋናን ይጀምራል/ገጽ26/:: ይህም ሲተረጐም «የዳዊት ልጅ ሆይ እንገዛልሻለን፤ ዳግመኛ ሰማይ፣ የፀሐይ መውጫ፣ አዶናይን የወለድሽ» የሚል ይሆናል:: በአንድ በኩል በሙሉ ልብ ለእግዚአብሔር መገዛትን ሲያመለክት በሌላ በኩል ደግሞ ለማርያም መገዛትን ያሳያልና የሚፋለስ ሐሳብ መሆኑን ምእመናን በቀላሉ ሊረዱት ይችላሉ::

## 7ኛ. የቤተክርስቲያንን ራስ በተመለከተ

በዚህ በመጽሐፈ ሰዓታት ውስጥ «ሞገስነ» በተባለው ክፍል ኢየሱስ ክርስቶስ «ሊቀ ማኅበር»/ገጽ122-123/ ተብሎ ተጠርቷል:: ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተክርስቲያን /አቅሌስያ-ማኅበር/ ራስ እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ከተነገረው እውነት ጋር ይስማማል/ቈላ1:18/:: ይሁን እንጂ የሰዓታት ቋሚዎች ይህንን እውነት በማፍረስ ጊዮርጊስን «ለቤተክርስቲያን ቅድስት ዘኮንከ ርእሳ ማለትም ለቅድስት ቤተክርስቲያን ራስዋ የሆንክ» እያሉ በማወደስ ያዜማሉ:: ቤተክርስቲያን አንድ አካል ስለሆነች ሁለት ራስ የላትምና ይህንን ሲያዜሙ ክርስቶስ ሊቀማኅበር መሆኑን ከመሰከረው ውዳሴያቸው ጋር አፋልሰውታል::

## 8ኛ. ነፍስን አደራ መስጠትን በተመለከተ

ሰዓታት ሲቆም ተአምረ ኢየሱስ የሚሰኘው መጽሐፍ ከተነበበ በኋላ ነፍስን ለኢየሱስ አደራ መስጠትን የሚያሳይ አንቀጽ ይዜማል፤ ይኸውም «አመ ትመጽእ ለኰንኖ.. አማኅፀንኩ ነፍስዬ ውስተ እዴከ ክቡር ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአ ሰማያት ወምድር .. ማለትም ለፍርድ በመጣህ ጊዜ.. .. የሰማይና የምድር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ.. .ነፍሴን ለክቡር እጅህ አደራ ስጥቻለሁ..»

/ገጽ241/ የሚል ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የመጽሐፈ ሰዓታት ደራሲ ራሱን ለጊዮርጊስ አደራ እንደሰጠ ለማመልከት ሲናገር «አማዕምቅቲሃ ለሲኦል ሶበ ጸዋዕኩከ ታውፅአኒ ነዐ ማኅፀንተከ ጊዮርጊስ እዴየ እኂዘከ ማለትም ጊዮርጊስ ከሲኦል ከታችኛው ክፍል ሆኜ በጠራሁህ ጊዜ እኔን የአደራ ገንዘብህን እጄን ይዘህ ታወጣኝ ዘንድ ና»/ገጽ208/ ይላል። በዚህም ደራሲው አንድ ጊዜ ለኢየሱስ እጅ አደራ ያላትን ነፍሱን በሌላ ጊዜ የጊዮርጊስ የአደራ ገንዘብ ሲያደርጋት ይታያል። አንድ ነፍስ ለሁለት ባለአደራ ልትሰጥ ስለማትችል ይህም ይፋለስበታል።

# ምዕራፍ 4
# መጽሐፈ ሰዓታት ለምን የሚፋለሱ ክፍሎች ሊኖሩት ቻለ?

አንባቢው በመጽሐፈ ሰዓታት ያለውን የእርስ በርስ መፋለስ እንዲያውቅ ለማስቻል ያህል አስቀድመን ያየናቸውን ጥቂት ክፍሎች መርጠን አቀረብን እንጂ በመሠረቱ በመጽሐፈ ሰዓታት የሚጋጩ ሐሳቦች እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት አይደለም። ሆኖም መጽሐፈ ሰዓታት እርስ በእርሳቸው የሚፋለሱ ክፍሎች እንዳሉት ለማስገንዘብ ያህል ይኸው በምዕራፍ ሦስት የቀረበው በቂ በመሆኑ ቀጣዩ ጥያቄ መጽሐፈ ሰዓታት ለምን የሚፋለሱ ክፍሎች ሊኖሩት ቻለ? የሚል ይሆናል። ለዚህም ጥያቄ መልስ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮች እንደሚከተለው በየተራ ቀርበዋል፤

1ኛ. ድርሰቱ በኋላ ዘመን ተጠቃሚዎች ሲከለስ

የመጀመሪያው የመጽሐፈ ሰዓታት ድርሰት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚሄዱ ምስጋናዎች ያሉት ሆኖ ከዚያ በኋላ የነበሩት ተጠቃሚዎች ቆይተው ወደ ስህተት ሲዘፈቁ የፊተኛውን ድርሰት ሳይሽሩ በላዩ ላይ በየጊዜው እያከሉበት የኖሩ እንደሆነ ከላይ የተመለከትነው መፋለስ ይከተላል፤ ይህ ከሆነ ደግሞ አሁን ያለው መጽሐፈ ሰዓታት ብዙ ደረጃዎችን ያለፈ፣ በየጊዜው መምለኪያን ፍጡራን በሆኑ ሰዎች ስህተት ሲከላለስበት የኖረና የብዙ ሰዎች ሐሳብ እየታከለበት አሁን ከሚገኝበት ደረጃ ለመድረስ የበቃ ድርሰት ነው ማለት ነው። ይህም የመጽሐፉን እርስ በርስ መፋለስ ሊያብራራልን ይችላል፤ ይህም ሁኔታ

የመጽሐፈ ሰዓታት ጠባይ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም በአገራችን በጥንታዊነታቸው በሚታወቁ እንደ ያሬድ ድርሰቶች ባሉት ድርሰቶች ላይ የሚንፀባረቅ በመሆኑ መጽሐፈ ሰዓታት በየጊዜው እንግዳ ሐሳብ የተጨማመረበት ድርሰት እንጂ ወጥ ድርሰት አይደለም የሚለው ሐሳብ በቀላሉ የሚታለፍ አይደለም::

## 2ኛ. የደራሲው እምነት የተበረዘ ሲሆን

ሁለተኛው ሐሳብ ደግሞ ደራሲው አንድ ሰው ሆኖ ሳለ ነገር ግን የተጣራና የተስተካከለ እምነት ያልነበረው ሰው ሲሆን ይህ መፋለስ ሊከተል ይችላል የሚል ነው፤ ይህ ከሆነ ደግሞ ደራሲው ፈጣሪንና ፍጡራንን አዳብሎ የሚያመልክ ሰው ነበር ማለት ይቻላል፤ በዘመናችንም በርካታ ሰዎች በዚህ መልኩ ሲመላለሱ ስለምናያቸው ይህም ሊሆን የሚችል ሐሳብ ነው:: ይህ አማራጭ የመፋለሱ መንስኤ ከሆነ ደግሞ ደራሲው መዝሙረ ዳዊትንና አንዳንድ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ለፍጡራን ውዳሴ ለማዘጋጀት እንዲረዳው በሞዴልነት ተጠቅሞባቸዋል ያስብላል::

## 3ኛ. ደራሲው ቆይቶ ወደ ኑፋቄ የገባ ሲሆን

ሦስተኛው ሐሳብ ደግሞ ደራሲው ቀደም ብሎ የተስተካከለ ትምህርት ኖሮት ከጊዜ በኋላ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ወደ ስህተት አዘንብሎ ወይም በሐሳውያን ነገሥታት ተጽዕኖ ሥር ወድቆ ድርሰቱን የከለሰው እንደሆነ ነው:: ይህም ሊሆን የሚችል ነው::

## 4ኛ. ኑፋቄን እውነተኛ እምነት ለማስመሰል የተደረሰ ሲሆን

አራተኛው ደግሞ አስቀድሞውኑ የኑፋቄ ድርሰት ተደርሶ ተቀባይነትን እንዲያገኝ ለማድረግ ሲባል ጤናማ ድርሰቶች እንዲከለሱበት ተደርጎ ይሆናል የሚል ነው፤ ይህም የሰው ልጅ በታሪኩ ሁሉ ሲያደርገው የኖረ ነው፤ ጣዖት ቀርጾ በእግዚአብሔር ስም መጥራት፣ የጣዖታትን በዓላት እያከበረ የእግዚአብሔር በዓል ነው ማለት የተለመደ ተግባሩ ነውና /ዘጸ32፡4-5፣ 1ነገሥ12:28/:: በዘመነ ሐዋርያትም የነበሩ መናፍቃን ኑፋቄያቸውን ለማስራጨት የተጠቀሙበት ዘዴ «ሐዋርያት ሳይሆኑ ሐዋርያት ነን»/2ቆሮ11፡13፣ራእ2፡2/፣ «የሰይጣን ማኅበር ሆነው ሳሉ የአይሁድ ማኅበር»/ራእ2፡9/ ነን ማለት ነው:: በዚህ መልክ ከሆነ ደግሞ በመጽሐፈ ሰዓታት ውስጥ ያለው ጤናማ የሆነው ድርሰት የገባው ኑፋቄው

ተቀባይነት እንዲያገኝ ሲባል ነው እንጂ እግዚአብሔርን ለማክበር አይደለም።

## 5ኛ. ድርሰቱ በከፊል የተሰረቀ ሲሆን

ሌላው አማራጭ ደግሞ ደራሲው በመጽሐፈ ሰዓታት ውስጥ ጤናማ የሆኑትን ውዳሴያትንና ልመናዎችን እምነትንና ክርስትናን ጠንቅቆ በሚያውቅ ጸሐፊ ከተጻፈ ሌላ ጽሑፍ ውስጥ ምንጭ ሳይጠቅስ በስርቆት ወስዶ የራሱ በማስመሰል ከራሱ የስህተት ድርሰት ጋር የቀላቀለ ሲሆን ይህ መፋለስ ሊከተል ይችላል። ስለሆነም በመጽሐፈ ሰዓታት ውስጥ የሚገኙት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታዎች ምናልባት አንዳንዶች እንደሚገምቱት መጽሐፈ ሰዓታት በተደረሰበት ዘመን «ሎቱ ለባሕቲቱ ይደሉ ሰጊድ ማለትም ለእርሱ ብቻ ስግደት ይገባል» በማለት ለእግዚአብሔር ብቻ ሊቀርብ ስለሚገባው ስግደት/አምልኮ/ ይጋደሉ የነበሩት እንዲሁም የፍጡራንንና የቅርጻ ቅርጽን አምልኮት ይቃወሙ የነበሩት «አኃው/ወንድሞች/»* ከጻፏቸው ድርሰቶች ተሰርቀው ይሆናል።

ሌላው ሊታወቅ የሚገባው ነገር ከእነዚህ ምክንያቶች ውጪ እነዚህ እጅግ የተራራቁና እርስ በርስ የሚፋለሱ ሐሳቦች ከአንድ ጤናማና የተስተካከለ አእምሮ ካለው ሰው ሊወጡ የ ማይችሉ መሆናቸውን ነው። ይህ ሊሆን ይችላል ካልን ደግሞ «በረከትና መርገም» ከአንድ አፍ የሚያወጣ እንዲህ ያለ አንደበት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «የሚገድል መርዝ የሞላበት ወላዋይ ክፉት ነው» /ያዕ3፡8-10/ ተብሏል። እንደዚሁም «ምንጭስ ከአንድ አፍ የሚጣፍጥንና የሚመርን ውኃ ያመነጫልን? ...በለስ ወይራን ወይስ ወይን በለስን ልታፈራ ትችላለችን? ከጨው ውኃ ጣፋጭ ውኃ አይወጣም» ይለናል/ያዕ3፡11-12/።

---

* እነዚህ ሰዎች ከ15ኛው ክ/ዘመን ጀምሮ የነበሩና ለማርያምና ለመስቀል አንሰግድም በማለታቸው ምክንያት በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ትእዛዝ የተሠዉ ክርስቲያኖች እንደሆኑ ይተረካል፤ ሲጠሩሩም አኃው/ወንድሞች/ እየተባባሉ እንደነበር ይነገራል።

# ማጠቃለያ

ምንም እንኳን መጽሐፈ ሰዓታት በአንዳንድ ክፍሎች ውስጥ እውነትነት ያለውን ሐሳብ ይዞ ቢገኝም የዚህ እውነት በብዙ ሐሰቶች መካከል መገኘት ነፍሳትን ለማታለል የበግ ለምድ ሆኖ ከማገልገል በቀር እግዚአብሔርን አያከብርም፤ የሚገለገሉበትንም አይጠቅምም፤ ምክንያቱም ከእውነት ጋር የተደባለቀ ሐሰት ብቻውን ከቀረበ ሐሰት ይልቅ ጎጂና ሰይጣናዊ መሆኑ ለማንም የተሰወረ አይደለምና:: ስለሆነም በዚህች አነስተኛ መጽሐፍ ውስጥ እውነትነት ያላቸውን የመጽሐፈ ሰዓታት ክፍሎች ያነሳነውም ተጠቃሚዎቹ ከገቡበት ድንዛዜ እንዲነቁ ለማስቻል ብቻ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል::

በዚህ መጽሐፍ በተካተቱት በአራቱም ምዕራፎች እንደተመለከትነው መጽሐፈ ሰዓታት የተሰኘው መጽሐፍ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን ብቃት የሌለው ከመሆኑም ባሻገር የእግዚአብሔርን እውነትና ትክክለኛውን የክርስትና እምነት የሚጋፉ የስህተት ትምህርቶችን ያዘለ በመሆኑ እውነተኛ አማኞች ከእንዲህ ዓይነቱ ስህተት ማኅበረተኛ ከመሆን ሊርቁ ይገባቸዋል:: የእግዚአብሔር ቃል «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከዓመፅ ይራቅ»/2ጢሞ2:19/ እንደሚልና «ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ ርኩሱንም አትንኩ»/2ቆሮ6:17/ በማለት እንደሚያዛቸው ከዚህ ዓይነቱ በማር ከተለወሰ መርዝ ለእግዚአብሔር ክብር በመቅናት ራሳቸውን እንዲያገሉ በማሳሰብ ጥናቱን እንደመድማለን::

ስብሐት ለከ ኢየሱስ በአፈ ኵሉ ውዱስ
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ቀዳሴ ሥጋ ወነፍስ
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ለሰረቃን ዐብስ
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ዘኢትለወጥ ንጉሥ
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ቃለ አብ ቅዱስ

ማሳሰቢያ

ይህንንም መጽሐፍ ሆነ ሌሎች መንፈሳዊ ጽሑፎችን ተጻጽፋችሁ ማግኘት የምትፈልጉ በፖ.ሣ.ቁ. 14787 አ.አ. መጻፍ የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን